# ሐመር

ዘኦርቶዶክስ ተዋሕዶ

ሐመር ፲፯ኛ ዓመት ቁጥር ፪ ግንቦት-ሰኔ ፳፻፩ ዓ.ም




# ሐመር

ዘኦርቶዶክስ ተዋሕዶ

፲፯ኛ ዓመት ቁጥር ፪ ግንቦት/ሰኔ ፳፻፩ ዓ.ም.


## ይዘት


**መልእክት ዘማኅበረ ቅዱሳን**

* በሃይማኖት የመከባበር ባህላችንን እንጠብቅ!.......... ፪

**መልእክቶቻችሁ** .......... ፫

**በረከተ ወንጌል**

«በዓለ ሃምሳም የተባለው ቀን» .......... ፭

**ወቅታዊ ጉዳዮች**

* ዐሥር ነጥቦች ስለመጽሐፍ ቅዱስ .......... ፯
* ስለ ስብከቶቻችን እንወያይ.......... ፱

**ትምህርተ ሃይማኖት**

* ዐርገ እግዚእ ከመ ያለቡ ዕርገተ ጻድቃን .......... ፲፫
* ዕጣ በቤተ ክርስቲያን ትምህርትና ሥርዓት.......... ፲፮
* በእንተ ኵሎሙ ክህናት.......... ፲፱

**ምሰሬፍ** .......... ፳፩

**የጥያቄዎቻችሁ መልሶች**

* በክህነት መያዝ፣ መሻርና ውግዘት መካከል ያለው ልዩነት ምንድን ነው?.......... ፳፪

**ኪነ ጥበብ**

* ጽናት .......... ፳፭

**እናስተዋውቃችሁ**

* ከቅዱሱ ሐይቅ በረከቶች .......... ፳፯
* ጥብርያዶስ .......... ፴፩

**ክርስትና በማኅበራዊ ኑሮ**

* የሴቶች አለባበስና አጋጊያጥ .......... ፴፬

**ሐመረ ሕይወት**

* በመታመሜ ደካማነቴን፣ በመፈወሴ ሃይማኖቴን አውቄአለሁ.......... ፴፯

**ስቡጊዳ - የግእዝ ቋንቋ ትምህርት**

* ግእዝ ከእስያ ልሳናት ጋር ሲነጻጸር .......... ፴፱



**ዋና አዘጋጅ**
ዲያቆን ብርሃኑ አድማስ

**ም/ ዋና አዘጋጅ**
ዲያቆን ያረጋል አበጋዝ

**አዘጋጅ**
ዲ/ን ማለደ ዋስይሁን

**ከፍተኛ ሪፖርተር**
ኅሩይ ስሜ

**ሪፖርተሮች**
ጌታቸው በቀለ
ዲ/ን ምትኩ አበራ

**የገጽ መልክአ /ሌይ አውት/ ዲዛይነር**
ርብቃ ኃይለማርያም

**ረ/ የገጽ መልክአ /ሌይ አውት/ ዲዛይነር**
ወይንሸት ወልደጻድቅ

**ጸሐፊዎች**
ጸዳሉ ሁንዴሳ
ልደት አስፋው
ደብረወርቅ ተክለጽዮን

**የዝግጅት ክፍሉ**
☎ 011 1 553442

**የዝግጅት ክፍሉ:**
Email:- hamermk08@gmail.com

**የማኅበሩ ጽ/ቤት**
E-mail: eoc-m-kidusan@ethionet.et
www.eotc-mkidusan.org

**በማኅበረ ቅዱሳን የስሜን አሜሪካ መካነ ድር**
www.mahiberekidusan.org

*መ.ሣ.ቁ 80078*
*አዲስ አበባ*


## «ማኅበረ ቅዱሳን»

እግዚአብሔር ያከበራቸው
የነቢያት፣ የሐዋርያት፣ የጻድቃን፣
የሰማዕታት በአጠቃላይ የቅዱሳን ገድል፣
ትሩፋትና አማላጅነት የሚዘከርበት
በመሆኑ ይህን ስያሜውን አግኝቷል።

*በኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን በሰንበት ትምህርት ቤቶች ማደራጃ መምሪያ በማኅበረ ቅዱሳን የሚዲያና ሕዝብ ግንኙነት ዋና ክፍል በመጽሔት ዝግጅት ክፍል የሚዘጋጅ ትምህርታዊ መጽሔት።*

*የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያንን ትምህርተ ሃይማኖት፣ ሥርዐተ እምነትና ክርስቲያናዊ ትውፊት ጠብቆ የሚወጣ።*


www.eotcmk.org

# በሃይማኖት የመከባበር ባህላችንን እንጠብቅ!

ሰው በሥነ ፍጥረቱ በእግዚአብሔር አርአያ የተፈጠረ ክቡር ፍጥረት በመሆኑ አንድ ቢሆንም በዘመናት ባሳለፋቸው ጉዞዎች በገጠሙት የተለያዩ ተፈጥሮአዊና ሰው ሠራሽ፣ ማኅበራዊና ፖለቲካዊ ክስተቶች አንዱ ካንዱ የሚመሳሰልባቸው ወይም የሚለያይባቸው ነገሮች ይኖሩታል፡፡ ይህም በባህሉ፣ በቋንቋው፣ በሃይማኖቱና በአመለካከቱ የራሱ የሆነ መገለጫዎች አሉት፡፡ ይሁንና ሰው በዚህች ምድር በሚኖርባት አጭር ዘመን ሰላማዊ ኑሮ በመኖር የዕለት ምግባሩን ማከናወን የሚችለው አንዱ የሌላውን ጉዳይ አክብሮ መኖር ሲችል ነው፡፡ ሰው በተፈጥሮው ማኅበራዊ ፍጥረት ነው፡፡ ሰው ብቻውን ከሌላው መሰል ፍጥረቱ ጋር ሳይገናኝ መኖር አይችልም፡፡ አብሮ ለመኖር እግዚአብሔር የሰጠውን ሀብት በጋራ ለመጠቀም መከባበር ዓይነተኛ መማሪያ ነው፡፡

መከባበር ማለት ጠቅለል ባለ መልኩ ስናየው በሰዎች መካከል ያለውን ልዩነት ተቀብሎ አንዱ የሌላውን ሃይማኖት፣ ባህልና ማንነት አክብሮ የራሱንም ማንነት አስከብሮ መኖር ማለት ነው፡፡ አንድ ሰው እርሱ የማይቀበለውን የማያምነውን ነገር እንኳ ቢሆን ሌላው አምኖ ተቀብሎ የመኖር መብት በሰውነቱ እንዳለው መረዳት የመከባበር አንዱ ገጽታ ነው፡፡ ሰው በፈቃድ ነጻነቱ ተጠቅሞ በማይዘው አቋም የሚቀበለው ዋጋ የራሱ ሆኖ ነገር ግን በፍጥረቱ ክቡር እንደሆነ እናውቃለን፡፡ ነቢዩ «ሰው ክቡር ሆኖ ተፈጥሮ ሳለ» እንዳለው፡፡ እግዚአብሔር ሁሉን ፈጥሮ የሚገዛ አምላክ ሲሆን ለሚያምኑትና ለማያምኑትም ለደጋጎችና ለክፉዎችም ፀሐይን የሚያወጣ መግቦቱንም የማያጓድል አምላክ ነው፡፡ አስቀድመን እንዳልነው፡፡ ሁሉም እንደሥራውና እንደ ሃይማኖቱ መልካምነት በመጨረሻው ዘመን ፍርድ የሚቀበል ቢሆንም ሰው ሆኖ በመፈጠሩ ግን የመኖር መብቱን ጠብቆ እግዚአብሔር ፍጥረቱን ሁሉ ይንከባከባል፡፡ እንዲሁ ሁሉ ሰው በተፈጠረባት ምድር ሲኖር የሌላውንም የመኖር መብት መጋፋት የለበትም፡፡ በወንጌል እንደምናነበው «እንክርዳዱን እንንቀል ስንዴውን እንንከባከብ» ላሉት ሠራተኞች ጌታቸው «ተውአቸው እስከመከር ይኑሩ» አለ እንጂ ስንዴውን የማይመስል እንክርዳድ ሁሉ ይጥፉ አላለምና፡፡ ስለዚህ ክርስቲያን ሁሉ በሌላው ሃይማኖትና ማንነት ጣልቃ ሳይገባ የራሱን መስመር ጠብቆ መኖር ያስፈልገዋል፡፡

አገራችን ኢትዮጵያ የብዙ ወገኖች አገር፣ የብዙ ቋንቋዎች መነጋገሪያ የተለያዩ ሃይማኖቶች ተቋማት የማኅ፟በት አገር ናት፡፡ ኢትዮጵያ በአምልኮተ እግዚአብሔር የረጅም ዘመን ታሪክ ያላት እና ሕዝቧም በውስጡ ካለው ፈሪሃ እግዚአብሔር እና የጨዋነት መንፈስ የተነሣ እርስበርሱ ተከባብሮ ለዘመናት አብሮ የኖረ ነው፡፡ የሚመጣውን ሁሉ እጁን ዘርግቶ በመቀበልና በፍቅር በማስተናገድ ኢትዮጵያን እንግዳ አፍቃሪ እንግዳ ተቀባይ መሆንዋን በዓለም አሳውቋል፡፡ የራሱን ሃይማኖትና ባህል ጠብቆ የሌላውንም ባህልና ሃይማኖት አክብሮ በማኅበራዊና አገራዊ ጉዳዮች በጋራ ሲተጋገዝ ሲተሳሰብ ኖሯል፡፡ ይህ የመከባበር አኗኗር ለአፍሪካም ሆነ በመላው ዓለም ጥሩ ምሳሌ የሚሆን ነው፡፡ ከሌሎች አገሮች ልምድ እንደምናየው አንድ ቋንቋ ተናግረው በአንድ ሃይማኖት ኖረው እንኳ በፍቅር መኖር አቅቶአቸው ሲናወጡ እናያለን፡፡ ኢትዮጵያ ግን ብዙ ቋንቋዎች የሚነገሩባት ብዙ የተለያዩ የሃይማኖት ተቋማት ያሉባት አገር ሳለች በመከባበር ባህልዋ ግን ዓለምን አስደንቃ ኖራለች፡፡ ይህን ደግሞ ምንጊዜም ቢሆን ልንጠብቀው ልንከባከበው ይገባል፡፡ መልካም ባህላችንን ካልጠበቅነው የእኛ ላልሆነ ክፉ አመልና ባህል አልፈን እንሰጣለንና፡፡ ይህ ደግሞ በማንኛውም መልኩ አይጠቅመንም፡፡

ከቅርብ ጊዜ ወዲህ ግን በመከባበር ላይ የነበረን ባህል እየተዘነጋ ከእኛ በመነጨ ሳይሆን ከውጭው ዓለም በነፈስ የአክራሪነት መንፈስ በአንዳንድ ቦታና ገጠመኞች ሰላማችን ሲደፈርስ እናያለን፡፡ ይህ የሌላውን የመኖር፣ የማመን፣ የመሥራትና የመጠቀም መብት ያላገናዘበ አስተሳሰብ ለእኛ ለኢትዮጵያውያን ባዕድ ነገር ነውና ከእኛ ልናርቀው ይገባል፡፡ የተለያየ በጐ ያልሆነ ዓላማ አንግበው ለሚንቀሳቀሱ ኃይሎችም መሣሪያ እንዳይሆን ማንኛውም ዜጋ መጠንቀቅ ያስፈልገዋል፡፡ ከዚህም ሌላ ነቢዩ ኢሳይያስ እንዳለው «መራራውን ጣፋጭ፣ ጣፋጩን መራራ» በማለትና በማድረግ ክርስቲያኑን ከክርስቲያን፣ ክርስቲያኑን ከመንግሥትና ከሌሎችም አካላት ጋር ለማጋጨት ጥረት የሚያደርጉ የውስጥ አካላት ሊኖሩ ስለሚችሉ ክርስቲያኑና የሚመለከታቸው ሁሉ በንቃት መቆም ይገባቸዋል፡፡

ለእኛ የሚበጀን በመከባበር ለአገራችን ዘርፈ ብዙ ዕድገትና አንድነት በጋራ መሥራት ነው፡፡ ቤተ ክርስቲያን ራስዋም መሠረትዋም የሰላም ንጉሥ ኢየሱስ ክርስቶስ በመሆኑ ለሰላም ያላት ቦታ ከፍተኛ ነው፡፡ ሰላምን ትሰብካለች ሰላምን ታስተምራለች፡፡ ሁሉም በሰላም ለመኖር የሰላም ተጠቃሚ ለመሆን ከእርሱ የሚጠበቀውን ድርሻ ሊወጣ ይገባል፡፡ ነገር ግን አንዱ ለሰላም ሲጥር ሌላው ለትንኮሳ የሚሮጥ ከሆነ አስቸጋሪ ይሆናል፡፡ የመከባበር ባህላችንንም ያጠፋብናል፡፡ ስለዚህ ሁሉም የድርሻውን መወጣት አለበት፡፡ ከቅዱስ መጽሐፍ እንደምንረዳው እኛ ሊሆንልን፣ ሊደረግልን የምንሻውን ለሌላው ወንድማችንም እንደሚያስፈልገው ማመን እንዳለብን ነው፡፡ ያ ከሆነ የሌላውን ሰላም የማደፍረስ፣ መብቱንም የመጋፋት አስተሳሰብ አይኖረንም፡፡ መብት ሲባል ደግሞ የሌላውን መብት አክብሮ የራስንም መብት አስጠብቆ መኖር ማለት ነው እንጂ የራስን አስጠብቃለሁ በሚል ሰበብ የሌላውን መብትና ሰላም ማናጋት አይደለም፡፡

መከባበር ከአንድ ወገን ብቻ የሚጠበቅ የግል ጉዳይ አይደለም፡፡ ከሁሉም ወገን የሚጠበቅ የጋራ ሓላፊነት ነው እንጂ፡፡ አንዱ ሲሰፋ ሌላው የሚቀድ አንዱ ሲጠግን ሌላው የሚያፈርስ ከሆነ ጤናማ ኑሮ መኖር አይቻልም፡፡ የተቋጠረውም ይበተናል፤ የተቀዳውም ይፈሳል፡፡ ስለዚህ የሁሉንም የጋራ ትኩረትና ትብብር ይጠይቃል፡፡ አንዳንድ ጊዜ ግን የራስን ድካምና ችግር ለመሸፈን የጤናማውን ስም ማጥፋትና ንጹሐንን ወንጀለኛ አስመስሎ ማናፈስ አንዱ የፀረ መከባበር ደቀመዛሙርት መገለጫ በመሆኑ ልንጠነቀቅ ይገባል፡፡

በተለየ የሃይማኖት ተቋማት ለመከባበር ባህላችን መጠበቅ ትልቅ አስተዋጽኦ ማድረግ ይጠበቅባቸዋል፡፡ በመሆኑም ለአገራችን ሰላምና ለሕዝባችን አንድነት የመከባበር ባህላችንን መጠበቅ እንደሚኖርብን ማኅበረ ቅዱሳን ያምናል፡፡ በመከባበር ላይም ብዙ ሥራዎችን እየሠራ ይገኛል፡፡ በሚዲያዎቹም ሰፊ ሽፋን ሰጥቶዋል፡፡ ለምሳሌ በጥቅምት ፲፱፻፺፱ ዓ.ም እትሙ በስምዐ ጽድቅ ጋዜጣ ርዕሰ አንቀጽ ላይ የመከባበር ባህል ዳብሮ መቀጠል እንዳለበት የመንግሥትም ሆነ የአካባቢ ሽማግሌዎች ሊወጡ የሚገባቸውን ድርሻ ጠቁሞአል፡፡ በዚሁ ዓመትም በኅዳር ወር እትሙ በመከባበር ላይ ሰፊ ዘገባ አቅርቧል፡፡ በተለያዩ ጊዜያትም አብሮ ተከባብሮ መኖር የሚያስገኘውን አገራዊ፣ ተቋማዊና ግለሰባዊ ጥቅም ለማስቀመጥ ተሞክሮዋል፡፡ ሃይማኖትን በመከላከል ረገድ ያለበትን ክርስቲያናዊ ሓላፊነት ደግሞ ለተጠየቁ ጥያቄዎች መልስ በመስጠት፣ በሃይማኖቱ ላይ የቀረቡ ትችቶችንም ተገቢ አለመሆናቸውን በመጠቆምና ክርስቲያኖች ሃይማኖታቸውን ተችተው በወጡ ጽሑፎች ግራ መጋባት እንዳይፈጠርባቸው በሐመረ ተዋሕዶ ቁጥር ፩ እና ፪ እትሞቹ አፖሎጂያዊ /መጠበቂያ/ ጽሑፍ አዘጋጅቷል፡፡

አሁንም ቢሆን ማኅበረ ቅዱሳን ለመከባበር ትልቅ ቦታ በመስጠት በዚህ ጽሑፍም ተጠናክሮ እንዲቀጥል አበክሮ ማሳሰብ ይወዳል፡፡ አባቶቻችን ሃይማኖታቸውን ሥርዓታቸውን አጥብቀው ይይዛሉ እንጂ ሌላው አይኑር አይሉም፡፡ በሃይማኖት በባህል የማይመስላቸውን እንኳ ከታሪክ እንደምንረዳው በእንግድነት ተቀብለው ያስተናገዱ ናቸው፡፡ ማንኛውም ሰው ለሚያምንበት ሃይማኖትና ሥርዓት ተገዝቶ በትክክልም በዛ መኖር መቻሉ በሌላው ላይ የሚያመጣው ተጽዕኖ የለም፡፡ ችግሩ ግን የራሱን ሃይማኖትና ባህል ለመጠበቅ ሌላው አይኑር ሲል ነው፡፡ እንዲህ ከሆነ ነው በዘመኑ አነጋገር አክራሪ ነው የሚባለው፡፡ አክራሪነት ደግሞ የመከባበር ጠላት በመሆኑ አክራሪነትን አጥብቀን ልንጠላው ይገባል፡፡ ስለዚህ የሌላውን መብት አክብሮ የራስን ሃይማኖት አጥብቆ በመያዝና ሌላው ጨርሶ መኖር የለበትም በሚል አክራሪነት መካከል ያለውንም ልዩነት መረዳት ይገባል፡፡ ለአንዳንዶች የሃይማኖት ትእዛዛትን ጠብቆ ሳያጓድሉ ሳያዛንፉ እየተጉ መኖን እንደ አክራሪነት በማሰብ የባሰ ሌላ ቀውስ እንዳይፈጥሩ መጠንቀቅ ይገባልና፡፡ የመንግሥት አካላት የሃይማኖት ተቋማትም ሆነ ሌሎች ባለድርሻ አካላት የመከባበር ባህልን ጠብቆ ለመኖር በጋራ አብሮ መሥራት ይኖርባቸዋል፡፡ በተጀመረውም መልካም ጅምር መቀጠል የበለጠ በመቀራረብና በመወያየት መሥራት ከፍተኛ ጠቀሜታ ይኖረዋል፡፡ እኛ ኢትዮጵያውን ለረዥም ዘመን በቆየና በዳበረ ባህላችን በመመካከር በመሸመጋገል እርቀ ሰላምን በሁላችን ዘንድ በማስፈን ለአገራችን ዕድገትና ለጋራ ጥቅማችን በጋራ መራመድ አለብን፡፡ መልካሙን ክፉ ክፉውን መልካም አድርገው እያሳዩ ሊለያዩን ለሚያስቡት ጠላቶቻችንም ቀዳዳ መስጠት የለብንም፡፡ መከባበር ረጅም ዘመን የቆየ ኢትዮጵያዊ ባህል ነው፡፡ ይህ ተጠብቆ ለትውልድ እንዲደርስ ክርስቲያኖች ሁሉ እንጠብቀው፤ እንከባከበው፡፡ ሐዋርያው «ቢቻላችሁስ ከሁሉም ጋር በሰላም ኑሩ» /ሮሜ ፲፪ ÷ ፲፰/ ብሎናልና፡፡✦

*ወስብሐት ለእግዚአብሔር*



www.eotcmk.org



## አመስግኑልኝ

ዛሬ ብዕሬን እንዳነሣ ያደረጉኝ ምክንያቶች በኪነ ጥበብና በመንገደኛው ዓምድ የተመለከትኳቸው ነገሮች ናቸው። በኪነ ጥበብ ዓምድ አንዱዓለም አባተ /የአፀደ ልጅ/ የሚጽፋቸው ጽሑፎች እጅግ በጣም ስላስደሰተቱኝ ጸሐፊውን በርታ በሉልኝ።

ሌላው ደግሞ መንገደኛው ዓምድ ነው። መንገደኛው ጠፋብን ምነው? ጉዞውን /ዙረቱን/ አቆመ? መረረው? በእርግጥ መዞር አስቸጋሪ ነው። ያው የእግዚአብሔር ተጓዥ ቢሆንም አትሰልችብን፤ ጠንክር፤ ረጅም መንገድ መጓዝን ልመደው፤ በኋላም ርቀት መጓዝ ትችላለህ በሉልኝ።❖

*ባለው ሙኔ*
*ደብረ ማርቆስ*

## ይታሰብበት

መልእክት ወደ እናንተ ለመጻፍ ያነሳሳኝ አንድ ሁሌ በጭንቅላቴ የሚመላለስ ነገር ነው። እኔ የተወለድኩት ወታደሮችም በብዛት በሚኖሩበት አካባቢ በመሆኑ፤ ስለ ወታደሮች መንፈሳዊ ሕይወት ዘወትር ያሳስበኛል። በትምህርት ጊዜ ብዙ ቅርርብ ነበረንና አብዛኛዎቹን ስመለከታቸው ስለመንፈሳዊ ሕይወት ዕውቀቱ የላቸውም። ለዚህ ምክንያቱ ደግሞ መንፈሳዊ ትምህርትና ጽሑፎችን ስለማያገኙ ነው። በዚህ የተነሣ ሕይወታቸው በመጥፎ ሱሶች /መጠጥ፣ ሲጋራና ጫት፣ ዝሙት .../ የተበላሸና ብሎም ለበሽታዎች በቀላሉ የተጋለጡ እየሆኑ ነው። ማኅበረ ቅዱሳንና ሰንበት ት/ቤቶች በውትድርና ሕይወት ውስጥ ላሉ እኅቶችና ወንድሞች የስብከተ ወንጌልና የተለያዩ የመንፈሳዊ አገልግሎት እንቅስቃሴዎች የሚሰጥበትን አማራጭ ቢያስቡበት መልካም ነው እላለሁ።❖

*ዲ/ን ፍስሐ ጽዮን*

## ተስፋ

በሁለት የሐመር ተከታታይ እትም ከዶ/ር ዓለማየሁ ዋሴ ጋር የተደረገው ቃለ መጠይቅ ብዙ ነገር አሳውቆናል። በመጀመሪያው ክፍል «ታሪክ ራሱን ይደግማል» እንዲሉ፤ በካርቦን ትሬድ ቤተ ክርስቲያን ለራሷ ቀርቶ ለሀገሪቱ ተስፋ እንደምትሆን ገልጸዋል። በሁለተኛው ክፍል ደግሞ ስለ ሕይወት ተሞክሮአቸው የሰጡን ትምህርት እጅግ ማራኪ ነው በተለይ የዓለሙንና የቤተ ክርስቲያንን ምሁር /የፕሮፌሰሩንና የድኅ. መምህሩን/ ሲያወዳድሩ፤ በዓለሙ ያለውን መባዘን በክርስቶስ ቤት ደግሞ ያለውን ሰላም ተረድቻለሁ። ስለ ሃይማኖታቸው ያላቸውን ቁርጠኝነት፤ እምነታችንን በጊዜ፣ በቦታ በሥራ ምክንያት ሊወሰን /መቀነስ/ እንደሌለበትም ተረድቻለሁ። እንደበታቸው ብዙ ቁም ነገርና ተጨባጭ ዕውቀት አግኝቻለሁ። ተፈጥሮን የማድነቅ ባህሪ ስለሚኖረኝም በጣም ረካሁ፣ ተደሰትኩ። እንዲሁም የሕይወት ተሞክሮአቸውና ፍልስፍናቸውን ከክርስትና ኑሮ ጥንካሬአቸው ጋር አጫውተውናል። «ሃይማኖቴን በማንኛውም ጊዜ አብሮኝ እንዲኖር ጥረት አደርጋለሁ» ይሉ ነበርና። እንደዚህ ዓይነት ምሁራን ለቤተ ክርስቲያን እና ለሀገር የሚበጁ ናቸው። ዝግጅት ክፍሉም ወደፊት ሌሎች ምሁራንንም እየጋበዛችሁ ስለ ሀገራችን፣ ስለ ሃይማኖታችን የሚያስተምሩ፣ የሕይወት ተሞክሮአቸውን የሚያካፍሉንን ቃለ መጠይቅ ቢቀርብ መልካም ነው። ከሕይወት ተሞክሮአቸው ብዙ እንማራለን።❖

*ማቴዎስ ሉሃ/ወላይታ ዞን አርብ ከተማ/*
*እና መ/ር ዓለሙ በላይ /ዳንግላ/*

## ራሴን እንድመረምር አድርጐኛል

በኪነ ጥበብ ዓምድ «ይቅርታው» በሚል ርእስ የቀረበው እውነተኛ ታሪክ በብዙ መንገድ /በሚረባውም በማይረባውም/ ተኮራርፈው በመንፈሳዊ አገልግሎት ለሚያገለግሉም ሆነ ይህን ለሚያነቡ ለሌሎች በጣም ያስተምራል። ምንም እንኳን አንብቦ ከጽሑፍ መማር የአኩራፊዎች ፈንታ ቢሆንም፤ ለእኔ ግን ይህ ጽሑፍ ራሴን እንድመረምር አድርጐኛል።❖

*ጌታሰው አምሳሉ*
*እስቴ*

## ብታሳትፉን

በአንድ ወቅት ያወጣችሁት የሥነ ጥበብ /ሥነ ጽሑፍ፣ ሥዕል፣ ድርሰት/ ውድድር በጣም የሚያስደስት ነው። እንደዚህ ዓይነት መድረኮች ብዙ ክህሎት ያላቸውን ወጣቶች ከማሳተፋቸውም በላይ ባላቸው ችሎታ አስተማሪ የሚሆኑ ሥራዎችን ማቅረብ የሚችሉትንም ያበረታታል። እንደከዚህ ቀደሙ አሁንም ውድድሩ የሚወጣበትን ወቅት እናፍቃለሁ።❖

*ታምር አዳም*
*ምሥራቅ ጐጃም*
*ብቸና*

ከዚህ በታች ስማችሁ የተዘረዘረው አንባብያን ደብዳቤዎቻችሁ ደርሰውናል። እናመሰግናለን። መልእክቶቻችሁንና የጥቆማ ሐሳቦቻችሁን ወደፊት እንደ አስፈላጊነታቸው እንጠቀምባቸዋለን።

ሰሎሞን ደሳለኝ - አዲስ አበባ፤ ዲ/ን ጋሻው ውቤ-ሰሜን ጎንደር፤ ወልደ ሰንበት-ጎንደር፤ ዲ/ን ኩራባቸው ሣህለ -ወላይታ ሶዶ፤ ዳዊት ጥበቡ- ወንዶ ገነት፤ አቶ አሳየኸኝ ይልማ- እምድብር፤ አሸናፊ መኩሪያ-ቴፒ፤ ታደሰ አበበ -ናዝሬት፤ ኃይሉ ተስፋዬ ዲላ፤ ደረጀ ጀማል- ዲላ ዩኒቨርስቲ፤ መ/ር አናንያ አስፋው -ምዕራብ ሐረርጌ፤ መስፍን አበጀ - አዲስ አበባ፤ ብርሃኑ ከተማ- አዲስ አበባ፤ የሺጥላ ኃይሌ- ምዕራብ ጐጃም ዞን።



www.eotcmk.org



## የቤተ ክርስቲያን ሕግ በሁሉም ምእመናን እኩል ይከበር

ለሐመር ጋዜጣ አዘጋጆች እንደምን አላችሁ:: ዛሬ ል ጽፍላችሁ የተነሣሁት በዓብይ ጾም ስለታዘብኩትና በጣም ስላሳዘነኝ ጉዳይ ነው:: ይኸውም ዓሣን በጾም ወቅት መብላት እና ባለመብላት መካከል ያለው ጉዳይ ግራ ስላጋባኝ ነው:: የቤተ ክርስቲያን ቀኖና እንደማይበላ ይደነግጋል:: ይህንንም ተቀብሎ የሚተገብር የቤተ ክርስቲያኒቱ ምእመናን አሉ:: እንደገናም ደግሞ የተፈቀደ ይመስል የቤተ ክርስቲያን ዓበይት አጽዋማት ሲጀመሩ ሲበላ ይታያል:: እኔን ግን በጣም ያስደነገጠኝ እና ተፈቅዶዋል እንዴ እንድል ያደረገኝ ደግሞ እዚህ በአዲስ አበባ በአራት ኪሎ አካባቢ ከሚገኙት ሬስቶራንት መካከል በአንዱ ውስጥ ያጋጠመኝ እውነታ ነው:: ይኸውም በቤተ ክርስቲያንዋ ውስጥ በከፍተኛ የአገልግሎት ደረጃ ላይ ያሉ በሰባኪነት እና በዘማሪነት የሚታወቁ ባሳለፍነው ዓብይ ጾም ውስጥ በምሳ ሰዓት ላይ የዓሣ ሥጋ ሲበሉ ሳይ ዓሣ ተፈቅዶዋል እንዴ የሚል ጥያቄ ስለፈጠረብኝ ምላሽ እንድትሰጡኝ ስል በእግዚአብሔር ስም እጠይቃለሁ::

ተፈቅዶ ከሆነ ለምን ለምእመናን በይፋ ተነግሮ በመምህራንና በዘማርያን ላይ ጥርጣሬ አድሮባቸው ከመሰናከል እንዲጠበቁ አይደረግም? ካልሆነ ደግሞ ከቤተ ክርስቲያን ሥርዓት ውጪ በዓመፅ የሚንቀሳቀስ የሰባክያንና የመዘምራን ቡድን አለ ማለት ነው:: ለማንኛውም ምላሽ እፈልጋለሁ::✥

*ሥነ ጊዮርጊስ*
*ከአዲስ አበባ*

### ከዝግጅት ክፍሉ

ውድ ወንድማችን ዓሣ በዓቢይ ጾም እንዲበላ የተፈቀደበት አዲስ ሥርዓት አልተሠራም:: በዚህ ወቅት ከማኅበረ ክርስቲያኑ አንድነት ተለይተው በራሳቸው ፍልስፍና የሚራመዱ ዘማሪና ሰባክያን ካሉ ሊመከሩ ይገባል እንላለን:: ምክንያቱም ዓሣ የሥጋ ዓይነት እንጂ የቆሎ ወይም የቅጠል ዓይነት አይደለም:: ቅዱስ ጳውሎስም «የዓሣም ሥጋ ሌላ ነው» በማለት የሥጋ ዓይነት መሆኑን ነግሮናልና:: /፩ቆሮ.፲፭÷፴፱/ ስለዚህ በዚህ መንገድ የሚጓዙ ምእመናን በተለይም «ታዋቂ» የሚባሉ ሰባክያንና ዘማርያን ምእመናን አንድ ሐሳብ አንድ ልብ ሆነው ከሚጾሙበት ጊዜ ተለይቶ ያንን በማድረጋቸው የሚያገኙት ትርፍ ምን እንደሆነ ራሳቸውን ይጠይቁ እንላለን::

## የሕይወት ስንቅ

እኛ በሕግ ጥላ ሥር ለምንገኝ ታራሚዎች የእግዚአብሔር ቃል ዘወትር ያስፈልገናል:: በመሆኑም ሐመር መጽሔት ወደ ቤተ መጻሕፍታችን በምትደርስን ወቅት በአንባቢያን ትሞላለች:: ይህ ደግሞ የሚያመለክተው ምን ያህል የእግዚአብሔርን ቃል መጠማታችንን ነው:: በሐመርም ሆነ በስምዐ ጽድቅ በተለያየ ዓምድ የምታነሧቸውን ሃይማኖታዊ ጽሑፎች አንድም ሳናስቀር እናነባቸዋለን:: ሌሎች ያላነበቡትም ካሉ የያዟቸውን ጽንሰ ሐሳብ በማስተዋወቅ እንዲያነቧቸው ግፊት እናደርጋለን:: በተለይ በቅርቡ በሐመር ፲፮ኛ ዓመት ቁጥር ፭ ዕትም ከዶ/ር ዓለማየሁ ዋሴ ጋር በተደረገው ቃለ ምልልስ ቅድስት ቤተ ክርስቲያናችን ምን ያህል ለኢትዮጵያ ደንህብት፣ ልማትና ጥበቃ የምታበረክተውን አስተዋጽኦ ተረድተናል:: በመዝሙራችን በኩል ያሉ ችግሮችና መፍትሔዎቻቸው፣ ስለ ስብከቶቻችንና በአሁኑ ጊዜ በጣም አሳሳቢ የሆኑ ወቅታዊ ችግሮች ... ወዘተ በመጽሔቷ የምታቀርቡት ትምህርት ማንኛውም ክርስቲያን አንብቦት በቀላሉ ሊረዳው የሚችል ነው:: እኛም የቅድስት ቤተ ክርስቲያናችንን ትምህርት በትክክል ጠንቅቀን በማወቅ ለወደፊቱ በዓለማዊም ሆነ በመንፈሳዊ ሕይወታችን አስተማማኝ የሕይወት ስንቅ በእስር ቤት ሆነን ለመሰነቅ አስችሎናል:: የእናንተም ጥረትና ዓላማ ፍሬ እንዲያፈራ፣ እኛም ከዘመኑ አታላይ ሰባኪዎችና ተኩላዎች ራሳችንን እንድንጠብቅ አስችሎናል::✥

*በትረ ጊዮርጊስ*
*ከወልድያ ማረሚያ ቤት*
*ቤተ መጻሕፍት*

### ሃሎ

በስምዐ ጽድቅ ጋዜጣ ያነበብነው በደቡብ ክልል በሆሳዕና አካባቢ ታየ የተባለውን ተአምር አንብቤዋለሁ:: በሆነውም ነገር እግዚአብሔር ልጆቹን አስተምሮናል:: የሆነው ነገር ግን በእጅጉ ተብራርቶ በሐመር መጽሔት በሰፊው ቢዘገብና የበለጠ መረጃ እንድናገኝ ቢሆን መልካም ነው::

*ጫኔ*
*ከመቀሌ*


በስመ አብ ወወልድ ወመንፈስ ቅዱስ አሐዱ አምላክ አሜን::

# ታላቅ የቅዱሳት መጻሕፍት ሽያጭ ሳምንት

ምግብ የሰውነት፣ ንባብ ግን የነፍስ ምግብ ነው::

ያለ ቅዱሳት መጻሕፍት የሚመራ ሕይወት ያለልብ የሚኖር ሰው ነው::

ፈልገው ያጡአቸው መንፈሳዊ መጻሕፍትን፣ መጽሔቶችን፣ ጋዜጦችን፣ ካሴቶችን እና የቆዩ ኅትመቶችን ለማግኘት የግቢ ጉባኤ ተማሪዎች እንዲሁም ምእመናን ያለባቸውን የአቅምና የአቅርቦት ችግር ለማቃለል ይረዳ ዘንድ ታላቅ የቅዱሳት መጻሕፍት ሽያጭ ሳምንት ተዘጋጅቷል::

ከሰኔ ፲፱ እስከ ሰኔ ፳፰/፳፻፩ ዓ.ም

ሁሉምንም ተሸላሚ የሚያደርግ ልዩ ዕጣ ተዘጋጅቷል::

ከመ/ፖ/ቅ/ቅ/ማርያም ገዳም ፊት ለፊት እየተሠራ በሚገኘው በማኅበሩ ሕንጻ

ነፍስዎን በቃለ እግዚአብሔር ያለምልሙ!

*በኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን*
*በሰንበት ት/ቤቶች ማደራጃ መምሪያ*
*ማኅበረ ቅዱሳን*

# «በዓለ ሃምሳም የተባለው ቀን»

ቀሲስ ፋሲል ታደሰ

ሐዋ. ፪፥፩-

በዓለ ሃምሳ በዓለ ጰራቅሊጦስ ወይም በዓለ ጰንጠቆስጤ መንፈስ ቅዱስ ለሐዋርያት የወረደበትን ቀን የምናስብበት ከዐበይት በዓላት አንዱ ነው፡፡ በዚህም ዕለት ትንቢተ ነቢያት ተፈጽሟል፤ ለሐዋርያት ምስጢር ተገልጦላቸዋል፤ ኃይልንም ተጎናጽፈዋል፡፡ ይህችን ዕለት ቅዱስ ዮሐንስ አፈወርቅ «የቤተ ክርስቲያን የልደት ቀን ናት» ይላታል። በመሆኑም ቤተ ክርስቲያን በየዓመቱ ከትንሣኤ በሃምሳኛው፣ ከዕርገት በዐሥረኛው ቀን ትውፊቷን ጠብቃ በዓሉን ታከብራለች፡፡ ይህ ዕለት በዓለ ሃምሳ፣ ጰንጠቆስጤ፣ ጰራቅሊጦስ ይባላል፡፡ ለመሆኑ የቃላቶቹ ትርጉምና መነሻ ምንድነው? በጥቂቱ እንመለከታለን፡፡


## ፩. በዓለ ሃምሳ

እስራኤላውያን በስደት ምክንያት ብዙዎቹ በተለያዩ ሀገሮች ከሚኖሩ አሕዛብ ጋር ተቀላቅለው በሕጋቸው ይኖሩ ነበር፡፡ ከአሕዛብም ወገን የእስራኤልን አምላክ እግዚአብሔርን አምነው ወደ ይሁዲነት የገቡም አሉ፡፡ እነዚህ የተለያዩ ቋንቋዎችን የሚናገሩ እስራኤላውያን ሁሉ በዓለ ፋሲካን ለማክበር በኢየሩሳሌም ይሰባሰባሉ፡፡ ይህ በዓል በብሉይ ኪዳን ?እሸት በዓል /በዓለ ሰዊት/ ይባላል፡፡ በሃምሳኛይቱ ቀን በዓለ ሰዊት /የእሸት በዓልን/ ያከብራሉ፡፡ በዓሉን ለማክበር ሀገሩ የነረበውም ከሀገሩ የራቀውም ስንቁን ይዞ በዚያው ይሰነብታል፡፡ የእሸት በዓል የሚ ባለውም ከፋሲካቸው በሃምሳኛው ቀን ካመረቱት ምርት በኩራቱን ለቁርባን በማቅረብ እንዲያከብሩት ከእግዚአብሔር በታዘዙት መሠረት የሚከበር በዓል ነበር፡፡ /ዘሌ. ፳፫፥፲፮-፲፯/

ይህ በዓል ሲወርድ ሲዋረድ መጥቶ ከዘመነ ሐዋርያት ደረሰ፤ ታዲያ በዓሉን ለማክበር የሔዱት ተመልሰው፤ ያሉት ተሰብስበው በነበረበት ዕለት ለሐዋርያት በጽርሐ ጽዮን መንፈስ ቅዱስ ስለወረደላቸው «በዓለ ሃምሳ» የሚለውን ስያሜም አገኘ፤ ከጌታችን ትንሣኤ በኋላ በሃምሳኛው ቀን የሚከበር ማለት ነው፡፡

## ፪. ጰንጠቆስጤ

የዚህ በዓል ሁለተኛው ስያሜ ሲሆን፤ ጰንጠቆስጤ /ጰንጠኮንቴ/ ማለትም ከሃምሳኛይቱ ቀን አስቀድሞ የሚውሉት አርባ ዘጠኝ ቀናት ማለት ነው፡፡ምሳሌ ሆኖ የኖረው ዕለትም ፍጻሜ ማግኘቱን ያመለክታል፡፡



፩




. /የሐዋ.ሥራ ፪፥፩/

## ፫. ጰራቅሊጦስ

የግሪክ ቃል ሲሆን «መንጽሂ፣ ወመጽንዒ፤ የሚያነጻ፣ የሚያጸና» ማለት ነው፡፡ ይህም ከአብና ከወልድ ጋር ለምንሰግድለት የዘለዓለም አምላክ ለሆነው የሚያነጻ፣ የሚያጸና፣ የሚቀድስ የመንፈስ ቅዱስ መጠሪያ ነው፡፡ በዚህ የተነሣ በዓለ መንፈስ ቅዱስ ለማለት በዓለ ጰራቅሊጦስ እንለዋለን፡፡

መንፈስ ቅዱስ በጽርሐ ጽዮን የወረደበትን ሁኔታ መጽሐፍ ቅዱስ እንደሚከተለው ገልጾታል። «በዓለ ሃምሳም የተባለው ቀን በደረሰ ጊዜ በአንድ ልብ ሆነው አብረው ሳሉ ድንገት እንደሚነጥቅ ዐውሎ ነፋስ ከሰማይ ድምፅ መጣ ተቀምጠው የነበሩበትንም ቤት ሁሉ ሞላው ... በሁሉም መንፈስ ቅዱስ ሞላባቸው መንፈስም ይናገሩ ዘንድ እንደሰጣቸው በሌላ ልሳኖች ይናገሩ ጀመር» ይላል። /ሐዋ. ፪፥፩-፬/

*በነፋስ አምሳል መውረዱ፡-* ነፋስ የመንፈስ ቅዱስ ምሳሌ በመሆኑ ነው፡፡ መድኃኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ስለ ምስጢረ ጥምቀት እና የመንፈስ ቅዱስን ጥበብ ልጅነት ስጪነት ለኒቆዲሞስ ሲያስተምረው መንፈስ ቅዱስን በነፋስ መስሎ ተናግሯል፡፡ /ዮሐ.፫፥፰/ ምሳሌነቱም ነፋስ ረቂቅ ነው፤ መንፈስ ቅዱስም ረቂቅ ነውና፡፡ /ዮሐ.፬፥፳፬/ ነፋስ ኃያል ነው፤ ፍሬን ከገለባው ይለያል፤ መንፈስ ቅዱስም ጻድቃንን ከኃጥአን ይለያልና፡፡ ነፋስ በምልዓት ሳለ አይታወቅም፤ ባሕር ሲገሥጽ፤ ዛፍ ሲያናውጽ እንደሚታወቅ፤ መንፈስ ቅዱስ በምልዓት ሳለ አይታወቅም፤ ቋንቋ ሲያናግር፤ ምስጢር ሲያስተረጉም የሚታወቅ ነውና፡፡ ነፋስ መዓዛን ያመጣል፡፡ መንፈስ ቅዱስም መዓዛ ጸጋን ያመጣልና፤ ነፋስ ለሰውና ለተክል ዕድገት አስፈላጊ ነው፡፡ «እስመ ነፋስ ይስህቦ ለቁመተ ሥጋ» እንዲል መንፈስ ቅዱስም መንፈሳዊ ዕድገት ይሰጣልና፡፡

*በእሳት አምሳል መውረዱ፡-* እሳት የመንፈስ ቅዱስ ምሳሌ በመሆኑ ነው፡፡ ይህም «ወውእቱ ያጠምቀክሙ በመንፈስ ወበእሳት» በሚለው የቅዱስ ዮሐንስ ትምህርት ይታወቃል፡፡ /ማቴ.፫፥፲፪/ ምሳሌነቱም እሳቱ ኃያል ነው፤ መንፈስ ቅዱስም





'
www.eotcmk.org

በባህርዩ ኃያል ነውና። እሳት ጣዕምን ያመጣል፤ መንፈስ ቅዱስም ጣዕመ ጸጋን ይሰጣልና። እሳት ከአንዱ ፋና ሃምሳና ስድሳ ፋና ቢያበሩበት ተከፍሎ የለበትም፤ መንፈስ ቅዱስም ተከፍሎ ሳይኖርበት ጸጋና ረድኤትን ሲሰጥ ይኖራልና። እሳት የበላው መሬት ለእህል ለተክል እንደሚያመች መንፈስ ቅዱስ ያደረበት ሰውነትም ለገድል ለትሩፋት ያመቻልና። እነዚህን በመሰሉ ምሳሌዎች ነገረ መንፈስ ቅዱስን እንረዳለን ማለት ነው።

## መንፈስ ቅዱስ በበዓለ ሰዊት ዕለት ለምን ወረደ?

በዓለ ሰዊት /የእሸት በዓል/ ለበዓለ ሃምሳ ምሳሌ ሆኖ ይከበር ነበርና ነው። ይህም ለፋሲካቸው ሃምሳኛ ቀን መሆኑ፤ ለአማናዊው ትንሣኤ ሃምሳኛውን ቀን የመንፈስ ቅዱስ በዓል እንደሚሆን ቀድሞ በምሳሌ እንደትንቢት ማመላከቱ ነው። በተጨማሪም በበዓለ ሰዊት ካህናተ ኦሪት ሕዝቡ ያመጡትን ዓሥራት፣ በኩራቱን እየተመገቡ ለሕዝቡ ይጸልዩላቸዋል። በዚህም ከራብ፣ ከቸነፈር ተጠብቀው ይኖሩ ነበር። /ዘጸ.፳፫÷፴፱/ በበዓለ ጰራቅሊጦስም ሐዋርያት መንፈስ ቅዱስን ተቀብለው ምእመናንን እያጠመቁ፣ እያቆረቡ ጸጋና ክብርን አስጥተዋልና።

*መንፈስ ቅዱስ ልሳን መስጠቱ፡-* ልሳን በቁሙ የአንደበት ክፍል /ሕዋስ/ ስያሜ ነው። የልሳን መሣሪያነት ለንግግር የሚያበቃ ነው። በሌላ አገላለጽ ቋንቋ ነው። መንፈስ ቅዱስ ለሐዋርያት በወረደበት ዕለት ከሰጣቸው ጸጋ አንደኛው ልሳን ነው። ልሳን ባልተማሩበት፣ ባልኖሩበት . . .ቋንቋ መናገር መቻልን ያመላክታል። እግዚአብሔር ባወቀ በዚህ ዕለት የባህርይ ሕይወቱ መንፈስ ቅዱስን ለሐዋርያት የሰደደው በዚያ የተሰበሰቡ ከብዙ ሀገር የመጡ ልዩ ልዩ ቋንቋ ይናገሩ የነበሩ እስራኤላውያን ሁሉ በራሳቸው ቋንቋ የክርስቶስን ነገር ሰምተው ያምኑ ዘንድ ነው። ሕዝቡም በየገዛ ቋንቋቸው ሲናገሩ ሰምተዋል ለዚህም ነው። «እያንዳንዱም በገዛ ቋንቋው ሲናገሩ ይሰማ ስለነበር የሚሉትን አጡ» የሚለው። /ሐዋ. ፪÷፮/ ከሰሙትም ውስጥ በዚሁ ቀን ሦስት ሺሕ ያህል ሰዎች አምነው ተጠምቀዋል። ሐዋ. ፪÷፴፩-፴፪

### በበዓለ ሃምሳ ፍጻሜ ያገኙ ትንቢቶችና ተስፋዎች

*ሀ. የነቢያት ትንቢት*

ነቢያት በመንፈስ ቅዱስ መሪነት ከተናገሩት ትንቢት አንዱ ስለ በዓለ ሃምሳ ነው። ለአብነት ያህል በነቢዩ ኢዩኤል የተነገረው ተጠቃሽ ነው። «መንፈሴን በሥጋ ለባሽ ሁሉ ላይ አፈስሳለሁ ወንዶችና ሴቶች ልጆቻችሁም ትንቢትን

> አንድ ልብ መሆን በዚህ መልኩ የሚቀርብ ጸሎት የመንፈስ ቅዱስን ጸጋ እንደሚያ ስገኝ ዛሬም ላለነው ካህናትና ምእመናን የሚያስተምረን የቤተክርስቲያን ታሪክ ነው።

ይናገራሉ። ሽማግሌዎቻችሁም ሕልምን ያልማሉ. . .» ኢዮ.፪÷፳፰ በዚህ ትንቢት መሠረት የመጨረሻው ዘመን የተባለው የኦሪትን መጨረሻ ሲሆን «ወንዶች ሴቶች» ያላቸውም መዩ ሃያውን ቤተሰብ እንደሆን ቅዱስ ጴጥሮስም በዕለቱ በሰበከው ስብከት ተርጉሞታል። ሐዋ. ፪÷፳፰-፴፩ በተጨማሪም ነቢዩ ዳዊት «ዐረገ ውስተ አርያም ጼዊውከ ጼዋ ወወሀብከ ጸጋከ ለእጓለ እመ ሕያው፤ ወደላይ ዐረግህ ምርኮንም ማረክ ስጦታን ለሰዎች ሰጠህ» በማለት የተናገረው። ከዕርገቱ በኋላ መንፈስ ቅዱስን እንደሚልክ የተነበየው ነው። /መዝ. ፷፯÷፲፰/

*ለ. የጌታችን የተስፋ ቃል ተፈጸመ*

መድኃኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስ በማስተማር ዘመኑ እና በዕርገቱ ጊዜ «እነሆ አባቴ የሰጠውን ተስፋ እኔ እልክላችኋለሁ» በማለት ለሐዋርያት የተስፋ ቃል በነገራቸው መሠረት፤ ጊዜው ሲደርስ አጽናኝ ኃይልና ምስጢር ገላጭ መንፈስ ቅዱስን ልኮላቸዋል። /ዮሐ.፲፬÷፳፮፤ ሉቃ. ፳፬÷፵፱፤ ዮሐ. ፲፮÷፲፪/

### ሐዋርያትን ብቁ ያደረጓቸው ነገሮች

ቅዱሳን ሐዋርያት መንፈስ ቅዱስ ወርዶ ምስጢር እንዲገልጽላቸው፣ ኃይልን እንዲጎናጸፉ ያበቃቸው ከእነርሱም የሚጠበቅባቸውን ድርሻ ስለተወጡ ነው። ከእነዚህም ውስጥ፡-

*፩. በእምነትና በትዕግሥት መጠባበቃቸው*

መድኃኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ከተለያየ ተግባር የጠራቸው ሐዋርያት በዋለበት እየዋሉ፣ ባደረበት እያደሩ ከእርሱ ጋር ተመላልሰዋል፣ ተምረዋል። ስለዚህም «ሁሉን ትተን ተከተልንህ» ለማለትም በቅተዋል። ጌታችን ከዕርገቱ በኋላ መንፈስ ቅዱስን እንደሚልክላቸው ቢነግራቸውም መቼ እንደሚፈጸም? ግን አያወቁም ነበር። ቢሆንም ግን እስከመጨረሻው ቃሉን በማመን እና በትዕግስት ጠብቀዋል። ይህም ጸጋ መንፈስ ቅዱስ ማግኘታቸው ምክንያት ሆኗል ። እግዚአብሔር የማያደርገውን አይናገርም፤ የተናገረውንም አያስቀርምና፤ ዛሬም ቢሆን ከሁላችን የሚጠበቀው ቃሉን በእምነትና በትዕግስት መጠበቅ፣ ደጅ መጥናት ነው። ነቢዩ ዳዊት «እግዚአብሔርን ቆይቼ ደጅ ጠናሁት፤ እርሱም ዘንበል አለልኝ» በማለት እንደገለጸው በቃሉ አምኖ ደጅ የጠና ሁሉ የተስፋው ቃል እንደሚፈጸምለት የሚያረጋግጥ ነው። /መዝ. ፴፱÷፩/

*፪. ትእዛዝ በመፈጸማቸው*

ጌታችን መድኃታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ከማረጉ በፊት ከሐዋርያት ስለሚጠበቀው ድርሻ ሲነግራቸው «እናንተ ግን ከላይ ኃይልን እስክትለብሱ ድረስ በኢየሩሳሌም ከተማ ቆዩ» ብሏቸው ነበር። ሉቃ.፳፬÷፵፱ እነርሱም ምንም እንኳን ሰቃልያነ ክርስቶስ አይሁድ ሊያሳድዷቸው ቢፈልጉም ከኢየሩሳሌም ሳይወጡ በማርቆስ እናት ቤት ተሰብስበው ትእዛዙን በመፈጸም ቆዩ በተባሉበት ጸንተዋልና የመንፈስ ቅዱስ ጸጋን አገኙ። «ትእዛዜን ለሚጠብቁ ምሕረት የማደርግ እኔ ነኝ» ተብሎ እንደተጻፈ ምሕረተ ሥጋ ወነፍስ ያገኙ ሁሉ ለትእዛዙ ተገዝተው ነው። /ዘጸ.፳÷፮/ በመሆኑም ለእግዚአብሔር ቃል መታዘዝ ለጽድቅ የሚያበቃ የመንፈስ ቅዱስን ጸጋ የሚያስገኝ መሆኑን በማመን ኢየሩሳሌም በተባለች በቤተ ክርስቲያን ሥርዓት ልንጸና ይገባል። «ትእዛዜን ጠብቁ» የሚለንን ቃልም በተግባር መግለጥ ይጠበቅብናል። /ዘጸ.፲÷፲፩፣ ፳፫÷፩-፲፰፤ ዮሐ. ፲፬÷፲፭/


*፫. የኢየሱስም እናት በዚያ ነበረች*

ቅዱሳን ሐዋርያት ቆዩ በተባሉበት ቦታ ሲቆዩ እመቤታችን ቅድስት ድንግል ማርያምን ይዘው ነው። ሐዋ.፩÷፲፬ ኤልሳቤጥ መንፈስ ቅዱስ የመላባት እመቤታችን

ወደ ገጽ ፲፯ ዞሯል

# ዐሥር ነጥቦች ስለመጽሐፍ ቅዱስ

መ/ር መንግሥተአብ አበጋዝ



*፩. ቅዱስ ነው /ቅዱስ መጽሐፍ ነው/*

በዕብራይስጥ «ክዳሽ» በሱርስት ቃል «ካዲሽ» የሚለው ቃል በዐረቢኛና በግእዝ ቋንቋዎች «ቅዱስ» የሚለውን አቻ ቃል ይተካል:: ትርጓሜውም የተለየ ማለት ነው::

የመጽሐፍ ቅዱስ ቅድስና አስገኚው ቅዱስ እግዚአብሔር በመሆኑ እንዲሁም ስለ ቅዱሱ እግዚአብሔርና ስለ ቅዱሳን ወዳጆቹ የሚናገር በመሆኑ ነው::

መጽሐፍ ቅዱስ የሚያነቡትን የሚቀድስ የሚሰሙትን ወደ ቅድስና የሚመራ መጽሐፍ ነው:: /ሉቃ.፲፩÷፳፰፡ ራእ.፩÷፴፩/ ቅዱሳን ሰዎችም በመንፈስ ቅዱስ ተመርተው ጽፈውታልና ቅዱስ ነው::

*፪. የበረከት መጽሐፍ ነው*

መጻሕፍትን የሚያነብ ሰው ዕውቀትን ይገበያል:: መጽሐፍ ቅዱስን የሚያነብ ሰው ግን በረከትን ይጨምራል:: ይማራል፤ ይገሠጻል፤ ልቡም ይረጋል:: /፪ጢሞ.፫÷፲፯፡ ራእ.፫÷፲፱፡ ምሳ.፳፫÷፲፱/

የመጽሐፍ ቅዱስ በረከት በአጥንት ጠገን ለነፍስም ምግብ ነው:: ስለዚህም ንጉሥ ዳዊት «ለጕሮሮዬ ጣፋጭ ነው» ሲል ነቢዩ ሕዝቅኤልም «ይህን መጽሐፍ ብላ» እያለ ይመክራል፤ የሚበላ የበረከት መጽሐፍ ነውና:: /መዝ.፻፲፰÷፻፫፡ ሕዝ.፫÷፩-፫/ ጌታችን ይህንን ሲያስረግጥ «ሰው በእግዚአብሔር ቃል ሁሉ እንጂ በእን ጀራ ብቻ አይኖርም» ብሏል:: ከጌታው የተማረ ቅዱስ ጴጥሮስ ይህን በረከት «ተንኰል እንደሌለበት ሕጻን... የቃልን ወተት ተመኙ» ይለናል::

የመጽሐፍ ቅዱስ በረከት ከወርቅና ከብር ሀብት ሁሉ የሚልቅ የከበረ ሀብት ነው:: /መዝ.፻፲፰÷፻፳፯/ የመንገዳችን ሁሉ ብርሃን ስለሆነ እንቅፋትን የምናልፍበት የጠላትንም ጦር የምንዋጋበት ኃይላችን ነው:: /መዝ.፻፲፰÷፻፬፡ ኤፌ.፮÷፲፯/

*፫ የቅዱሳት መጻሕፍት ሁሉ ራስ ነው*

ቅዱሳት መጻሕፍት የመጽሐፍ ቅዱስ ልጆች ናቸው:: ለዚህ ነው አዋልድ የምንላቸው:: መጽሐፍ ቅዱስን በይዘት መስለው በመልእክት አህለው ተወልደዋልና::

የአንድ ሰው ልጆች ወላጆቻቸውን በመልክ መስለው በጠባይ አህለው እንዲወለዱ መጽሐፍ ቅዱስ እናትም አባትም ሆኖ በብዙ ሚሊዮን የሚቆጠሩ መጻሕፍትን የወለደ ወላድ መጽሐፍ ነው::

*፬. የትምህርተ ሃይማኖታችን መሠረት ነው::*

ቤተ ክርስቲያናችን እምነቷ፣ ሥርዓቷና ትውፊቷ የተመሠረተው በመጽሐፍ ቅዱስ ላይ ነው:: በዚህ ምክንያት ያለ መጽሐፍ ቅዱስ የሚፈጸም ሥርዓተ ጸሎት የለንም:: ለአንድ ምእመን ከልደት እስከ ዕረፍት ያለመታከት መጽሐፍ ቅዱስን የምታነብ ቤተ ክርስቲያን አለችን::

ክርስትናው እለት አንሥቶ ለቅዳሴ ሲመጣ፣ ማኅሌት ሲቆም፣ ኪዳን ሲያደርስ፣ በተክሊል ሲያገባ፣ ዐርፎ /ሞቶ/ እስኪፈታ ድረስ ከመጽሐፍ ቅዱስ የተለየ ሕይ ወት የለውም::

ሃይማኖታችንን የምንማረው፣ የምናስረዳበትና የምናስረግጥበት መጽሐፍ በመሆኑ፤ መጽሐፍ ቅዱስ የትምህርተ ሃይማኖታችን መሠረት ነው::

*፭. ለጅማሬውም ለፍጻሜውም ወሰን የለውም*

መጽሐፍ ቅዱስ ትላንት የሆነውን ዛሬ እየሆነ ያለውንና ነገ የሚሆነውን በእርግጠኝነት የሚናገር ነው:: ይኸውም ዓለም ከመፈጠሩ በፊት፣ ከተፈጠረ በኋላና ዓለም ሲያልፍ ስለሚሆነው ነገር የሚናገር ለይዘቱ ወሰን የሌለው መጽሐፍ ቅዱስ ብቻ ነው:: ሌሎች መጻሕፍት ልብወለዶች፣ መላምቶች ወይም ታሪክ ብቻ ናቸው::

የኦሪት መጻሕፍትን የጻፈው ሊቀ ነቢያት ሙሴ ነው:: ነቢዩ ከሦስት ሺሕ ዓመተ ዓለም በኋላ ስለ ሥነ ፍጥረት ሲጽፍ «እግዚአብሔር በመ ጀመሪያ ሰማይንና ምድርን ፈጠረ::» «ፈጠረ» አለ እንጂ በጥርጣሬ /በግምት/ ቃላት «ሳይፈጥር አይቀርም» «ፈጥሮ ይሆናል» ወዘተ አላለም:: /ዘፍ.፩÷፩/

**መጻሕፍትንና የእግዚአብሔርን ኃይል አታውቁምና ትስታላችሁ**

/ማቴ.፳፪÷፲፱/



www.eotcmk.org

ነቢዩ ዳዊት ወደፊት ስለሚሆነው የጌታችን ምጽአት /መምጣት/ በእርግጠኝነት «እግዚአብሔር ግልጥ ሆኖ ይመጣል» በማለት ግልጽ ትንቢት ተናግሯል፡፡ /መዝ.፵፰÷፪/ ከሙታን ትንሣኤ በኋላም ስላለው ዘላለማዊ ሕይወት በእርግጠኝነት የሚናገር መጽሐፍ በመሆኑ ለጅማሬውም ለፍጻሜውም ወሰን የሌለው መጽሐፍ ነው፡፡

*፮. ሲነበብ የኖረ የማያልቅ መጽሐፍ ነው*

መጽሐፍ ቅዱስ ከተጻፈበት ፴፻፲፭ ዓ.ም ጀምሮ ሲነበብ የኖረ የማያልፍ መጽሐፍ ነው፡፡ «ዕለት ዕለት አዲስ ነው» «አያልፍም» «ለዘላለም ይኖራል» /ማቴ.፳፬÷፴፭፣ ፩ጴጥ.፩÷፳፭/ ከሌሎች መጻሕፍት በተሻለ መልኩ ማየት ለተሳናቸው በብሬል፣ ማንበብ ለማይችሉ በድምፅ የተዘጋጀ እና ለብዙዎች በብዙ ቋንቋ የደረሰ መጽሐፍ ይሁን እንጂ ብዙ ትውልድ አንብቦ አልጨረሰውም፡፡ /ኢሳ.፵÷፰/ እስከ አሁን መጽሐፍ ቅዱስ ከ፳፻ በሚበልጡ የዓለማችን ቋንቋዎች እና በረቀቁ የቴክኖሎጂ ጥበባት የተሠራጨ መጽሐፍ ነው፡፡

*፯. በተለያየ ዘመን፣ ቋንቋና ቦታ በተለያዩ ሰዎች የተጻፈ አንድ መጽሐፍ ነው፡፡*

መጽሐፍ ቅድስ ከ፴፻፲፭ ዓ.ዓለም እስከ ፻ ዓ.ም ድረስ ከአርባ በላይ በሚሆኑ ቅዱሳን ሰዎች ተጽፏል፡፡ ብሉይ ኪዳን በዕብራይስጥ ሲጻፍ ሐዲስ ኪዳን በግሪክ /በጽርዕ/ ቋንቋ ተጽፏል፡፡

የመጽሐፍ ቅዱስ ጸሐፊዎች በተለያዩ ዘመን የነበሩ ሰዎች ብቻ ሳይሆኑ ከልዩ ልዩ ማኅበራዊ ሕይወትም የተጠሩ ቅዱሳን ነበሩ፡፡ ከእረኝነት፣ ከግብርና፣ ከክህነት፣ ከንግሥና፣ ከነቢይነት … ተጠርተዋል፡፡ በልዩ ልዩ ሁኔታዎችና ሥፍራዎች ውስጥም ሆነው ጽፈዋል፡፡ ሙሴ በሲና ምድረ በዳ ሲጽፍ ዮሐንስ ራእዩን በፍጥሞ ደሴት ጽፏል፡፡ ሌሎች በርካታ መጻሕፍት በኢየሩሳሌም እና በምርኮ ዘመን በባቢሎን ተጽፈዋል፡፡

በልዩ ሁኔታ ውስጥ የተዘጋጁ አስደናቂ መጻሕፍትም አሉት፡፡ ለምሳሌ የትንቢተ ዮናስ ሁለተኛው ምዕራፍና የነቢዩ የዮናስ ጸሎት በዓሣ አንበሪ ሆድ ውስጥ የቀረበ ልመና ሲሆን፤ ጸሎተ ሠለስቱ ደቂቅ /መዝሙረ ሠለስቱ ደቂቅ/ ደግሞ በእሳት ውስጥ ሳሉ የዘመሩት መዝሙር ነው፡፡

መጽሐፍ ቅዱስ በተለያየ ዘመን፣ ቋንቋና ቦታ እንዲሁም በተለያዩ ሰዎች ይጻፍ እንጂ ቅዱሳን ሰዎች በመንፈስ ቅዱስ ተመርተው የጻፉት አንድ መጽሐፍ ነውና እርስ በርሱ አይጋጭም፡፡



## መጽሐፍ

* ያንብቡት -
ምግብ ነውና ይጠግቡበታል
* ይማሩት -
ምክር ነውና ይገሠጹበታል
ይመኙት -
ወተት ነውና ያሳድጎታል
* ያብሩት -
ብርሃን ነውና ያበራሎታል
* ያጥኑት-
ጥበብ ነውና ይጠበቡበታል
* ይመሩበት-
ቅዱስ ነውና ይቀድሶታል

## ቅዱስ

* ይመገቡት -
በእንጀራ ብቻ አይኖሩምና
* ይታጠቁት -
ሰይፍ ነውና ይቆርጡ በታል
* ይያዙት -
ጋሻ ነውና ይመክቱበታል
* ይኑሩት -
ሕይወት ነውና ይጸድቁበታል
* ይሰበኩት -
አዋጭ ነውና ያተርፉበታል

*፰. እውነተኛ መጽሐፍ ነው*

በመጽሐፍ ቅዱስ አድሎአዊነት የለም፡፡ የንጉሥ ዳዊትን ታሪክ ስናነብ ዳዊት ሲበድልም ጽድቅን ሲፈጽምም እናገኛለን፡፡ በተመነ ሳይም የጴጥሮስ ታሪክ ውስጥ «አንተ ክርስቶስ የሕያው የእግዚአብሔር ልጅ ነህ» በማለት መስክሮ «አንተ ዐለት ነህ» ሲባል ባነበብንበት መጽሐፍ ውስጥ «አላ ውቀውም» ብሎ ጌታውን ሲክድና ደግሞ ተጸጽቶ ሲመለስ እናነባለን፡፡ መጽሐፍ ቅዱስ የእውነት መጽሐፍ የመሆኑ ምስክር ይህ ብቻ አይደለም፡፡ እውነተኛውን የሰው ዘር ታሪክ አመጣጥ፣ እውነተኛውን አምላክና እውነተኛውንም እምነት የሚመሰክር እውነተኛ መጽሐፍ ነው፡፡ /ዮሐ.፲÷፩-፲፰/

*፱. የራሱ መልክአ ምድርና ባሕል አለው*

መጽሐፍ ቅዱስን የሚያነብ /የሚያጠና/ ሰው የመጽሐፍ ቅዱስን መልክአ ምድር ማወቅ ይጠበቅበታል፡፡ የመጽሐፍ ቅዱስን መልክአ ምድር ሳያጠኑ መጽሐፍ ቅዱስ ማንበብ የሚሄዱበትን ሳያውቁ ታክሲ መሳፈር ነው የሚባለው ለዚህ ነው፡፡

በርካቶቹ የመጽሐፍ ቅዱስ ድርጊቶች በእስራኤል መልክአ ምድርና ባሕል የተፈጸሙ ናቸው፡፡ ስለዚህ ቢያንስ አንድ የመጽሐፍ ቅድስ አንባቢ በመጽሐፍ ቅዱስ የተጠቀሱ ዋና ዋና ከተሞችን ለምሳሌ ኢየሩሳሌምና ፍልስጥኤምን ለይቶ ማወቅ አለበት፡፡

መጽሐፍ ቅዱስ በእስራኤል ባህል ወግና ልማድ የተ ጻፈ እንደ መሆኑ በጥቂቱም ቢሆን አስፈላጊ የሆኑትን የእ ስራኤል ባሕል መረዳት አለበት፡፡ ለምሳሌ ደጊመ ቃላትን፣ ዝምድና፣ እረኝነት … ያሳቸውን ትርጉም ጠንቅቆ ማወቅ ይጠቅማል፡፡ /አስፈላጊ ነው/

*፲. የጥበባት ሁሉ መገኛ ነው*

መጽሐፍ ቅዱስ የብዙ ዓይነት ጥበባት መገኛ ነው፡፡ የአስተዳደር፣ የታሪክ፣ የፍልስፍና /ምርምር/፣ የሕክምና፣ የሥነ ሕንጻ፣ የሥነ ጽሑፍ፣ የግብርናና… የሌሎችም የበርካታ ጥበባት መገኛ ምንጭ ነው፡፡

ብዙዎች መጽሐፍ ቅዱስን የሃይማኖት መንገሪያ /መማሪያ/ መጽሐፍ ብቻ አድርገው ቢያስቡትም መጽሐፍ ቅዱስ የጥበባትም ሁሉ መገኛ ነው፡፡ በእርግጥም ቅዱስ መጽሐፍ ነው፡፡✤

*ዋቢ መጻሕፍት*

ዓባይነት ካሤ /ዲያቆን/፣ ፲፱፻፺፬ ዓ.ም፣ የመጽሐፍ ቅዱስ ጥናት በኦርቶዶክስ ተዋሕዶ፡፡ ማኅበረ ቅዱሳን፣ ብራና ማተሚያ ድርጅት፣ አዲስ አበባ፡፡





www.eotcmk.org

# ስለ ስብከቶቻችን እንወያይ

## የማያነብ ሰባኪ

ለሐመር መጽሔት አዘጋጆች መንፈሳዊ ሰላምታዬ ይድረሳችሁ። በስብከትና በሰባክያን ዙሪያ ያሉ ችግሮችን ለመቅረፍ የውይይት መድረክ በመክፈታችሁ የተሰማኝ መንፈሳዊ ደስታ ከፍተኛ ነው። እኔም እንደ አቅሜ የታዘብኩትን በስብከትና በሰባክያን ያሉ ክፍተቶችን ልጠቁም፡-

ስብከት፡- ከጊዜ ወደ ጊዜ እየተጠናከረና በርካታ ምእመናን በንስሐ ሕይወት እንዲመለሱ በምግባረ ሃይማኖት እንዲፀኑ አሕዛቡም፣ መናፍቁም ወደ ክርስትና እንዲመለሱ ከፍተኛ አገልግሎት እየተሰጠ ይገኛል። በተለያዩ መምህራን የሚዘጋጁ ስብከቶች በተለያዩ የቴክኖሎጂ ውጤቶች እየተዘጋጁ በቀላሉ ወደ እያንዳንዱ ቤት ሰተት ብለው እየገቡ ይገኛሉ። ትልቁ ችግር ግን በከተማ ተወስኖ ሰፊ ሕዝብ ወደ አለው የገጠር ክፍል በበቂ ሁኔታ አለመሠራጨቱ ነው።

ሰባክያን፡- ከእግዚአብሔር ክብር ይልቅ የራስን ጥቅም ማስደቀም፣ አገልግሎቱን ገንዘብ ተኮር ማድረግ፤ ለሥጋ ምቾት ወደ ከተማ እንጂ ወደ ገጠር ያለመውጣት፣ የተሰባኪ ሕዝብ ቁጥር ካልበዛ ደስተኛ አለመሆንና ያለመስበክ ቁልፍ ችግሮች አሉባቸው። ለአንባቢያን ግልጽ እንዲሆን መጠነኛ ትንታኔ ልስጥ።

፩. እግዚአብሔር ፍቅር መሆኑን ከማስተማር ይልቅ «ሊቀስፍህ ነው፤ ሊቆርጥህ ነው»፣ በሚል ዛቻ፣ በኃይለቃል ብቻ የተሞላ አነጋገር በመጠቀም የምእመናንን ልብ ከማነፅ ይልቅ ማሸፈትና ተስፋ ማስቆረጥ፤

፪. «እልል በሉ፤ አጨብጭቡ» በማለት ሰማእያንን ማጨናነቅ፤ አንድ ወቅት «እልል በሉ ካልሆነ ሌላ ጊዜ አልመጣም» እያለ አንዱ ሰባኪ ሲናገር በአጠገቤ የነበሩ አንድ ምእመን «አድርገኸው ነው» ያሉትን አልረሳውም። ሌላው ነጥብ ከሚያስተምሩት ርእሰ ነገር ለማጣፈጫ የሚያቀርቡትን ተረት የሚያበዙ፣ እንዲሁም የትምህርቱ ርእስና የሚያስተምሩት የማይገናኝላቸው፣ ከርእስ ወጥተው ሳይመለሱ በዚያው የሚቀሩ ብዙዎች ናቸው። የትምህርቱን መቋጫ አጥተው አሜን ካስባሉ በኋላ «አሁን ጠቀለለው» ሲባሉ ሌላ ርእስ የሚጀምሩ ሰባኪያን ቁጥር ቀላል አይደለም።

፫. ድምፃቸው የማይሰማ ከአትሮንሱ ጋር የሚነጋገሩ የሚመስሉ፤ ምእመናን ላይ እንቅልፍ የሚለቁ፣ አንድ በአንድ እየተነሣ ግማሽ ሕዝብ እስኪቀር የማያስተውሉ ሰባኪዎች አሉ። ድምፃቸው የገደል ማሚቱ የሆነ፣ መልእክቱ ምን እንደሆነ የማይጨበጥ፣ ግለ ታሪካቸውን የሚያወሩ ብዙዎች ናቸው። እዚህ ላይ አንድ ጓደኛዬ ያጫወተኝን ላስታውሳችሁ፡- ሰባኪው መድረክ ላይ ወጣና ማይክ ጨብጦ «... የደሴ ሕዝብ ልዩ ነው። ትናንት ኮረም ነበርኩ፣ አቤት ሕዝቡ ትምህርት ሲወድ፤ ነፍስ ነው፤ የሠቆጣውንማ ተዉት፤ በነቂስ ነው የሚወጣው፤ የአላማጣ የአዲስ አበባን ሕዝብ ነው የሚመስለው...» እያለ ሲቀባጥር ትዕግስቱ ያለቀበት ምእመን «ስማ ወንጌሉ እንደዚያ ይላል» ብሎ ከምእመናን ፊት ገሠፀው።

፬. «ባለፈው እንደተማርነው»... ይላል ግን እኮ አላስተማረም። አንድ ርእሰ ነገር ያነሣና ሳይቋጨው «እንመለስበታል» ይላል፤ እስከ ምፅዓት ላይመለስ። ለሰዎች መልክአ ውዳሴ በማነብነብ ጊዜ የሚያባክን ሰባኪም አለ።

፭. እጅግ የሚገርመኝ ደግሞ የማያነብ ሰባኪ መኖሩ ነው። በየሔደበት ደብር አንድ ጊዜ የያዛትን በአንድ ቦታ ያስተማራትን ርእስ እየደጋገመ የሚኖር። ሕፃናት ብቻ ባሉበት «በጉብዝናህ ወራት ፈጣሪህን አስብ» ሽማግሌዎች ባሉበትም ጉባኤ «በጉብዝናህ ወራት...» እያለ የሚሰብክ። ሌላ ርእስ እንዳይቀይር አላነበበም። አንድ ወቅት ከአዲስ አበባ የመጣ ሰባኪ «ወደ እግዚአብሔር ቤት እንሂድ ባሉኝ ጊዜ ደስ አለኝ»። ብሎ አስተምሯል። ልቡ የተነካው ሌላኛው ሰባኪ ደግሞ በሌላ ጊዜ መድረክ ላይ ወጥቶ እየሰበከ «ሰማችሁ እኛ እዚህ ሆነን ቤተ ክርስቲያን አንሔድም። ከአዲስ አበባ የመጣ ወንድማችን ግን ወደ ቤተ እግዚአብሔር እንሂድ ሲሉኝ ደስ አለኝ አለ፤ አይገርማችሁም» ይላል። የቅዱስ ዳዊት ቃል መሆኑን ማን ይንገረው! እሱ እንደሆነ ማንበብ ሲያልፍም አይነካውም፤ የማያነብ ሰባኪ ደግሞ ጎደሎ እንሥራ ነው።

> ቤተ ክርስቲያን የአርምሞ ቦታ በመሆኗ እንኳን ጮኾ መሳቅ ጮኾ መነጋገርም የሚገባባት ቦታ አይደለችም። ... ውብ የቤተ ክርስቲያናችን የአሰባበክ ለዛ፣ ዛሬ በዘመናዊነት ስም ውኃ ሲቸለስበት እየተመለከትን ነው። የክርስቶስ መንግሥት የሚሰበክበት ዐውደ ምሕረት፣ የመሳቂያ ቦታ፣ የዓለም ትርኢ ምርኢ መነጋገሪያ ቦታ ሲሆን ማየት ለምን አያሳዝን?

ሌላው ቁልፍ ችግር ሰባኪ የሚናገረውን ሆኖ አለመገኘቱ ነው። ጾሙ እያለ በጥዋቱ ይበላል። ቁረቡ ይበል እንጂ ኪዳን አድ ርሶ አስቀድሶ የማያውቅ አለ። ሳያገባ አግቡ የሚል ሰባኪም አለ። ተፋቀሩ እያለ ቂም የሚይዝ አለ። የሰባኪያን ችግር ብዙ ነው። ከብዙ በጥቂቱ ለዛሬ ይህንን ካልኩ በሌላ ጊዜ እስክንገናኝ ደህና ሁኑ። ስብከቶቻችን ለማሳደግ ችግሮ ቻችን ለመቅረፍ። ያብቃን።✥

*ረድኤተ እግዚአብሔር አይለየን።*

*ገ/መድኅን አያሌው ከማይጨው*







www.eotcmk.org

## ሁሉ በአግባብና በሥርዓት ይሁን

በሐመር ተከታታይ እትሞች ስለ መዝሙሮቻችን እንወያይ የሚለው ርእስ ጉዳይ ጥሩ ትምህርት አግኝተንበታል። አሁንም ስለ ስብከቶቻችን መወያየት ወቅታዊ ብቻ ሳይሆን በጣም አስፈላጊ በመሆኑ፤ እንድንወያይበትና እንድንማማርበት መደረጉ ተገቢ ነው።

ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን ከሌሎች የሚለያት ትምህርተ ሃይማኖቷ ብቻ ሳይሆን መዝሙሯ፣ ስብከቷ፣ የንግግር፣ የአለባበስ ሥርዓቷና እምነቷም ጭምር ነው።

በዚህች ቤተ ክርስቲያን የጸኑ የቀድሞ አባቶቻችንና እናቶቻችን በሰውነታቸው ባደረች፣ በልቡናቸው በነደደች በኅሊናቸው በተቃጠለች የክርስቶስ ፍቅር በቤተ ክርስቲያን ውስጥ እንደ ብረት ችንካር ተተክለው ለዶግማዋና ለሥርዓቷ ታማኝ በመሆን ዘብ ቆመው፣ ከሐዋርያት ጀምሮ ሲወርድ ሲዋረድ በቅብብል የደረሳቸውን የቤተ ክርስቲያን ሥርዓትና ሃይማኖት ሳይበረዝና ሳይቀየጥ ለዘመናችን አድርሰዋል። ዛሬ ዐረፍተ ዘመን ገትቷቸው ቢለዩንም፤ ባለውለታነታቸውን ግን አንዘነጋውም። በዚህች የቅዱሳን መኖሪያና የአገልግሎት ሥፍራ በሆነች ቅድስት ቤተ ክርስቲያን የተተካን የዛሬ አገልጋዮችም፤ ይህንን የቤተ ክርስቲያን አንጡራ ሀብት ልንጠብቀውና ልንከባከበው ይገባል። አለበለዚያም በአንድ ወቅት ብፁዕ አቡነ ጎርጎርዮስ ካልዕ እንዳሉት ይህንን ከቀበርን በኋላ ሃይማኖታችንን ፍለጋ ወደ ቤተ መዘክር እንዳንሔድ ያስፈራል።

ይህንን እንድል ያስደፈረኝ በዘመናችን እንደ ሰደድ እሳት እየተዛመተ ያለው የስብከት ዘዬ ነው። በየከተማውና በየደብሩ የሚካሔዱት ጉባኤዎች አዎንታዊ ጎን ቢኖራቸውም፤ በተለይ በአንዳንድ «ሰባኪዎች» የሚነገሩት ቃላት ለጆሮ የሚቀፉ፣ ክርስቲያናዊ ለዛ የሌላቸው፣ ምእመኑን ለንስሐ የማያበቁ እንዲያው ለሳቅና ስላቅ የሚያቀርቡ በመሆናቸው ብዙዎቻችንን አሳዝኖናል። ቤተ ክርስቲያን የአርምሞ ቦታ በመሆኗ እንኳን ጮኾ መሳቅ ይቅርና ጮኾ መነጋገርም የሚገባባት ቦታ አይደለችም። በአንዴ ስብከት ሰዎችን ለንስሐ የሚያበቃ፣ አንዴ ሰምተነው ምንጊዜም ከአእምሮአችን የማይጠፋውና የማይጠገበው ውብ የቤተ ክርስቲያናችን የአሰባበክ ለዛ፣ ዛሬ በዘመናዊነት ስም ውኃ ሲቸለስበት እየተመለከትን ነው። የክርስቶስ መንግሥት የሚሰበክበት ዐውደ ምሕረት፤ የመሳቂያ ቦታ፤ የዓለም ትርኪ ምርኪ መነጋገሪያ ቦታ ሲሆን ማየት ለምን አያሳዝን?

በተለይ በየክፍላተ ሀገሩ የሚሔዱ ሰባኪዎቻችን ለሁለትና ሦስት ቀናት እንኳን ሔደው የሚያሳዩት ሥነ ምግባር የሚናገሩት ቃላት፣ የሚያመሹበት ቦታ ሲታይ፤ በጠቅላላው ከክርስትና በተፈታ ሕይወታቸው የየዋህ ምእመናንን ልብ እየከፈሉ ነው። ዛሬ ድምፁ ያማረ ሁሉ ዘማሪ፣ አንደበት ያለው ሁሉ ሰባኪ የሆነበት ጊዜ ይመስላል። ሰባኪ ዘማሪ ለመሆን የእነቅዱስ ጳውሎስን፣ የእነ ቅዱስ ያሬድን ዜና ሕይወት ማወቅ ብቻ ሳይሆን እነሱን መስሎ መገኘትም እንደሚያስፈልግ የተዘነጋ ይመስላል።

ለነገሩማ የአንዳንድ «ሰባኪዎቻችን» የአሰባበክና የአነጋገር እንዲሁም የስብከት ርእስ አመራረጥና አብነታቸው የቤተ ክርስቲያናችን ሊቃውንት ሳይሆኑ፤ የመናፍቃን ፓስተሮች ለመሆናቸው ከራሳቸው «ከመምህራኖቻችን» እና ከጓደኞቻቸው መስማት ከጀመርን ሰነበትን። ይህ የሆነበት ምክንያትም በየጉባኤ ቤቶቻችን ሔዶ ለመማር የሚጠይቀውን ውጣ ውረድ መክፈል ከብዷቸው ይሆንን? በአቅራቢያቸው ከሚገኙ መናፍቃን ጉባኤ የሚያውሳቸው ወይንስ ሌላ ነገር አላቸው? አንድ ሰባኪ ልመንፈሳዊ ሕይወቱ ጥንካሬና እድገት መጨነቅ ሲገባው አንዳንድ ሰባኪዎቻችን ግን ፀጉራቸውን ፈትለው /ፈርዘው/፣ ለዘመን አመጣሽ አኗኗር ብልፅግና እየተሯሯጡ ሲኖሩ ማየት በአንደበታቸው ከሚያስተምሩት ይልቅ በሕይወታቸው የሚያበላሹት የሚበዛ ይመስለኛል።

ዛሬ ዛሬ «ሰባኪዎቻችን» ለጉባኤ ሲጠሩ የሚያሳስባቸው የምእመናንን ልብ ሰብሮ ለንስሐ ማዘጋጀቱ ሳይሆን፤ የእራሳቸውን ተደናቂነት አጉልቶ ለመምጣት ይመስላል። የሚገርመው ደግሞ የየጉባኤ አዘጋጆቻችን መምህራኖቹን መምረጥ ሲገባቸው የዚህ ጥፋት ተባባሪ መሆናቸው ነው።

በትሕትና፣ በተዘክሮተ እግዚአብሔርና በፍርሃት በምንወልበት ዐውደ ምሕረት ቀልድና እንቶ ፈንቶ በማብዛት፣ ሕዝቡን ድፍረት በማስተማር ዐውደ ምሕረቱን የቴአተር አዳራሽ የሚያስመስሉትን ማስመጣቱ ትርፉ ምኑ ላይ ነው?

አስተባባሪዎችም ጉባኤ ከማዘጋጀታቸው በፊት አጥብቀው ሊያስቡበት የሚገባው የሚጋበዙ ዘማሪዎችና መምህራን ጉዳይ መሆን አለበት።

**በጣም ስለጮኹ ድንቅ ሰባኪ የሆኑ የሚመስላቸውም አሉ።**

በቅርብ የማውቀውን ትዝታ ላካፍላችሁ አንዴ በአንድ ከተማ በተዘጋጀ ጉባኤ ላይ የተጠሩ ሰባኪዎችና መዘምራን ወደተጋበዙበት ቦታ በጊዜ ገቡ። የእንኳን በሰላም ደረሳችሁ አቀባበል ከተደረገላቸውና ራት ከበሉ በኋላ ወደተዘጋጀላቸው ማረፊያ ለማድረስ ቢፈለጉ ጠፉ። በዚህ የተደናገጡት ኮሚቴዎች ሲፈልጓቸው ከሰዓታት ፍለጋ በኋላ ከDSTV ቤት ሲወጡ አገኟቸው።

«ሰባኪዎቻችን» መድረክ ላይ ወጥተው ተገቢውን ቃለ እግዚአብሔር አስተምረው ምእመናን በተረጋጋ መንፈስ እንዲሰሟቸው ከማድረግ ይልቅ፤ ተነሡ፣ ቁጭ በሉ፤ እጃችሁን አውጡ፤ ከእኔ ጋር አብራችሁ ይህንን በሉ፤ እያሉ በየደቂቃው ምእመናንን በጥያቄ ማሰላቸት የቤተ ክርስቲያን ሥርዓት አይደለም።

አንድ ጊዜ በአንድ ቦታ በተደረገ ጉባኤ ላይ «ሰባኪው» የተለያዩ ጥያቄዎችን እያነሣ ሕዝቡን በማሰላቸቱ ሕዝቡ ዝምታን ሲመርጥ «ሰባኪው» ሲመልስ «በመጨረሻው ሰዓት እንደ ዚዳን እንዳታሳስቱኝ» አለ። ስንቶቹ እናቶችና አባቶች ዚዳንን ያውቁ ይሆን? ደግሞስ እንደዚህ ዓይነቱ ነገር ለሳቅ በሚገባ ቦታ ላይ ቢቀርብ ምናለ?

ነጣላ አጣጥለው፣ ዐውደ ምሕረት የተሰበሰቡ ምእመናንን «እጆቻችሁን ከአፋችሁ ላይ አንሡ! ለማሽሟጠጥ፣ ቡና ለመጠጣት አይደለም የተጠራችሁት» እያለ ምእመናንን የሚያስደነብር «መምህር» ተብዬን፤ ጉባኤ አዘጋጆች መምከር መገሠጽም ይጠበቅባቸዋል። ለሚያስተምራቸው ነፍሳት የማይጨነቅ፣ የማያከብር የተዋሕዶ መምህር ሊሆን አይገባውምና። ሁሉ በአግባቡና በሥርዓት ይሁን።✤

*ዮሴፍ ታምራት*
*ዘጨፋሮቢት*



www.eotcmk.org

## ዝና ፈላጊዎች

ከዚህ ቀደም በቀረበው የመዝሙር ውይይት ብዙ ጠለቅ ያሉ ቁምነገሮችን ለማግኘት ችያለሁ:: ለውይይት ባቀረባችሁት «ስብከት» ላይ የታዘብኩትን በጥቂቱ ለመግለጽ እሞክራለሁ::

ስብከት ማለት የእግዚአብሔርን እውነት በሚገባ ቋንቋ፣ በሥርዓት ሰውን ከፈጣሪ ጋር ማስታረቅ ነው:: ለዚህ አገልግሎት የተመደበ ደግሞ ሰባኪ ይባላል:: «ከእግዚአብሔር ጋር ታረቁ ብለን ስለ ክርስቶስ እንለምናለን» እንዲል:: /፪ቆሮ. ፭፥፳/ ይህም አገልግሎት የጸጋ ስጦታን ከእግዚአብሔር የሚሻ መሆኑ ቅዱሳት መጻሕፍት ይመሰክራሉ::

በዐውደ ምሕረትም ሆነ በመቅረጸ ድምፅና ምስል የሚቀርቡት ስብከቶች ሁሉንም ሰባኪ ባይመለከትም በብዙዎች የሚከተሉት ስሕተቶች ይታይባቸዋል::

### ፩. ለገንዘብ ብሎ መስበክ


ዛሬ ብዙዎች የእግዚአብሔርን ቃል መሸጥ ጀምረዋል:: ለእ ነዚህ ሰዎች እውቀቱ የተሰጣቸው ያለምንም ክፍያ እንደሆነ ይታወቃል:: ሁላችንም ያለ ዋጋ ተቀብለናልና «ያለ ዋጋ ተቀብላችሁ ያለ ዋጋ ስጡ» /ማቴ.፲፥፰/ በማለት ጌታችን ያስተማረው ቃል ሲጣስ ቅጣትን ያመጣል:: ይህ ማለት ግን አገልጋዮች ምንም ገንዘብ አያስፈልጋቸውም ማለት አይደለም:: «የሚያበራየውን በሬ አፉን አትሰር» ይላልና:: /፩ቆሮ.፱፥፫/ ተቃውሞዬ ከልክ በላይ መጠየቅን ነው::

ስለገንዘብ ብሎ መስበክ እጅግ በጣም አሳፋሪና የእግዚአብሔርን ጸጋ ለሚጠፉ ነገር መለወጥ ነው:: ገንዘብን መውደድ ደግሞ የኃጢአት ሁሉ ሥር ነው:: /፩ጢሞ. ፮፥፲/ ስለዚህ በሰባክያን ሕይወት ውስጥ ቅናትና ከንቱ ውድድርን ያስከትላል::

ሰባኪ ሰዎችን እንጂ ያላቸውን መፈለግ የለበትም:: ለምሳሌም ቅዱስ ጳውሎስ «እናንተን እንጂ ያላችሁን አልፈልግም» በማለት ተናግሮአል:: /፩ቆሮ.፲፪፥፲፬/ እርሱ ከእነሱ ገንዘብ እንዳይቀበልም ድንኳን በመስፋት ይተዳደር እንደነበር ከሁላችን የተሰወረ አይደለም:: እንዲህ ብሎም አላቆመም፤ በዚሁ ምዕራፍ ፲፪ ወረድ ብሎም «እኔ ግን ስለነፍሳችሁ በብዙ ደስታ ገንዘቤን እከፍላለሁ፤ ራሴን እንኳን እከፍላለሁ» ያለው ሕይወቱ ምንኛ ድንቅ ነው!

### ፪. የቤተ ክርስቲያን ሊቃውንት ንና አባቶችን ማቃለል

ከቅርብ ጊዜ ወዲህ «ባህታዊ» ነን ከሚሉት ሰዎች ጀምሮ «ሰባኪ» ነን ብለው እራሳቸውን ከሚጣሩም መካከል አንዳንድ ሊቃውንተ ቤተ ክርስቲያንን ማቃለልና መሳደብን ተያይዘውታል::




እዚህ ላይ ምን አልባት እነርሱ ከእግዚአብሔር ቃል በላይ ናቸው ወይ? መወቀስ አይገባቸውም? የሚል ጥያቄ ሊነሣ ይችላል:: በርግጥ አይደሉም፤ ነገር ግን እኔም ጥያቄ ላንሣ ስለ አባቶች በደል /ኃጢአት/ ለምእመናን ማውራት ምን ይጠቅማል? የግለሰቦችን ስምስ እያነሡ መኮነን የሚችል ማን ነው?

እኔ በተለይ ሊቃውንተ ቤተ ክርስቲያንንና ካህናት አባቶችን በሚያቃልሉ ሰባኪዎች ላይ ጥርጣሬ አለኝ:: ሕዝቡን ከአባቶቹ ለይቶ የራስ ተከታይ ማድረግና ከንስሓ የራቀውን ሕዝብ የበለጠ እንዲርቅ ማድረግ ይመስለኛል::

### ፫. የእግዚአብሔርን ቃል በትክክል አለመተርጎም

ለምሳሌ ያህል፡- የሰናፍጭ ቅንጣት ታክል እምነት ቢኖራችሁ» የሚለውን ቃል ትንሽ /ጥቂት/ እምነት ቢኖራቸው በማለት የተረጎመ ሰባኪ ገጥሞኛል:: እኔ ደግሞ የተማርኩት ሰናፍጭ ፍፅምት ናት፤ ስለዚህ ፍፁም እምነት ቢኖራችሁ ማለቱ ነው ተብዬ ነው:: ስለዚህ ከእንዲህ ዓይነቱ ስሕተት መታረም ይገባል:: በተለይ ትንቢቶችን ማንም በገዛ ራሱ ሊተረጉም አልተፈቀደለትምና:: /፪ጴጥ. ፩፥፳-፳፩/

### ፬. የማይመሳሰሉ ነገሮች ማቅረብ

እንዲህ ዓይነቱ ረብ ስብከት መስሎ በማይረባ የዓለም ተረት ሰዎችን ለማሳቅ ተብሎ የሚቀርብ መሆኑን ለመረዳት ችያለሁ::

አንድ ምሳሌ ላንሣ ሰባኪው ስለ አንዲት እናት ስእለት ተስላ እንደነበር ተናገረ:: «ስእለቱም ከቤተ ክርስቲያን አጥር በር እስከ ዐውደ ምሕረት ድረስ እንደሕፃን መዳህን ነበር:: ከዚያም ልመናው ሲደርስላት ለመዳህ አቃታት ሐሞቷ ፈሰሰ:: «ከዚያም ሰዎች ተሰብስበው ሆ እያሉ ሲያጨበጭቡላት ሔደች» አለና ይህን ሲያነጻጽር «ሌባ ሰርቆ ከተያዘ በኋላ ካልተጨበጨበልኝ አልሔድም እንደሚለው ነው» አለ:: በእውነቱ በጣም ያሳዝናል ምክንያቱም

፩ኛ. የሴትዮዋና የሌባው ጉዳይ አለመገናኘቱና

፪ኛ. ካልተጨበጨበልኝ፤ አልሔድም የሚል የትኛው ሌባ ይሆን? ብዬ እራሴን ጠየቅሁ::

### ፭. ብዙ ሕዝብ ከሌለ አንሰብክም ማለት

በአንዳንድ ዓውደ ምሕረቶች መርሐ ግብር የሚመሩ አባቶችና ወንደሞች «አስተማሪዎቻችን ብዙ ካልሆናችሁ አንመጣም ስለሚሉ ሰብሰብ በሉ» በማለት በድምፅ ማጉያ ሲናገሩ ስሰማ ያሳፍረኛል::

ለስም አጠራሩ ምስጋና ይግባውና ጌታችን መድኃኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስ «በሰማሪያ ሊያልፍ ግድ ሆነበት» ይላል:: /ዮሐ.፬፥፭/ የሚያድናት አንዲት





www.eotcmk.org

ነፍስ ነበረችና:: ፈጣሪያችን የአንድ ሰው ነፍስ ግድ ይለዋል:: ለዚህም ነው «ሁለትና ከዚያ በላይ ሆናችሁ በስሜ ብትሰባሰቡ እኔ በመካከላችሁ እገኛለሁ» ያለው ታዲያ ሕዝቡ ካልበዛ አንሰብክም የሚሉ ሰባኪዎችን ምን እንላቸዋለን? ዝና ፈላጊዎች ወይስ አገልጋዮች? መልሱን ለእናንተ እተዋለሁ::

፮. በጣም መጮኽ

በጣም ስለጮኹ ድንቅ ሰባኪ የሆኑ የሚመስላቸውም አሉ:: የሰዎች ድምፅን መስማት የምንችለው በጣም ሳይጮኽና በጣም ዝቅ ሳይል በመካከለኛ የድምፅ ሞገድ ነው:: ከዚህም በተጨማሪ እንደየታሪኩ ሁኔታ ድምፅን መቀያየር ይገባል እንጂ አብዝቶ መጮኽ ስብከት አይደለም:: ይኼም ቢታረም ጥሩ ነው::

፯. እራስን መስበክ

የራስን ታሪክ ዝርዝር መናገር፣ ስለ እራስ አገልግሎትና የትምህርት ደረጃ ማውራት፣ እንግሊዝኛ እንደሚያውቁ ሊገልጹ የሚፈልጉ ወዘተ የመሳሰሉ ሰባኪዎች እንዳሉም አልፎ አልፎ ለማየት ችያለሁ:: ይህ በሰው ዘንድ ለመከበርና ለመወደስ የታለመ ይመስላል::

መጥምቀ መለኮት ቅዱስ ዮሐንስ «እነሆ የእግዚአብሔር በግ» /ዮሐ. ፩፥፴፮/ በማለት ደቀ መዛሙርቱን ወደ ክርስቶስ መራቸው፤ እነርሱም ተከተሉት ስለዚህ ሰባኪ ሕዝቡና ክርስቶስን እንዲከተል ማድረግ ነው እንጂ የራሱን አጃቢ የማሰባሰብ ዓላማ ሊኖረው አይገባም:: ስለዚህ ይህም ሊታረም ይገባል «ሰባኪ ማለት ነፍሳትን ወደ እግዚአብሔር የማምጣት አገልግሎት እንጂ ውዳሴን ለራስ ማከማቸት አይደለም» በቅርቡ አንድ ሰባኪ በአንድ መጽሔት ላይ በሰጠው ቃለ ምልልስ «ከጀርባችን መቶ ሺዎች አሉ» ማለቱን ልብ ይበሉ::

፰. ሰባኪም ዘማሪም የሆኑ /ካሴትን ማስተዋወቅ/

እነዚህ ሰዎች ዓላማቸው ዘመርን ያሉትን ካሴት መሸጥ ብቻ እንደሆነ አቋማቸው ያስረዳል:: ከካሴታቸው ጋር የሚመሳሰል ርእስ በመምረጥ ይሰብኩና በየስብከቱ ጣልቃ ከዚያ ካሴታቸው ውስጥ ይዘምራሉ:: እነዚህ ሰዎች የቃሉ ነጋዴዎች እንደሆኑም ያስታውቃሉ:: ከዚያም «ይህ የእኔ መዝሙር ነው ቁጥር እንደዚህ» እያሉ በመስበክ አብዛኛውን ጊዜ የራሳቸውን ማስታወቂያ በመሥራት ያጠፋሉ::

በአጠቃላይ ግን ለመዘርዘር ስለሚያስቸግር ከላይ ካሉት በተጨማሪ ርእስን አለመጠበቅ፣ የተሰባኪውን ዕውቀት አለመለካት /አለመመርመር/፣ በጊዜ አለመጠቀም /አለመቆጠብ/፣ በስብከታቸው ውስጥ የምንአልባት የሚሉትን የጥርጣሬ ሐሳቦች /አባባሎች/ የሚከቱ፣ የአካል እንቅስቃሴን በልክ አለማድረግ /በእግዚአብሔር ቤት እግርን አለመጠበቅ/ የመሳሰሉት በሙሉ የሚታዩባቸው አገልጋዮች በዝተዋል:: ይህንንም ስንል በቅንነት የሚሰጠውን አስተያየት ነገርን ባለመሰንጠቅ ሊቀበሉ ይገባል:: የሚደረገው ሁሉ ንጹህና ሙሉ የሆነው የእግዚአብሐርን ቃል በሥርዓትና ሰውን ለማነጽ በሚረዳ መልኩ ቢሰብኩ መልካም ነው እያልኩ እሰናበታችኋለሁ::✥

*ገብረ መስቀል*
*ከየካ ደ/ም/ኪዳነ ምሕረትና*
*መድኃኔዓለም ቤተ ክርስቲያን*
*መሠረተ ሕይወት ሰንበት ት/ቤት*

## ደራሽ «ሰባክያን»

በቀደሙት የሐመር ኅትመቶች ተገቢውን ምክክር፣ መረጃና የሊቃውንት ብስለትን ያየንበት በ«መዝሙሮች» ላይ የተደረገ ውይይት መልካም ነበር::

ስለ ስብከቶቻችን ለመወያየት ሰፊ ነገር ማለት ቢቻልም፤ ከሁለት ጉዳዮች አንጻር ላብራራና ሌሎቹንም ልጠቁም

፩. በእርግጥ ዛሬ ዛሬ የስብከት አገልግሎት አድጓል:: ለመጥቀስ ያህል ጥቂት ሰንበት ት/ቤቶችና የአብነት መምህራን በበዓላትና በሰንበት /ቅዳሜና እሑድ/ የሚያስተምሩባቸው ዘዴዎች እየጠነከሩ፣ እየሰፉ፣ ሕዝቡን እየማረኩ እስከ ፲፱፻፺ዎቹ መግቢያ የበለጠ አድጓል:: ይኸውም በሠርክና በመምህራኑ ፈቃድ በሚዘጋጅ ሰፊ ሰዓት ኋላም የሁለትና ሦስት ቀን ጉባኤ ለረጅም ሰዓታት ሲደረግ እያደር ልዩ ልምድ ሆኖ አንጉረ ስብከቶች በአድናቆትና በጉጉት ቶሎ ተላምደውት እያለ የመምህራን እጥረት ከፍ ያለበት ወቅት ሆነ:: ይህንን የተረዱ ብዙ ወጣቶች ወደ ስብከተ ወንጌል ሲመጡ ደግሞ መምህራንን መምረጥ፣ አገልግሎቱ እንዳይከብዳቸው አስፈላጊውን ሁሉ ወጪ እስከ ማውጣት ተደርሷል:: ኋላ ደግሞ በሰባኪያኑ የሚዘጋጅ የመጽሐፍና የመዝሙር ገበያ እየተቀላቀለና ገበያ ያለውን ጉባኤ ወደ ማፈላለግ ተደረሰ:: በዚህ ሁኔታ ግራ የተጋቡ የተወሰኑ መምህራን ደግሞ የነገሩ ሒደት እስኪጠራ ይመስላል ጥግ ይዘው ቆመዋል:: በዚህ መሐል ግን አዳዲስ የስብከት ባሕሎች እየተንሠራፉ መጡ::

አሁን ምእመናን በተለይ /ወጣቱ/ ጠማማ ጎዳና እየተመራ ሲሆን ኅልማሳው በፍቅርና ተመስጦ የሚማረው ቃል እያጣ፣ የሰከነና መንፈሳዊ ለዛ ያለው ስብከት ተአምር እየሆነ ነው:: ይህ እኔ ትናንሹንና ትላልቁን ከተሞች እስከ ገጠር ድረስ ያለውን የሰሜን ምዕራብ፣ የደቡብ የምዕራብና የመሐል ኢትዮጵያን ስብከተ ወንጌል ታሪክ በግርድፉ የገመገምኩት ነው::

፪. ሌላው ዕይታዬ መምህራኑ ካላቸው የእግዚአብሔር ፍቅርና ተመክሖ አንጻር ነው:: የወንጌል መምህራን የሚመኩት በመከራ መስቀል፣ ስለ እውነት በመገፋታቸው፣ ተስፋቸውና ደስታቸውም የእግዚአብሔር ስጦታ /ጸጋ/ ብቻ መሆን አለበት:: ስጦታው ሁለመናችንን የሚባርክ ነው:: ለጤናም፣ ለዕለት ጉርስም ለዓመት ልብስም ጸጋው ይበቃናል እንጂ ሌላ ተስፋ የለንም:: ይህን ተስፋ ይዘው ብዙዎች በዘመናችን ጭምር ቃሉን በግልጽና ከተአምር ጋር መስክረው ብዙዎችን ማርከዋል:: ይሁን እንጂ ይህን ምርኮና የቤተ ክርስቲያን የስብከተ ወንጌል መነቃቃትን የሚያደበዝዙ ቃሉና ተአምሩ ሳይማርካቸው እንጀራነቱ የማረካቸው ገቡበት፤ እናም ለራሳቸው በሚመች ስምሪት ቃኙት:: የመጽሐፍ ቅዱስን ቃል በትክክል ስለመስበካቸው፣ የቤተ ክርስቲያኗን አስተምህሮ በቃልና በሕይወት ስለመቀበላቸውና ስለ መግለጣቸው፣ ደንታ የለሽ የሆኑ የመድረክ ላይ አንበሶች፣ ኀጉተው ለቀረቧቸው የተራቡችን ነፍስ በቅድስና አልባ ቃላቸውና ሕይወታቸው ከበረቱ የሚያስደነብሩ ተኩላዎች ተከሰቱ::

ስለዚህ እኔ የምለው የተተኪው ትውልድ መሰብሰቢያ ሰንበት ት/ቤት ተልእኮውን እንዲወጣ ይደገፍ፤ ምእመናኑን የሚያስናክሉ ደራሽ «ሰባክያን» በሥርዓት ተለይተው ይመኪሩ፤ ከግብዝነትና ከሥጋዊ ገበያ የጸዳ የሃይማኖት ሥርዓታችንን እንደዚህ ያሉ ወገኖች እንዳይበክሉት በእርጋታ ይታሰብበት ከቃል ብዛት ሳይሆን በእውነተኛ መንፈሳዊ ኃይል የኖርንበት ተገቢ ሕይወት ይጠናከር እላለሁ፤ አምላክ በረድኤት አይለየን::

✥

*ቄስ ሰይፉ*
*ከጅማ*





www.eotcmk.org

# ዐርገ እግዚእ ከመ ያለቡ ዕርገተ ጻድቃን

## ጌታችን የጻድቃንን ዕርገት ያስገነዘበን ዘንድ ዐረገ

*ዲ/ን ዘላለም ቻላቸው*

ጌታችን መድኃኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስ የሰውን ልጅ ከወደቀበት ለማን ሣት ከሰማየ ሰማያት ወርዶ በድንግል ማርያም ማኅፀን ዘጠኝ ወር ከአምስት ቀን አድሮ፣ ከሥጋዋ ሥጋ ከነፍስዋም ነፍስ ነስቶ፣ ተወልዶ፣ ሠላሳ ሦስት ዓመት ከሦስት ወር በዚህ ምድር ላይ ተመላልሶ፣ የእኛን የእዳ በደል ለመደ ምሰስ ተይዞ፣ ተገርፎ፣ የእሾህ አክሊል ተቀዳጅቶ፣ ተሰድቦ፣ ወሪቀ ምራቅን ተቀብሎ መስቀል ተሸክሞ፣ እጆቹንና እግሮ ቹን ተቸንክሮ፣ በመ ስቀል ላይ ተሰቅሎ፣ ስለ እኛ ሲል የሞ ትን ጽዋ ቀምሶ፡፡ ሦስት ቀን እና ሌሊት በመቃብር ካደረ በኋላ ለትንሣ ኤያችን በኩር ሊሆነን አስቀድሞ እንደተናገረ ከሙ ታን ተለይቶ ተነሥቷል፡፡ ክብር፣ ኃይል፣ አምልኮና ስግደት ለእርሱ ይሁን፡፡

ጌታችን ከሙታን ተለይቶ ከተነሣ በኋላ ለአርባ ቀናት ያህል በዚህ ምድር ቆይቶ በተለያየ ቦታና ጊዜ ለሐዋ ርያት ተገልጧል፡፡ ይህም የት ንሣኤውን ምስጢር ይረዱ ዘንድ ነው፡፡ /ሐዋ.፩÷፫/

ሊቃውንት አባቶቻችን ሲያ ስተምሩ ጌታ ለእነ መግደላ ዊት ማርያም /ሉቃ.፳፬÷፩/፣ ለሉቃስና ለቀለዮጳ /ሉቃ.፳፬÷፲፫-፴፪/ እንደተገለጠው ሁሉ አርባውን ቀን ሙሉ ለአንዱ ወይም ለሁለቱ ደቀመዛሙርት ሳይገለጥላቸው አይውልም ነበር፡፡ ነገር ግን ጉባኤ ዘርግቶ ሁሉም ሐዋርያት በተገኙበት ያስተ ማረባቸው ዕለታት ግን የተ ወሰኑ ናቸው፡፡

ጌታችን በእነዚህ ዕለታት ለሐዋርያት ሰባቱን ኪዳናት አስተምሯቸዋል፡፡ እነዚህም ጸሎተ ኪዳን፣ ቅዳሴ እግዚእ /በሰማይ የሃሉ/ ቅዳሴ እግዚእ /ፍሬ ቅዳሴው ነአኩተከ/፣ ትም ህርተ ኅቡአት፣ በእንተ ቅድ ሳት፣ እግዚአብሔር ዘብርሃንና እና በቅዳሴ ጊዜ ድርገት ሲወ ርድ የሚባለው ቅዱስ ቅዱስ ቅዱስ ሥሉስ ዘኢይትነገር የሚሉት ናቸው፡፡

ከዚህ በኋላ ጌታችን መድኃኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስ አስቀድሞ ክቡር ዳዊት በመዝሙሩ «ዐርገ እግዚአብሔር በይባቤ፣ ወእግዚእነ በቃለ ቀርን» /መዝ.፵፮÷፭/ ብሎ እንደተናገረ በክብር በምስጋና ወደ ሰማይ ዐርጓል፡፡

የጌታችንን የዕርገቱን ነገር ቅዱስ ሉቃስ ከሌሎቹ ሁሉ አስፍቶ ጽፎታል፡፡ /ሉቃ.፳፬÷፶-፶፫፤ ሐዋ.፩÷፲፩/

ጌታ ደቀመዛሙርቱን ይዟቸው ወደ ደብረ ዘይት ተራራ ወጣ፡፡ ይህ ተራራ ጌታ የተራራው ስብከት ተብሎ የሚጠራውን የመጀመሪያውን ታላቅ ስብከት የሰበከበት /ማቴ.፭÷፯/፣ ስለ ምጽአት ያስ ተማረበት /ማቴ.፳፬÷፩/ በተራራው ሥር በሚገኘው የጌቴሰማኒ የአትክልት ሥፍራ አዘውትሮ የሚጸልይበት /ማቴ.፳፮÷፴፮/ ቦታ ነበር፡፡ ጌታ ይህንን ተራራ ለዕርገ ቱም መርጦታል፡፡ ብዙ መምህራን ደግሞ ለፍርድ ሲመጣም የሚገለጠው በዚህ ተራራ ላይ ነው፤ እግሮቹ ያርፉበታል ይላሉ፡፡

በዚያ ተራራ ላይም ጌታችን ደቀመዛ ሙርቱን ከባረካቸው፣ በዓለም ሁሉ ምስ ክሮቹ እንዲሆኑ ከአዘዛቸው፣ ስለሚመ ጣላቸው አጽናኝ መንፈስ ከነገራቸው እና ኃይልን ከሰማይ እስኪ ያገኙ ድረስ በኢየሩሳሌም እንዲ ቆዩ ከነገራቸው በኋላ ደቀ መዛሙርቱ ከበው ቆመው እየተመለ ከቱት ከፍ ከፍ እያለ ወደ ሰማይ ዐረገ፡፡ «እየባረካቸውም ራቃቸው ወደ ሰማ ይም ዐረገ» /ሉቃ.፳፬÷፶፩/፣ «ይህንንም እያ ነጋገራቸው ከፍ ከፍ አለ፤ ደመናም ሰውራ ተቀበለችው፤ እነርሱም ወደ እርሱ እያዩ ወደ ሰማይ ዐረገ....» /ሐዋ.፩÷፱/

አባቶቻችን ይህንን የጌ ታችንን ዕርገት እንዲህ በማ ለት ይገልጡታል፡፡ ጌታ ያረ ገው በርቀት /ቀ ጠብቆ ሲ ነበብ/ ሳይሆን በርቀት /ርህ ቀት/ /ቀ ላልቶ ሲነበብ/ ነው፡፡ ርቀት /ቀ ጠብቆ ሲነበብ/ ማለት እንደ ጢስ ተኖ፣ በኖ መጥፋት ማለት ሲሆን ርቀት /ቀ ላልቶ ሲነበብ/ ........... በመራቅ፣ እየታየ ከፍ ከፍ በማለት መለየት ማለት ነው፡፡

የጌታችን ዕርገት እንደ ሁለተኛው ያለ ነው፡፡ የጌታ ችን ዕርገት በዚህ መልኩ መሆኑ ጌታ የእኛን ሥጋ ፍፁም መወሐዱንና ያ ሥጋም ወደ ዘበነ ኪሩብ ማረጉን የሚያጠ ይቅ / የሚያሳይ/ ነው፡፡

ቅዱስ ቄርሎስ የሥጋንና የመለኮትን መዋሐድ ጉዳይ ሲገልጽ «እንቲአሁ ለሥጋ ኮነ ለቃል፤ እንቲአሁ ለቃል ኮነ ለሥጋ» የሥጋ ገንዘብ የሆነው ሁሉ የመለኮት ገንዘብ ሆነ የመለኮት ገንዘብ የሆነው ሁሉ የሥጋ ገንዘብ ሆነ ብሏል፡፡

ይህም ማለት መልአኩ ቅዱስ ገብርኤል እመቤታችንን ባበሰራት ጊዜ ልክ እመቤታችን

ዐርገ እግዚአብሔር በይባቤ

ወእግዚእነ በቃለ ቀርን



ሲሔድ እንዳያችሁት እንዲሁ ይመጣል

«ይኩነኒ በከመ ትቤለኒ» እንደ ቃልህ ይደረግልኝ /ሉቃ.፩፥፴፰/ ባለችው ጊዜ /ቅጽበት/ እግዚአብሔር ወልድ /ቃል/ በተለየ አካሉ ከሰማየ ሰማያት ወርዶ ከሥጋዋ ሥጋ ከነፍሷ ነፍስ ነስቶ በማኅፀኗ አድሯል። እግዚአብሔር ወልድ /መለኮት/ የሥጋን ባህርይ ገንዘብ አድርጎ አንድ ቀን ተብሎ ዕድሜ ተቆጥሮለታል /ጥንትና ፍጻሜ የሌለው ሲሆን፣ የማይወሰን ምሉዕ ሲሆን/፤ በእመቤታችን ማኅፀንም ተወስኗል። በዚያች ቅጽበትም ያ ከእመቤታችን የተነሳው ሥጋ ወደ ሰማያት ወጥቶ ከአብና ከመንፈስ ቅዱስ ጋር በዘባነ ኪሩብ ተቀምጧል። እግዚአብሔር ወልድ በእመቤታችን ማኅፀን አደረ ስንል በዘባነ ኪሩብ የነበረው ወልድ ሥጋን ተዋሕዶ ነው። ስለዚህም ሥጋ /ፍጡር ሲሆን/፣ የመለኮትን ባህርይ ገንዘብ አድርጎ ምሉዕ ሆኗል/ ማለት ነው/.......... ምስጢሩን ይገልጥልን።

**ጌታችን ይህንን ያደረገው ትንሣኤው የጻድቃን የክብር ትንሣኤ እንዳለ እንደሚያስገነዝበን ሁሉ በዕርገቱም የጻድቃንን ዕርገት እንገነዘብ ዘንድ ነው።**

ስለዚህ ጌታችን ከትንሣኤው በኋላ በአርባኛው ቀን ዐረገ ስንል ሥጋ ወደ ዘባነ ኪሩብ የወጣው በዚህ ዕለት ነው ማለታችን አይደለም። ሥጋ ወልድ በማኅፀነ ድንግል ከተፀነሰበት ቅጽበት ጀምሮ ሥጋ በዘባነ ኪሩብ ነበር።

የጌታችን ዕርገት ይህንን ምስጢር በተረዳ ነገር ያወቅንበት ዕለት ነው። ለምሳሌ እግዚአብሔር በአንድነት በሦስትነት ጸንቶ ይኖር የነበረው ዓለም ከመፈጠሩ አስቀድሞ ነው። ይህ የእግዚአብሔር ሦስትነት ግን ለሰው ልጆች በግልጽ የታወቀው ጌታችን በተጠመቀበት ጊዜ ነው። አብ ከሰማይ ሆኖ «የምወደው ልጄ» ሲል ወልድ በዮርዳኖስ ሲጠመቅ፣ መንፈስ ቅዱስም በተለየ አካሉ በርግብ አምሳል ሲወርድ እግዚአብሔር ሦስትነት እንዳለው ታውቋል። ስለዚህ የጥምቀትን ቀን ምስጢረ ሥላሴ /የሦስትነት ምስጢር/ የተገለጠበት ቀን ነች እንላለን። ቀኗ በግሪክ ቋንቋ ኤጲፋንያ ትባላለች። ኤጲፋንያ ማለት መገለጥ ነው። ይህ ማለት ግን ጌታችን ከተጠመቀበት ቀን በፊት እግዚአብሔር ሦስትነት ያለው አልነበረም ማለት አይደለም። /ማቴ.፫፥፲፫- ፲፯/

ዕርገቱንም በተመለከተ ያለውን ነገር ልንረዳው የሚገባው በዚህ መልኩ ነው። ጌታችን መጋቢት ፳፱ ቀን በእመቤታችን ማኅፀን ከተፀነሰባት ቅጽበት ጀምሮ ሥጋና ቃል ለአንዲት ቅጽበት አልተለያዩም። ሥጋም በዘባነ ኪሩብ ነበር። የጌታችን ዕርገት ደግሞ ጌታችን ደቀመዛሙርቱ እያዩት ከፍ ከፍ እያለ /በርህቀት/ ወደ ሰማይ በመውጣቱ / በማረጉ/ ይህ ረቂቅ ምስጢር ለሰው በሚረዳ መልኩ የተገለጠበት ነው።

ከዚህ በመቀጠል ደግሞ ይህ የጌታችን ዕርገት ለሰው ልጆች ያለው ትርጉም ምንድን ነው? የሚለውን እንመለከታለን።

### ሀ. እግዚአብሔር ለሰው ልጆች ያለው ጥልቅ ፍቅር የተገለጠበት ነው

በነገረ ድኅነት ውስጥ ለተከናወኑት ነገሮች ማለትም የእግዚአብሔር ወልድ ሥጋን መዋሐድ፣ በሥጋ መወለድ፣ መሰቀል፣ ትንሣኤ፣ ዕርገት፣ ወዘተ መነሻ የሆነው የአዳም በደል ነው።

አዳም ዕፀበለስን የበላው «አምላክ ትሆናለህ» /ዘፍ.፫፥፭/ የሚለውን ... ሰምቶ አምላክ ለመሆን አስቦ በመሆኑ በደሉ «መልካምና ክፉን ከሚያስታውቀው ዛፍ አትብላ» /ዘፍ.፪፥፲፯/ የሚለውን ትእዛዝ መሻር ብቻ ሳይሆን «እግዚአብሔር በመሆን» ከእግዚአብሔር ጋር ለመጣላት በጠላትነት መነሣትም ነው፤ ሁለት እግዚአብሔር ሊኖር አይችልምና።

እግዚአብሔር ግን አዳም እንዲህ ያለ ታላቅ በደል ቢበድልም እንኳን ይቅር አለው። እግዚአብሔር ራሱ ተበዳይ ሆኖ ሳለ አንድያ ልጁን ልኮ ለአዳም በደል በሞት ካሳውን ከፈለ። ቅዱስ ሥጋውን ክቡረ ደሙን ሰጠን።

በጌታችን ዕርገት ደግሞ ከእነዚህም በላይ የሆነ እግዚአብሔር ለሰው ልጅ ያለውን ኃያል ፍቅር ተረድተናል። አዳም የበደለው፣ ዕፅ በለስን የበላው አምላክ መሆን ፈልጎ ነው። እግዚአብሔር አዳምን ይህንን እንኳን አልከለከለውም። እግዚአብሔር ወልድ /ቃል/ የተዋሐደው ሥጋ በዘባነ ኪሩብ በመቀመጡ የሰው ልጅ /አዳም/ አምላክ ሆኗል። ሊቃውንት «ሰው አምላክ ሆነ ፤ አምላክ ሰው ሆነ እንዲሉ።፡» ድንቅ ፍቅር።

ከነዚህ አስቀድመን እንዳልነው ምንም እንኳን ይህ የተደረገው በዕለተ ጽንሰት ቢሆንም ለሰው ልጆች ግን የተገለጠው /የተረዳው/ በዕርገት ጊዜ ስለሆነ ዕርገት ይህንን እግዚአብሔር ለሰው ልጆች ያለውን ታላቅ ፍቅር እና የሰውን ልጅ የዚያ.......... ባህርይ ተካፋይ በማድረጉ የሰጠንን ታላቅ ክብር የተረዳንበት ነው።

ምንም እንኳን ኀድሎበት ባንሞላለት፤ አንሶት ባንጨምርለት እንዲህ ለወደደን ለአምላካችን እኛስ ምን እናደርግ ይሆን? እናመስግነው እንጂ።

### ለ. የሰው ልጆች ዕርገት የተረጋገጠበት ነው

ቅዱስ ዮሐንስ አፈወርቅ «ዐርገ እግዚእ ከመ ያለቡ ዕርገተ ጻድቃን፡- «ጌታችን የጻድቃንን ዕርገት ያስገነዝበን ዘንድ ዐረገ» ይላል።

ይህም ማለት ጌታችን ዕርገቱን አስቀድመን ባየነው መልኩ ያደረገው አንድም በሰማያት የሌለ ሆኖ ወደዚያ መውጣት አስፈላጊ ሆኖ አይደለም፤ መጀመሪያውኑም ሥጋን ተዋሕዶ በዚህ ምድር ላይ ሲመላለስ ከሰማይ መንበሩ ጎሎ አይደለምና አንድም በአንድ ጊዜ በቅጽበት የአሰበውን ማድረግ የማይችል ቀስ በቀስ ማድረግ የሚያስፈልገው ሆኖ አይደለም፤ ለይኩን ብሎ ይህንን ዓለም የፈጠረ ነውና።

ነገር ግን ጌታችን ይህንን ያደረገው ትንሣኤው የጻድቃን ትንሣኤ እንዳለ እንደሚያስገነዝበን፤ በዕርገቱም የጻድቃንን ዕርገት እንገነዘብ ዘንድ ነው።

አዳም በበደሉ ምክንያት ከገነት ተባሮ ሲወጣ ሦስት ዋና ዋና ነገሮችን አጥቷል።



www.eotcmk.org

፩. በእግዚአብሔርና በሰው ልጆች /በአዳም/ መካከል በተፈጠረው የጥል ግድግዳ ምክንያት የእግዚአብሔር ልጅነቱን አጥቶ ልጅ ሳይሆን ባርያ እየተባለ መኖር ጀምሯል:: ከቅዱሳን መላእክት አንድነትም ተለይቷል::

፪. «በበላህ ቀን ሞትን ትሞታለህ» /ዘፍ.፪፥፲፯/ የሚለው የሞት ማስጠንቀቂያ ተፈጽሞበት በሰውነቱ ላይ ሞት ነግሦበት፤ በሕይወተ ሥጋ እያለም ኑሮው በጽላሎተ ሞት /በሞት ጥላ ስር/ ውስጥ/ የወደቀ እና በሞት ፍርሃት የተወጠረ፤ ሲሞትም ነፍሱ በጻዕር ተለይቶ ሥጋው ወደ መቃብር፣ ነፍሱ ወደ ሲዖል በመውረድ በጭንቅና በመከራ የሚኖር ሆኗል::

፫. ሰማያዊነቱን አጥቶ ምድራዊ ሆኗል:: የክርስቲያን አገሩ በሰማይ ነው:: ይህም ማለት የተፈጠርነው በምድር ላይ ለመኖር ሳይሆን በሰማያት ልክ እንደ ቅዱሳን መላእክት እግዚአብሔርን እያመሰገን ሰማያዊ ኑሮ ለመኖር ነው:: አዳምም ዕፀ በለሰን በልቶ ይህ ፍርድ ባይፈረድበት ኑሮ አንድ ሺሕ ዓመት በገነት ኖሮ፣ ዕፀ ሕይወትን በልቶ፣ ታድሶ ወደ ኢየሩሳሌም ሰማያዊት ይገባ ነበር:: እዚህ ላይ ማስተዋል የሚገባው ገነት፣ መሬት፣ ሲዖል፣ ብሔረ ሕያዋንና ብሔረ ብፁዐን የምድር ክፍሎች ሲሆኑ ኢየሩሳሌም ሰማያዊት፣ ዓለማተ መላእክት፣ ወዘተ... የሰማያት ክፍል መሆናቸውን ነው:: ስለ ዚህ አዳም ዕፀበለስን በመብላቱ ሰማያዊ መሆኑ ቀርቶ ምድራዊ ሆኗል ማለት ነው:: ምክንያቱም በገነት አንድ ሺሕ ዓመት ኑሮ ዕፀ ሕይወትን በልቶ ኢየሩሳሌም ሰማያዊት መግባቱ ቀርቶ በሕይወተ ሥጋ ሳለ በምድር፣ ሲሞትም ነፍሱ በሲዖል /ሁለቱም የምድር ክፍል ናቸው/ የሚኖር ሆኗል:: ሰማያዊነቱን አጥቷል:: ጌታችን መድኃኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስ የእኛን ሥጋ ተዋሕዶ ባደረገው የማዳን ሥራ እነዚህን ሦስቱንም ያጣቸውን መልሶለታል::

፬. ጌታችን በሕማማቱና በሞቱ የአዳምን የበደል ካሳ ከፍሎ፣ አማናዊ መሥዋት በመሥዋዕት እራሱ ካህን እና መሥዋዕት ተቀባይ ሆኖ በመስቀል ላይ ተሰቅሎ የጥል ግድግዳን አፍርሷል:: በዚያው በመስቀል ላይ ሳለም ልጅነቱንና ክብሩን አጥቶ በባርነት ውስጥ ሆኖና ተዋርዶ የነበረው የሰው ልጅ ዳግመኛ ከእግዚአብሔር የሚወለድበትንና ልጅነትን የሚያገኝበትን ለጥምቀት የሚሆነውን ውኃ በጐኑ አፍስሶ /ማየ ገቦ/ ሰጥቶታል:: /ገላ.፬፥፮፤ ዮሐ.፫፥፩-፲፭፤ ዮሐ.፲፱፥፴፬/ ወደ ቅዳሳን አንድነትም ተቀላቅሏል:: /ሉቃ.፪፥፲፬፤ ኤፌ.፲፬፥፲፰፤ ዕብ.፲፪፥፳፫-፳፬/

፭. ጌታ በትንሣኤው ሞትን ድል አድርጎ የሰውን ልጅ ከሞት አገዛዝ ነጻ አውጥቶታል:: በመቃብር ተይዞ ፈርሶና በስብሶ መቅረትን አጥፍቶልናል:: ከዚህም በኋላ ሞት እንደ ቀድሞው የሚያስፈራ ነገር ሳይሆን ወደማያልፈው ዓለም መሄጃ መንገድ ሆኗል::: /ዕብ.፪፥፲፬-፲፭፣ ፩ኛ.ቆሮ.፲፭፥፳፩- ፳፪፣፶፩/

፮. የሰው ልጅ እንደ ጥንቱ ሰማያዊ መሆኑ /እንደሚሆን/ እና ምድራዊ ሆኖ እንደማይቀር የተረጋገጠው ደግሞ በጌታችን ዕርገት ነው:: ቅዱስ ጳውሎስ በመጀመሪያው የተሰሎንቄ መልእክቱ ውስጥ ይህንን በሚከተለው መልኩ ጽፎታል::

«ወንድሞቻችን ሆይ ስለ ሞቱ ሰዎች ተስፋ እንደሌላቸው እንዳታዝኑ ልታውቁ እንወዳለን:: ኢየሱስ ክርስቶስ ሞቶ እንደተነሣ ካመንን እንዲሁ እግዚአብሔር ሙታንን ከመቃብር ያስነሣቸዋል ከእርሱም ጋር ያመጣቸዋል:: ይህንንም በእግዚአብሔር ቃል እንነግራችኋለን.... ጌታችን ራሱ በትእዛዙ በመላእክትም አለቃ ድምፀ መለከት ከሰማይ ይወርዳልና:: በክርስቶስም የሞቱ ሙታን አስቀድመው ይነሣሉ:: /ከዚያም በኋላ... ጌታችንን በአየር እንቀበለው ዘንድ ከእርሱ ጋር እንኖራለን::» /፩ኛ.ተሰ.፬፥፲፫-፲፯/

ቅዱስ ጳውሎስ በዚህ የመልእክቱ ክፍል እያስረዳን ያለው «በክርስቶስ የሞቱ ሙታን አስቀድመው ይነሣሉ» በማለት በእግዚአብሔር አምላክነትና በኢየሱስ ክርስቶስ የባህርይ ልጅነት አምነውና ምግባርና ትሩፋት ሠርተው ከሞቱ በኋላ በትንሣኤ ዘጉባኤ /በዳግም ምጽአት/ ትንሣኤ ዘለክብር የሚነሡ ሰዎች ከትንሣኤያቸው በኋላ የሚያጋጥማቸውን /የሚደረግላቸውን/ ነገር ነው::

በክርስቶስ ሞተው ትንሣኤ ዘለክብር የሚኖራቸው ሰዎች ጌታ በሚያስፈራ ግርማ፣ በታላቅ አጀብ በአባቱ ክብር ደግሞ በሚመጣ ጊዜ እርሱን ለመቀበል ልክ ጌታ በዕርገቱ ጊዜ እንዳደረገው እርሱን ለመቀበል በደመና ወደ ሰማይ ይነጠቃሉ:: ከዚያም በማታልፈው ዓለም በኢየሩሳሌም ሰማያዊት ከእርሱ ጋር ሆነው ለዘለዓለም ይኖራሉ::

ቅዱስ ዮሐንስ አፈወርቅም «ዐርገ እግዚእ ከመ ያለቡ ዕርገተ ጻድቃን፤ የጻድቃንን ዕርገት ያስረዳ ያሳውቅ ዘንድ ጌታችን ዐረገ» በሎ የገለጸው ይህንን ነው:: የእኛን ሥጋ ተዋሕዶ ባደረገው ዕርገት ሁሉን ያደረገልን አምላካችን የተመሰገነ ይሁን::♦

# «በዓለ ሃምሳም...»

ከገጽ ፯ የዞረ

በቤቷ ተገኝታ ሰላምታዋን ስታሰ ማት ነው:: /ሉቃ.፩፥፵፩/ በዶኪማስ ቤት ችግር የተፈታው እመቤታቸን በመገኘቷም ነው:: /ዮሐ.፪፥፩-፭/ ይህንን ያስተዋሉ ሐዋርያት የመንፈስ ቅዱስ መውረድ እውን እንዲሆንላቸው እና ደካሞች የነበሩ ኃያላን የሚሆኑበትን ኃይል እንዲያገኙ የአምላክ እናትን ይዘው ተማጽነዋልና ተፈጸመላቸው:: ዛሬም ቢሆን በአማላጅነቷ አምነው የምስጋናዋን ድምፅ ካልሰሙ በስሟም ካልተማጸኑ የመንፈስ ቅዱስ ጸጋ አይገኝም::

## ፬. በአንድ ልብ ሆነው ስለተጉ

ሐዋርያት መንፈስ ቅዱስን በተቀበሉበት ዕለት በአንድ ልብ ሆነው አብረው ይጸልዩ እንደነበር ወንጌላዊው ሉቃስ በጻፈው በሐዋርያት ሥራ ላይ ተመዝግቧል:: ሐዋ. ፩፥፲፬ አንድ ልብ መሆን የሚያመለክተው አንድ እምነትን፣ መዋደድን፣ መከባበርን፣ መደማመጥን ... ነው:: የሙቶ ሃያው ቤተሰብ አንድ ልብ መሆን በዚህ መልኩ የሚቀርብ ጸሎት የመንፈስ ቅዱስን ጸጋ እንደሚያስገኝ ዛሬም ላለነው ካህናትና ምእመናን የሚያስተምረን የቤተክርስቲያን ታሪክ ነው:: በተለያየ መንፈሳዊ አገልግሎት ላይ የምንገኝ እንደየክህነታችንና ድርሻችን የምጠንተጋ የቤተ ክርስቲያን ልጆች አለን:: ነገር ግን ምን ያህል አንድ ልብ ነን? አንድ ዓላማ ይዘን ነገር ግን አንድ ልብ መሆን ባለመቻላችን /መደማመጥ፣ መቻቻል፣ መከባበር...ገንዘብ ባለማድረጋችን/ አንዳንዶቻችን እንዲያውም ስብከታቸውም፣ ዝማሬያቸው፣ ስለ እምነት ሳይሆን ስለ መብት እስከመሆን ደርሷል:: አገልጋዮች ከእግዚአብሔር ይልቅ ለሰው ካደላን፣ ከመንፈሳዊነት ይልቅ ሥጋውያን ከሆንን፤ ከበረከት ይልቅ ገንዘብ ከወደድን፤ ኃጢአትና ጽድቅን መለየት ከተቸገርን ከመንፈስ ቅዱስ በራቀ ሕይወት ላይ እንደ ሆንን እናስተውል:: መለያየት የበዛብን፤ ትዕቢት የነገሠብንም ለዚሁ ነው:: የሐዋርያት አገልግሎት ለጽድቅ አክሊል ያበቃቸው በአንድ ልብ ሆነው መትጋታቸው መሆኑን ካመንን፤ እኛም ከአባቶች ጀምሮ እስከ ምእመናን ድረስ ያለን በሁላችን አንድ ልብ መሆንና ዓላማ እርሱም ለጽድቅ ለመሥራት፣ በቤተ ክርስቲያን በአንድነት ለማገልገል መቆም ይገባል::♦

*ረድኤተ እግዚአብሔር አይለየን*



www.eotcmk.org

# ዕጣ በቤተ ክርስቲያን ትምህርትና ሥርዓት

*በዲ/ን ምትኩ አበራ*

ዕጣ /እጸ/ የሚለው ቃል ዐፀወ ዕጣ ተጣጣለ /አወጣ/ ከሚለው ግስ የወጣ ሲሆን አለቃ ኪዳነ ወልድ ክፍሌ በግእዝ አማርኛ መዝገበ ቃላት መጽሐፋቸው አጭርና ቀጭን እንጨት፤ ከመካከለኛ ጣት የሚበልጥ፤» ብለው ይፈቱታል። ዕጣ እድል ድርሻም ሊባል ይችላል፡፡ የዕጣ አሠራር ከክርስቶስ ልደት በፊት ከአራቱ ጊዜ ጀምሮ እንደነበር መጽሐፍ ቅዱስ ይነግረናል፡፡ በጥንት ጊዜ ሰዎች ዕጣን በእንጨት፣ ጽሑፍ ባለበት ድንጋይ /ጠጠር/ ይጥሉ ነበር፡፡

የዕጣ ሥርዓትን ለሰዎች ያስተዋወቀው ራሱ እግዚአብሔር ነው፡፡ «እግዚአብሔር ሙሴን እንዲህ ብሎ ተናገረው፡- ለእነዚህ በየስማቸው ቁጥር ምድሪቱ ርስት ሆና ትከፈላለች... ለሁሉ እንደቁጥራቸው መጠን ርስታቸው ይሰጣቸዋል፡፡ ነገር ግን ምድሪቱ በዕጣ ትከፈላለች፤ በብዙዎችና በጥቂቶች መካከል ርስታቸው በዕጣ ትከፈላለች»፡፡ /ዘኁ.፳፮፥፶፪-፶፮/ ይህንን ትእዛዝ እግዚአብሔር ሲያስተላልፍ ሥርዐተ ዕጣውን የሚመሩትንም ጭምር «...ርስት ትሆናችሁ ዘንድ በዕጣ የምትደርሳችሁን ምድር... የሚከፍሉላችኹ ሰዎች ስማቸው ይህ ነው፤ ካህኑ አልዓዛርና የነዌ ልጅ ኢያሱ፡፡» በማለት አሳውቋቸዋል፡፡ /ዘኁ.፴፥፱-፲፮/ በዚህ ዐቢይ ትእዛዝ መሠረት ተሿሚዎቹ በተፈጥሮ ወጣ ገባ፣ ጭንጫና ለም ወዘተ... የሆነችውን ምድር ከሐሜት በጸዳና ከአድልኦ በራቀ መለኮታዊ ሥርዓት ርስቱን አከፋፍለዋል፡፡


ከዚህም ውጪ እስራኤላውያን በዕጣ ለእግዚአብሔር የሚሠዋውን ከማይሰዋው ለይተውበታል፤ ዘሌ.፲፮፥፰፣ ንጉሣቸውን መርጠውበታል፤ ፩ኛሳሙ.፲፥፲፩-፳፩፣ ወንጀለኞችን ለይተውበታል፤ /ኢያ.፯፥፲፰ ዮና.፩፥፯/፣ ለጦር ሥራ ተጠቅመውበታል፤ /፩ኛዜና.፳፬፥፲፱ መሳ.፳፥፱-፲/፣ ንብረት ለመካፈል ተጠቅመውበታል። ማቴ.፳፯፥፴፭፣

ከብሉይ ኪዳን ጀምሮ በእግዚአብሔር ትእዛዝና ፈቃድ ሲሠራበት የቆየው ዕጣ ወደ ሐዲስ ኪዳን ዘልቆ ቤተ ክርስቲያን ትጠቀምበት እንደነበር መዛግብት ያስረዳሉ፡፡

### ዕጣና ጥቅሙ

በዕጣ መመዘኛዎቹን ተከትለን በአግባቡ መጠቀም ከቻልን በርካታ ጥቅሞች አሉት፡፡

ዕጣ የፈቃደ እግዚአብሔር ማወቂያ መንገድ ሆኖ በሐዋርያትም ዘመን አገልግሎ ነበር፡፡ ሐዋርያት ይሁዳ ረግጧት በሔደው ዕድል ፈንታ ለመተካት የራሳቸውን ዕውቀት ተጠቅመው ሁለት ሰው /ማትያስንና ዮሴፍን/ በእጩነት ካቀረቡ



*ሐዋርያት ቅዱስ ማትያስን በዕጣ እንደመረጡት የሚያሳይ*

በኋላ፤ የሚፈለገው አንድ ብቻ ነበርና «የሁሉን ልብ የምታውቅ አንተ ጌታ ሆይ ይሁዳ ወደ ገዛ ራሱ ስፍራ ይሔድ ዘንድ በተዋት በዚህች አገልግሎትና ሐዋርያነት ሥፍራን እንዲቀበል የመረጥኸውን ከእነዚህ ከሁለቱ አንዱን ሹመው» ብለው ጸለዩ፡፡ ከዚያም «ዕጣን ተጣጣሉላቸው ዕጣውም ለማትያስ ወደቀና ከዐሥራ አንዱ ሐዋርያት ጋር ተቆጠረ» /ግብ.ሐዋ.፩፥፳፫-፳፮/ ፈቃደ እግዚአብሔር በዕጣው ላይ ተገለጠ፡፡

ዕጣ ዳኛ ሆኖ ያለ አድልኦ ይፈርዳል፤ ሰው ከፈረደው ፍርድ ይልቅ በዕጣ የተገኘን ፍርድ ሰው አክብሮ ያለማጉረምረም ይቀበለዋል፡፡ እስራኤላውያን በኢያሱ አማካይነት ምድረ ርስትን ሲከፋፈሉ በዕጣ ባይሆን ኖሮ መሬት ባላት ወጥ ያልሆነ አቀማመጥ ሳቢያ የሚፈጠረው ጠብ ያስከተለውን ጉዳት እናነብ ነበር፡፡ ያ ሳይሆን የቀረው ግን ርስት የማከፋፈሉ ሥራ በፈቃደ እግዚአብሔር ላይ ተመሥርቶ በዕጣ በመሆኑ ነው፡፡

ዕጣ ሐሜትን፣ ጭቅጭቅን፣ አድልዎን፣ ከማስወገዱ በተጨማሪም አስተማማኝና አምላካዊ ውሳኔን አውቆ በእምነት ለመቀበል ያስችላል፡፡ ጌታችንና መድኃኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስ በተሰቀለ ጊዜ ሰቃልያኑ ጭፍሮች ያቺን ሰብአሰገል ለጌታ የሰጡትን ከተግባረ ዕድ ነጻ የሆነች ቅድም፣ ስፍም የሌላትን ወጥ የሆነች ቀሚስ እንዳይቀዷትም እንዳይተውአትም ሳሉተው ዕጣ ተጣጣሉ፡፡ «ጭፍሮቹም ኢየሱስን በሰቀሉት ጊዜ ልብሶቹን ወስደው ለእያንዳንዱ ጭፍራ አንድ ክፍል ሆኖ በአራት ከፋፈሉት፤ እጀ ጠባቡን ደግሞ ወሰዱ። እጀ ጠባቡም ከላይ ጀምሮ ወጥ ሆኖ የተሠራ ነበረ እንጂ የተሰፋ አልነበረም፡፡ ስለዚህ እርስ በእርሳቸው ለማን እንዲሆን በእርሱ





www.eotcmk.org

ዕጣ እንጣጣልበት እንጂ አንቅደደው ተባባሉ፡፡...» እንደተባለ፡፡ /ዮሐ.፲፱÷፳፫-፳፬/

ጭፍሮቹ ነገሮቹን በትንቢቱ /መዝ.፳፩/ መሠረት የፈጸሙት ይሁን እንጂ የዕጣውን አሠራር ባይጠቀሙ ኖሮ ቀሚሷን ሁሉም ከወደዷት ለመውሰድ ሲሞክሩ የሚፈጽሙትን ሌላ የእርስ በእርስ ጠብ ልናነብ እንችል እንደነበር መገመት አያዳግትም፡፡ ስለዚህ ዕጣ አንድ ልብ አንድ ሐሳብ ለመሆን ይሰጣል፡፡


## መንፈሳዊ የዕጣ ሥርዓት የሚኖሩት ዋና ዋና መርሖዎች

፩. በዕጣው የእግዚአብሔርን ፈቃድ ለመረዳትና ያንንም ለመቀበል ተዘጋጅተን የሚፈጸም በመሆኑ ጸሎት የዕጣ ሥርዓት ቁልፍና ዐቢይ ተግባር ነው፡፡ ብላታ ወልደጊዮርጊስ እንዲህ ይላሉ

«አሳብ እንደ አንደበት በከንፈር፣ እንደ ዐይን በቅንድብ፣ እንደዦሮ በጣት አይዘጋም፡፡ አሳብ ረቂቅ ስለሆነ የነፍሳችን እንጂ የሥጋችን ሥራ አይደለም፤ ስለዚህ በግዙፉ ሥጋችን ልናግደው አንችልም፡፡ እንዲህ ዓይነቱን ትርምስ ውስጣችን ሲያነቃ በቅድሚያ እግዚአብሔርን ሁሉ የሚቻልህ አምላኬ ሆይ የምችለውንና የምሠራውን ብቻ አሳስበኝ የተበተነውንና የሚባክነውን አሳብ ወስንልኝ ብለን እንለምነው፡፡ ከዚህ በኋላ ግን የሚ ያስጨንቃችሁን ሁሉ በእርሱ ላይ ጣሉት፡፡ ተብሏልና ተገቢውን ጸሎት ካደረጉ በኋላ አሳብን በዕጣ መቁረጥ ተገቢ ነው፡፡ /፩ጴጥ.፭÷፯/ አንዳንድ ጊዜ ሁለት በጎ አሳቦችን ስናወጣና ስናወርድ እንገኛለን፡፡ የሁለቱም አሳቦቻችን ጥቅምና ጉዳት ተካክሎ ሲታየን እግዚአብሔር በማትያስ መመረጥ ጊዜ በሐዋርያት ኀሊና እንዳ ደረገው መምረጥን ለእሱ እንድንተውለት ሲሻብን ነውና በጸሎት ለምነን በዕጣ መቁረጥ ተገቢ ነው፡፡»

፪. ከብዙ ነገሮች አንድን ነገር ለመምረጥ የሚፈጸም ሳይሆን በእኛ አቅም ለምንሻው ግልጽ ዓላማ ግልጽ መስፈርት አውጥተን ከብዙ ጥቂቶችን ከለየን በኋላ የሚያጋጥመንን ማመንታት በእርግጠኝነት ለማለፍ በመሆኑ ከሁለት ወይም ከሦስት ሰዎች ወይም ሁኔታዎች የበለጡ ነገሮችን በዕጣ መለየት ላያስፈልግ ይችላል፡፡ ይህ ካልሆነ ግን በተመረጡ ሰዎች አለማመን ብቃታቸውን መጠራጠር ወዘተ. ስለሚከተል ይህ እንደ መርኅ መያዝ የሚችል ነው፡፡ መጽሐፍም «ዕጣ ክርክርን ትከለክላለች» ይላል፡፡ መክ. ፲፰÷፲፰

፫. የዕጣ ሥርዓት በራሱ ሁልጊዜ ከአድልዎ የጸዳ ቢመስልም ከዕጣ ዝግጅትና አወጣጥ ጋር የተያያዙ ሥርዓቶችን በፍፁም ታማኝነትና ግልጽነት መፈጸም ይገባቸዋል፡፡ በዕጣው መካተት ያለባቸው ተመራጮች መካተታቸው፣ ዕጣው በምንም መሥፈርት የተለያየ ያልሆነና አንዱ ከአንዱ መለያ የሌላቸውና ለማንኛችንም



ወገኖች ወጥተው ከሚገለጥቸው በፊት ሥውር ሊሆኑ ይገባል፡፡ «ዕጣ በጉያ /በስውር/ ይጣላል፤ መደብዋ ሁሉ ግን ከእግዚአብሔር ዘንድ ነው» እንዲል፡፡ /ምሳ.፲፮÷፫/

የዕጣ አሠራር ከዚህ ሥርዓት ሲወጣ ከባሕር የወጣ ዓሣ ይሆናል

፬. ሲያወጡም ከአድልዎ ነጻ በሆኑና ሁሉም በሚያምንባቸው አካላት ሊሆን ይገባል፡፡

ብዙ ጊዜ የተጠቀለለን ዕጣ በሕፃናት ማስወጣት የተለመደ ተግባር ሆኖ ይታያል፡፡ ይህ ብቻም አይደለም፤ ሰዎች ተንኮል ባልተቀላቀለው ፍቅር እንወድሃለን ሲሉ የሚያከብሩትንና የሚወዱትን እንግዳ በሕፃናት እጅ እቅፍ አበባ በማበርከት ይቀበሉታል፡፡ ዕጣን ማንኛውም ሰው ሊያወጣው ሲችል ሕፃናት የተመረጡበት ምክንያት ግን ለሁላችንም ግልጽ ይመስለናል፡፡ ሕፃናት ንጽሐ ጠባይ ያላደፈባቸው ስለሆኑ እግዚአብሔር በእነሱ ላይ አድሮ በዕጣው አማካኝነት እንዲፈርድልን ከማሰብ የተነሣ ነው፡፡ ክብር ምስጋና ይግባውና ራሱ ጌታችንና መድኃኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስ «ካል ተመለሳችሁ እንደ ሕፃናትም ካልሆናችሁ ኩዎ ወደ መንግሥተ ሰማያት ትገቡ ዘንድ አትችሉም» /ማቴ.፲፰÷፫/ በማለት እንደሕፃናቱ ኀዳጌ በቀል፣ የዋሕ፣ ንጹሕና ታማኝ እንድንሆን ይመክረናል፡፡ በየዓመቱ ሚያዝያ ፫ ቀን በዓለ ዕረፍቱ የሚታሰብለትና በአንድ ወቅት የእስክንድርያ ቤተ ክርስቲያን ሊቀ ጳጳስ የነበረው አባ ሚካኤል በስንክሳር መጽሐፍ የሰፈረው ታሪኩ የዕጣና ሕፃናትን አንድነት ያስረዳናል፡፡

*አባ ሚካኤል ከታናሽነቱ ጀምሮ በገዳመ አስቄጥስ በአባ መቃርስ ቤተ ክርስቲያን መንኵሶ በተጋድሎ የኖረ አባት ነው፡፡ ከእርሱ በፊት የነበረው ሊቀ ጳጳስ አባ ገብርኤል ሲያርፍ የቅዱስ ማርቆስ መንበር ለ፬ ወር ባዶ ሆኖ ቆየ፡፡ ሊቃውንት አባቶች በመንበሩ ላይ የሚተካ ሰው ከየገዳማቱ በመምረጥ ብዙ ከደከሙ በኋላ ሦስት ገዳማውያን አባቶችን በእጩነት አቀረቡ፡፡ ከዛም የሦስቱንም ስም በክርታስ /ወረቀት/ ጽፈው በመሠውያው /ታቦቱ/ ላይ ካኖሩ በኋላ ለሦስት ቀን እየጸለዩና ቅዳሴ እየቀደሱ እግዚአብሔር የወደደውን ያደርግ ዘንድ በመማለድ ቆዩ፡፡ ከሦስቱ ቀናት በኋላ አንድ ታናሽ ብላቴና ጠርተው ከእነዚህ ከሦስቱ ስሞች አንዱን አንሥተህ ስጠን አሉት፡፡ ያም ብላቴና የአባ ሚካኤል ስም ያለበትን ክርታስ አንሥቶ ሰጣቸው፡፡ ሁሉም እግዚአብሔር እንደመረጠው አውቀው ይገባዋል ብለው ሊቀጽጽስና ሾሙት፡፡ ይለናል፡፡*

## ዕጣና ውጤቱ

ዕጣ የጣልንበት አሳብ በዕጣው ሲገለጥ ውጤቱ እኛ የጠበቅነውም ያልተቀበልነውም ሊሆን ይችላል፡፡ እግዚአብሔር ሁልጊዜም ትክክል መሆኑን ካመንን ምንም ይሁን ምን ውጤቱን መቀበል ግዴታችን ነው፡፡ ለዕጣ የምናቀርበው አሳብ ወይም ሥራ በጎ ከሆነና እንደ ሐዋርያት በጸሎትና በተገቢው ሥርዓት የተደገፈ ሲሆን

ብዙ ጊዜ የተጠቀለለን ዕጣ በሕፃናት ማስወጣት የተለመደ ተግባር ሆኖ ይታያል፡፡ ... ሕፃናት ንጽሐ ጠባይ ያላደፈባቸው ስለሆኑ እግዚአብሔር በእነሱ ላይ አድሮ በዕጣው አማካኝነት እንዲፈርድልን ከማሰብ የተነሣ ነው፡፡





www.eotcmk.org

> **በዕጣው የእግዚአብሔርን ፈቃድ ለመረዳትና ያንንም ለመቀበል ተዘጋጅተን የሚፈጸም በመሆኑ ጸሎት የዕጣ ሥርዓት ቁልፍና ዐቢይ ተግባር ነው።**

እግዚአብሔር በዕጣው ውስጥ ተምኔታችንን ይፈጽምልናል።

የእስክንድርያ ቤተ ክርስቲያን ፓትርያርክ ምርጫ እስካሁን ድረስ የዕጣ ሥርዓቱን አልተወም። የሕዝብ ድምፅ የሚሰጠው ከዕጣ በፊት ነው። በሐዋርያት ቀኖና እንደተገለጸው ለከፍተኛ የክህነት መዓርግ የሚታጭ ሰው ሁሉ ከሕዝቡ ይሁንታ ማግኘት አለበት። በዚሁ መሠረት ለፓትርያርክነት የሚታጩትን ሦስት ሰዎች ለመምረጥ ከአባቶች ጀምሮ ምእመናኑ ሁሉ ድምፅ ይሰጣሉ። በዚሁ መሠረት ከአንደኛ እስከ ሦስተኛ የወጡት አባቶች ይለያሉ። ከዚህ በኋላ ግን የሦስቱም ስም ይጻፍና ሥርዓተ ሲሙቱ በሚፈጸምበት ቤተ ክርስቲያን መንበር ላይ ተደርጎ ሁለት ሱባኤ /ለ፲፬ ቀናት/ ሁሉም ሲጸልዩ ይሰነብታሉ። በአሥራ አራተኛው ቀን በዕለተ እሑድ ጸሎተ ቅዳሴው ከተጠናቀቀ በኋላ በዓይነ ስውር ሰው ወይም ለዚሁ በተዘጋጀ ሰው ዕጣው ይወጣል፤ በዕጣው የተመረጠው ሰው ፓትርያርክ ይሆናል፤ ሕዝቡም ይደልዎ ብለው ይቀበሉታል።

አሁን በፓትርክና መንበር ላይ ያሉት የእስክንድርያው ቤተ ክርስቲያን ፓትርያርክ ብፁዕ ወቅዱስ አቡነ ሽኖዳ ሣልሳዊ ከሌሎች ሁለት አባቶች ጋር ለዚህ ታላቅ ሰማያዊ ሥልጣን ሲታጩ የግብጽ ምዕመናንም ይሁኑ ሊቃነ ጳጳሳቱ ሁሉም ማለት ይቻላል አቡነ ሽኖዳ ከምእመናን ጋር ከነበራቸው ሰፊ ግንኙነት አንጻር ፓትርያርክ እንዲሆኑላቸው ቀድመው (ቢመኙም) በዕጣ የመለየቱ ሥርዓት . ብጽ ቤተ ክርስቲያን የተቀመጠ ግዴታ ስለሆነ ተገቢው ሥርዓተ ጸሎት ደርሶ እግዚአብሔር የወደደውን ያደርግ ዘንድ ዕጣው እንደተጣለ ይታወቃል።

በጣም የሚገርመው የሁሉም ምኞት የተሳካና ዕጣው የአቡነ ሽኖዳን ስም ይዞ ብቅ አለ። እግዚአብሔር በዕጣው ላይ ፈርዶ የልጆቹን የልቡናቸውን መልካም መሻት ፈጸመ። የግብጽ ቤተ ክርስቲያን ምእመናንም ሆነ ሊቃነ ጳጳሳቱ የእግዚአብሔርን ምርጫ በምስጋና ተቀበሉት። ውጤቱ ካሰቡትና ከተመኙት በተቃራኒው እንኳን ቢሆን መቀበል ግን ግዴታቸው ነው።

አንዳንድ ሰው ዕጣውን ለመጣል ይቸኩላል እንጂ ለዕጣው አጣጣል ካለመጠንቀቁም ሌላ ውጤቱን በጸጋ መቀበል እያቃተው ይሰነካከላል። ተገቢውን ሥርዓት ፈጽመን እግዚአብሔር በዕጣው እንዲፈርድ ድርሻ ሰጥተነው ስናበቃ በዕጣ በቆረጥነው አሳብና ተግባር ክፉ ቢያገኘን የእግዚአብሔር ፍርድ መሆኑን አውቀን፣ በጎም ቢያገኘን እሱን አመስግነን በጸጋ መቀበል እንጂ ምኞታችንና የዕጣው ፍርድ በመለያየቱ ከተማረርን ወደ ዕጣው ሥርዓት ከመግባታችን በፊት ያስጨንቁን ከነበሩት መንታ ሐሳቦችና ወደዕጣ እንድንገባ ምክንያት ከሆነን ተግባር ይልቅ ይህ ምሬታችን ብርቱ ፈተና ሆኖን ከእግዚአብሔር እቅፍ ሊያወጣን ይችላል። ስለዚህ ከዚህ የከፋ እንዳያገኘን «ምርሐኒ ፍኖተ እግዚኦ እንተ ባቲ አሐውር» /አቤቱ የምሔድባትን መንገድ አንተ ምራኝ/ እያልን ቆራጥ ልቡናን ከፈጣሪ መለመን አለብን።

## የማይገባ ዕጣ

በምንኖርባት ዓለም ለሰዎች ልጆች የተፈጠሩትንና የሚሆኑትን ስናስብ ለመልካም እንጂ አንድም ለጥፋት የሆነና የሚሆን የለም። /ዘፍ.፩÷፴፣፲፮፣፲፱፣፳፩፣፳፫፣ ፴፩/ ሁሉም ለመልካም ቢፈጠርም ቅሉ በአግባቡና በሥርዓቱ ስለማንጠቀምበት አንጻራዊ በሆነ መልኩ መልካሙ መጥፎ፣ ጠቃሚው ጐጂ፣ ለጽድቅ የሆነው ለኃጢአት ሲሆንብንና ስናደርገው ይታያል። «በጨለማ ለሚኖሩት ብርሃን ወጣላቸው» ተብሎ የተነገረለት ጌታ አይሁድ ባለማወቃቸው ምክንያት «የሚያዩ እንዲታወሩ፤ የማያዩ እንዲያዩ መጥቻለሁ» ብሎ ሲናገር እናነባለን።

እንደዚሁም ሥርዓተ ዕጣ ጥቅም እንዳለው ሁሉ ጉዳትም እንዳለው ልናውቅ ያስፈልጋል። እንዲያውም ዕጣ በተሳሳተ መንገድ እየተፈጸመ በማየታቸው ብቻ አብዝተው የሚናገሩት የዕጣን አላስፈላጊነት ነው። በጥቅሉ ዕጣ አያስፈልግም ተብሎ መደምደም ባያስኬድም ስለማይገቡ ዕጣዎች ገልጦ ማስረዳት ግን ግድ ነው።

ዕጣ አውጭው ጠንቋይ፣ ዕጣው የጠንቋይ ጠጠር ሲሆን ጉጂም ኃጢአትም ነው። ቀደም ሲል በገጠሩ አሁን አሁን ግን በሚያሳዝን መልኩ በየከተሞቻችን ሰዎች ለትዳር የፈለጉትን አጋር ወደ ጠንቋይ ቤት ተጉዘው «ዕጣ ክፍሌ ማን ነው?» በማለት ለማግኘት ሲሞክሩና ሚስት ወይም ባል ሽ ዕጣ ክፍልህ /ሽ/ አይደለም /ችም/ እየተባሉ ትዳራቸውን ፈተው ልጆቻቸውን ሲበትኑ እያስተዋልን ነው። «ዕጣ»ን ለተቀደሰ ዓላማ እንጂ ለክፋት ለማዋል መሞከርም አደጋው ከፍ ያለ ነው።

ሌላው የማይገባ ዕጣ ደግሞ ከክፉ ዓላማ ተነሥተን ክፉንም ለመፈጸም ስንጠቀምበት ነው። ክፉ ማለትም ሕገ-እግዚአብሔር ለሚያስጥሰን ለየትኛው ተግባር ማለታችን ነው።

ይህንንም ከንጉሥ አርጤክስስ ከፍተኛ ባለሥልጣን ከሐማ ውድቀት መማር ይቻላል። ሐማ መርዶክዮስ ለምን እግሬ ሥር ወድቆ እጅ አልነሳኝም በሚል ከንቱ ስሜት ተነሥቶ በመቶ ሃያ ሰባት ሀገሮች የሚኖሩ አይሁዳውያንን በጅምላ ለማስ ጨፍጨፍ የትኛው ጊዜና ወቅት ምቹ እንደሆነ ያውቅ ዘንድ በቤተ መንግሥቱ ዕጣ አስጥሎ ነበር። «ሐማ. በአርጤክስ መንግሥት የነበሩትን... አይሁድን ሁሉ ሊያጠፋ ፈለገ።... ከመጀመሪያው ወር ከኒሳን ጀምሮ በየዕለቱና በየወሩ እስከ ዐሥራ ሁለተኛው ወር እስከ አዳር ድረስ በሐማ ፊት ፉር የተባለውን ዕጣ /በአገራችን እንደጠጠር ጣይ የምንለው ዓይነት ማለት ነው/ ይጥሉ ነበር።» /መጽ. አስ.፫÷፮-፯/ ዳሩ ግን ሥርዓተ ዕጣው ከመነሻው የተበላሸና ዓላማው እግዚአብሔር የማይወደው ስለነበረ ውጤቱ ከፍቶ ሐማን በግንድ ላይ አሰቅሎ ተደመደመ። ሐማ የቤተ መንግሥቱን አዋቂዎች ሰብስቦ ዕጣ ሲያስጥል የነበረው አይሁድን በጅምላ ለመጨፍጨፍ የሚያስችለውን ጊዜ በመፈለግ መሆኑ ከላይ ተገልጧል።

## ማጠቃለያ

ዕጣ ውሳኔ ለሚያስፈልገው ለሁሉም ነገር የምንጠቀምበት ሥርዓት አይደለም። ለታወቀና ግልጽ ለሆነ ነገር ላን ጠቀም እንችላለን። አንጥረን ለለየናቸው በደረጃ እኩል ለሆኑ ለምናመነታባቸው ጉዳዮች ብንጠቀም ተገቢ ነው። ወይም በሥርዓት ተደንግጐ የሆነውን ደረጃ እኛ ካከናወነው በኋላ ቀሪውን እግዚአብሔር እንዲገባበት ስንሻ ተግባራዊ የም ናደርገው ይሆናል። ወይም ውሳኔያችን ክርክርና ፍቅር ማጣትን የሚያስከትል ከሆነ በዕጣ እናስማማዋለን። ከላይ በዝር ዝር እንዳየነው ዕጣ በፈቃደ እግዚአብሔር ለሰዎች የተሰጠ የዳኝነት ሥርዓትና የመንታ ልብ መቁረጫ መሣሪያ ከሆነ በሃይማኖታዊውም ሆነ በማኅበራዊው ሕይወታችን ለበጎ ዓላማ ብንጠቀምበት መልካም ነው። የዕጣ ሥርዓት በዓውደ ዓመት ጊዜ የቅርጫን ሥጋ ለመከፋፈልና ለዕቁብ ቤት አንዳንዴም የሰንበትት/ቤቶቻችን በየዓውደ ምሕረቱ ከሚጠቀሙበት የገቢ ማስገኛ ባለፈ መልኩ ለተለያዩ የቤተ ክርስቲያን ዓላማዎች በሐዋርያት ዘመን ይደረግ እንደነበረው ከብርቱ ጸሎትና ምልጃ ጋር ቢተገበር መልካም ነው። በነቢያትና በሐዋርያት የነበረውን ሥርዓትና ለረጅም ዘመንም በሀገራችን የነበረውን ትውፊት ከማስጠበቅ አንጻር በአፈጻጸም ክፍተት ሊኖርባቸው በሚችሉ አሠራሮቻችን ውስጥ ሁሉ ሥራ ላይ እንዲውል ሐዋርያት በሚታሰቡበት በዚህ ወቅት ለመጠቆም እንወዳለን።

✦





'

www.eotcmk.org

# በእንተ ክብሮሙ ካህናት

ስለ ሕዝቡ ትእዛዝ ካህናቱን ያከብሩ ዘንድ ካህናቱም ይመስሏቸው ዘንድ የሚገባውን ከነርሱም ጋር የሚያደርጉትን ይናገራል።

ከሌዋውያን ወገን ያይደለ ባዕድ ምንምን መሸከም እንደማይቻለው ወይም ከካህኑ በቀር ምንምን ወደቤተ መቅደሱ ያገባ ዘንድ እንደማይቻለው እናንተም እንደዚሁ ያለ ኤጲስቆጶሱ ፈቃድ ምንም አትሥሩ። እንደዚህ ካልሆነ ግን ከንቱ ይሆናል። አያምርም ሳይገባቸው የክህነትን ሥራ እንደሠሩ እንደ ያዝያንና እንደ ሳኦል፤ ያዝያን ካህን ስለ ኃጢአቱ በለምጽ ዝንጉርጉር የሆነ አይደለምን? እንዲሁም ሕዝባዊ ሁሉ ከቅጣት አይድንም እርሱ እግዚአብሔር ንቆታልና በክህነት ላይ ተደፋፍሮ ለራሱ ይህችን ክብር ተቀበለ። ሊቀ ካህናት ይሆን ዘንድ ራሱን ፈጽሞ ያላመሰገነ ክርስቶስንም አልመሰለውም። «እንደ መልከጼዴቅ ሹመት የዓለሙ አገልጋይ አንተ ነህ ሲል እግዚአብሔር ማለት አልተመለሰምም ሲል አብን እስኪሰማው ድረስ ታገሠ እንጂ» /ዕብ.፭፥፭-፮/ ክርስቶስንም ከርሱ ጋር የተካከለ ሲሆን ያባባቱ ብቻውን ያልተመሰገነ ከሆነ እርሱም በሥራው ሁሉ ከርሱ ጋር አንድ ነው። አንዱስ እንኳ ከርሱ ከሚበልጠው ይህንን መዓርግ ሳይቀበል ለራሱ ክህነትን ይቀበል ዘንድ እንዴት ይቻለዋል? እነርሱ የሌዊ ወገን ሲሆኑ ሙሴንና አሮንን በተቃወሟቸው ጊዜ የማይገባቸውንም በዳሰሱ ጊዜ የቆሬን ልጆች እሳት አላቃጠላቸውምን!

አጋንንትን የሚያገለግሉ ከወገኖቻቸው የሚከብሩ ከሆነ፤ ይኸችውም ዘበት ናት፤ ከካህኑ በቀር ምንም ሥራቸውን የማይጨርሱ ከሆነ እነዚህ ድንጋዮች አንደበት ያላቸው ይመስላቸዋል፤ የሚያዝዛቸውን ሁሉ እሱን ይሰሙታል። ይሠራሉም። ነፍስ የሌለው የጣዖት ክብሩ የከበረች እንደሆነች ያያሉ። የተረዳች ሃይማኖት የከበረች አለኝታ ያለፍርሃት ምስጋናን የተመላች የዘለዓለም ዋጋ ደጅ ጥናት ያለን እኛማ አስቀድመን አምላካችንን እግዚአብሔርን ቀጥሎ ካህናቱን ማክበር እንዴት አይገባንም? እነርሱም የእግዚአብሔር አፍ እንደሆኑ ስለ ኤጲስቆጶሳት እናስብ።

የሙሴ ወንድም አሮን ሙሴን በነገር በረዳው ጊዜ ነቢይ የተባለ ከሆነ ሙሴም የፈርዖን አምላክ ተባለ ይኸውም እንደናንተ በአንድነት ንጉሥ ሊቀ ካህናት የተባለው ነው። እግዚአብሔር እርሱን እኔ የፈርዖን አምላክ አደረግሁህ እንዳለው ሰምታችኋል ወንድምህ አሮንም ለአንተ ነቢይ ይሁንህ ስለነገር የሚያስታርቋችሁ ነቢያት እንደሆኑ ለምን አታስቡም የእግዚአብሔርም አገልጋዮች እንደመ

በአሮን ቦታ አለላችሁ። ኤጲቆጶሱም በሙሴ አምሳል እግዚአብሔር «አምላክ» ብሎ የጠራው ከሆነ እናንተም ዳግመኛ ኤጲስቆጶሱን እንደአምላክ፤ ዲያቆኑንም በነቢዩ አምሳል አክብሩት።

> በኤጲስቆጶሱ ላይ ክፉ ቃል የሚናገር እነሆ እግዚአብሔርን በደለ። እግዚአብሔር በአማልክት ላይ ክፉ ነገር አትናገሩ ያለውን አልሰማችሁምን? ስለ ጣዖታቱ ይህ ትእዛዝ የተባለ አይምሰልህ። ስለካህናትና ስለዳኞች ስለእነርሱ የተባለ ነው እንጂ «እናንተም ሁላችሁ አማልክትና የልዑል ልጆች ትባላላችሁ» /መዝ.፹፩፥፮/ እንዳለ።

በኤጲስቆጶሱ ላይ ክፉ ቃል የሚናገር እነሆ እግዚአብሔርን በደለ። እግዚአብሔር በአማልክት ላይ ክፉ ነገር አትናገሩ ያለውን አልሰማችሁምን? ስለ ጣዖታቱ ይህ ትእዛዝ የተባለ አይምሰልህ። ስለካህናትና ስለዳኞች ስለእነርሱ የተባለ ነው እንጂ «እናንተም ሁላችሁ አማልክትና የልዑል ልጆች ትባላላችሁ»። /መዝ.፹፩፥፮/ ዳግመኛም ሙሴ የሚቋቋሙትን ሕዝብ በእኔ ላይ የምታንጎራጉሩ አይደላችሁም፤ በእግዚአብሔር አምላክ ላይ ታንጎራጉራላችሁ እንጂ። /ዘኁ.፲፮፥፲፩/። አላቸው። ሕዝባዊውን /ጨዋውን/ አንተ ስሱ ወይም አንተ ሰነፍ የሚለው ከቅጣት የማይድን ከሆነ ይህ ተግዳሮት በክርስቶስ ላይ ነውና በአንብሮተ እድ እግዚአብሔር መንፈስ ቅዱስን በሰጣችሁ በኤጲስ ቆጶሱ ላይማ ይህን ቃል የተናገረ እንዴት ይሆን!

ልጄ ሆይ የእግዚአብሔርን ቃል የነገረህንና ለሕይወት ምክንያት የሆነህን ከፊትህ ላብና ከእጅህ ድካም ባገኘኸውና በኃይልህ ሁሉ እንደ እግዚአብሔር አክብረው /ርዳው/ እነሆ እግዚአብሔር ሥጋዊንና መንፈሳዊውን ምግብ የዘለዓለምን ሕይወት ከርሱ እንድትቀበል ዝግጁ ካደረገህ አንተም ፈጽሞ ጠፊውንና መናዊውን ምግብ ትሰጠው ዘንድ ይገባሃል። እነሆ ለሚያገለግል ዋጋው እንደሚገባው ተጽፎልናል። ዳግመኛም እህል በምታበራይበት ጊዜ የበሬውን አፍ አትለጉመው አለ። አንዱስ እንኳ ወይን ተክሎ ፍሬውን የማይበላ የለም። ከክህነት ሥራ ወገን ከሕዝባውያን ወገን ለአንዱ ይሠራ ዘንድ ምንም አናዝዝም። ይኸውም ሥጋውንና ደሙን ማቀበል፣ የክርስትና ጥምቀት ማጥመቅ ለታላቅም ሆነ ለታናሽ ለክህነት ሹመት እጅን መጫን ነው።

ስለ ካህኑ ይሰነካከል ዘንድ አንዱስ እንኳ አይገባውም። ከአለቃውም በቀር ይቀጣው ዘንድ አይገባውም። መጽሐፍ ግን ያስረዳል። ካህን ባኗኗሩ በጎ ቢሆን በስምምነት ሊያከብሩትና ሊታዘዙለት እንጂ ሊቀጡት አይገባምና። በአካሄዱ ክፉ ቢሆን በደሉም ቢታወቅ በዚህም ቢፀና ሕጉ እንደሚያዝዘው ፍርድ በርሱ ላይ ይፈርዱ ዘንድ ለሊቃውንት ይገባል። ለሕዝቡ ግን ስለዚህ ካህን ምሳሌ የጌታችን ትምህርት አላቸው። «በሙሴ ወንበር ላይ ጸሐፍት ፈሪሳውያን ተቀመጡ፤ የሚሏችሁን ሁሉ ጠብቁ ሥሩም እንጂ እንደ ሥራቸው ያለውን ግን አትሥሩ» /ማቴ.፳፫፥፪-፫/። በደሉ ባይገለጽ ግን በርሷም መጽናትን ባይጸና ሊሽሩት አይገባም የሚቀጣውም የገደል ትሩፋት ባለቤት ቢሆን «እንዳይፈረድባችሁ አትፍረዱ» /ማቴ.፯፥፩/። ካለው ከጌታችን ቃል የተ

እናንተ እንዳትበድሉ የተጠበቃችሁ ሁኑ» /ገላ.፮፥፪/:: ዳግመኛም «የአንተ ያይደለውን ባሪያ የምትነቅፈው አንተ ምንድን ነህ? አለ ቢቆም ወይም ቢወድቅ ለጌታው ነው:: ወንድምህን አትፍረድበት፤ አታቃለውም፤ እኛ ግን ሁላችን በክርስቶስ ዙፋን ፊት እንቆም ዘንድ አለን:: ከእኛ ወገን ሁሉም እያንዳንዱ ስለ ሰውነቱ መልስ ይሰጣል» ሮሜ. ፲፬፥፬-፲፭/

ዛሬም ከዚህ በኋላ እርስ በርሳችን አንፈራረድ በሥራው እንመስለዋለንና ዳግመኛም «በፈረዳችሁበት ይፈረድባችኋል በሠፈራችሁት ይሠፍሩላችኋል» /ማቴ. ፯፥፪-፮/:: ባለው በጌታችን ትምህርት እንመከር:: «በዓይንህ ውስጥ ያለውን ጉድፍ ሳታይ በወንድምህ ዓይን ውስጥ ያለው ጉድፍ ለምን ታያለህ? አንተ ግብዝ አስቀድመህ የዓይንህን ጉድፍ አውጣ:: ከዚህ በኋላ የወንድምህን ዓይን ጉድፍ ለማውጣት ታያለህ» /ማቴ.፯፥፲-፯/:: ሐዋርያው ጳውሎስ «ሰው ሆይ ወንድምህን የምትነቅፍበት ምክንያት የለህም አለ:: አንተ ወንድምህን በምትፈርድበት ገንዘብ ሰውነትህን ትፈርድበታለህና፤ ታስነቅፋትም አለህ:: ሰው ሆይ አንተ የምትሠራውን ይህችን ክፋት የሚያደርጉትን በምትፈርድባቸው ጊዜ ምን ይመስልሃል? ከእግዚአብሔር ፍርድ ማምለጥ ትችላለህን?»:: /ሮሜ. ፪፥፩-፬/

ልባዊ ፍርድም ይህ ነው አምላካዊት የምትሆን ሥልጣን ክህነት በካህኑ ልብ ውስጥ ትኖራለችና ልቡናውም ይበራባታልና ለዘለዓለሙ ያይደለ ለሕዝቡ ጥቅም መጨረሻ ከሾመው ወገን በርሷ እግዚአብሔር ያጸናዋልና ይህችውን ሕዝቡን ለመጥቀም በእጁም ለመርዳት ነው:: ራሱንና ሕዝቡን በአንድነት ለመጥቀም ክህነትን መስጠት የሚያሻ ከሆነ እንግዲህ አልቀረም:: ስለራሱና ስለ ሕዝቡ በሚገባ ሥራ ጸንቶ የሚሠራ ቢሆን፤ ስለፍጻሜውም በደል ባይኖር አስቀድሞ ስለራሱና ስለ ሕዝቡ እጥፍ ድርብ ዋጋ ይገባዋል:: በሚገባ የንስሐውን ቀኖና ባይፈጽም ግን ሰውነቱንም ከክህነት ቢለይ በሰውነቱ ስለሕዝቡም እጥፍ ድርብ ቅጣት ይገባዋል::

**ዐዴ ሆይ የእግዚአብሔርን ቃል የነገረህንና ለሕይወት ምክንያት የሆነህን ከፊትህ ባብና ከእጅህ ድካም ባገኘኸውና በኃይልህ ሁሉ እንደ እግዚአብሔር አክብረው /ርዳው/፤ እነሆ እግዚአብሔር ሥጋዊንና መንፈሳዊውን ምግብ የዘለዓለምን ሕይወት ከርሱ እንድትቀበል ዝግጁ ካደረገህ አንተም ፈጽሞ ጠፊውንና መናዊውን ምግብ ትሰጠው ዘንድ ይገባሃል::**

በሰውነቱ ላይ በደል የሌለበት ሰው ስለ ሕዝቡ ቅጣት ይገባዋል:: የጌታውን ወርቅ እንደቀበረ ባርያ በሰጡት ገንዘብ ስላልሠራበት እርሱ ተፈርዶበታልና:: ፈጽሞ ያላጠፋት ቢሆን ግን ስለ ራሱ ያይደለ ስለ ሕዝቡ ነው እንጂ ስለ ራሱ ብቻ የቅጣት ነጋ ይገባዋል:: በሕዝቡ ምክንያት ዕዳ የለበትም በርሱም ምክንያት በሕዝቡ ላይ ዕዳ የለባቸውም::

ነባቤ መለኮት ጎርጎርዮስ ስለ ጥምቀት በሚናገረው በአራተኛው ድርሳኑ እነሆ ክፉውንና በጎውን ሰው በሰምዐ ከነርሱ ካህናትን በሁለት ማኅተም መስሎ ተናገረ:: ከእነርሱ አንዱ የወርቅ ሁለተኛው የብረት ሆኖ በውስጣቸው የአንድ ንጉሥ መልክ የተቀረጸባቸው ናቸው:: ስምዕ በታተመባቸውም ጊዜ የንጉሣዊውን ቅርጽ በማስገኘት በወርቅ ማኅተም በታተመው መካከል ልዩነት የለም:: በኋላ ጊዜ በብረት ከታተመው ተለይቶ በወርቅ የታተመው አይታወቅም ነገር ግን መለያየትስ የሚያትሙበትን በሚቀበለውና በማይቀበለው መካከል ነው:: ለሥራ ግን በቅርፁ ልዩነት የለም:: ዳግመኛ ምግባር የጎደለው ካህን እንደሰም መብራት ነው:: የሚነደው እሳት በክህነቱ ይመሰላል:: እሳቱም ሰሙን ያቀልጠዋል ለሕዝቡ ግን ያበራል ከብርሃኗ የተነሣ ጨለማ አያገኛቸውም::

ስለዚህች ትርጓሜ ከሁለት ሰዎች ሌላ ምሳሌ እናምጣ አንዱ ደግ፣ አንዱ ክፉ ነው:: ሁለቱ ከንጉሡ ዘንድ ፈቃድ አላቸው፤ ፈቃዳቸውም አንድ ነው:: ለንጉሡም ሁለት መኳንንት አሉት አንዱ ደግ አንዱ ክፉ ነው:: ደጉ ሰው ከንጉሡ ፈቃዱን ይፈጽምለት ዘንድ ክፉውን ዳኛ ማለደው:: ክፉውም ሰው እንደዚሁ ፈቃዱን ይፈጽምለት ዘንድ ደጉን ዳኛ ማለደው:: ንጉሡ ግን አዋቂ ነው:: የሁለቱንም መኳንንት ሥራቸውን ያውቃል:: መኳንንቱ ስለ ግዳጃቸው ንጉሡን በማለዱት ጊዜ የደገኛውን ፈቃድ በክፉው ዳኛ እጅ ጨረሰ:: የዳኛው ክፋት ፈቃዱን አልከለከለበትም:: የክፉውን ፈቃድ በደጉ ዳኛ እጅ አልጨረሰም ስለርሱ ክፋት የዳኛው ደግነት አልጠቀመውም:: ቢቀበልና ቢጠቀምም እንጃ እግዚአብሔር ያውቃል::✥

*ከፍትሐ ነገሥት አንቀጽ ፲ የተወሰደ*


## በስመ አብ ወወልድ ወመንፈስ ቅዱስ አሐዱ አምላክ አሜን

***በተሰጠን መክሊት እናትርፍ ማቴ 25፥18***

በገጠራቱ የአገራችን ክፍሎች የሚገኙት ክርስቲያኖች ቅዱሳት መጻሕፍትን እና የኅትመት ውጤቶችን መምህራን-ወንጌል በማድረግ በሚያገኙት ትምህርት ራሳቸውን ከነጣቂ ተኩላ ይጠብቃሉ፤ ሥርዓተ ቤተክርስቲያንን ይማራሉ ያስተምራሉ፤ ወቅታዊ የቤተክርስቲያን መረጃዎችንም ያገኛሉ::

ነገር ግን እነዚህን ኅትመቶች ለማግኘት የገንዘብ አቅማቸው አነስተኛ ከመሆኑም ባሻገር ኅትመቶችን የሚያገኙባቸው አጋጣሚዎችም የጠበቡ ናቸው በመሆኑም በማኅበረ ቅዱሳን ልማት ተቋማት አስተዳደር በተለያየ ወቅት የታተሙ ስምዐ ጽድቅ ጋዜጦችን ለእነዚህ ገዳማትና አድባራት በቅናሽ ዋጋ ለማዳረስ በማሰብ ስፖንሰሮችን ይፈልጋል::

| ተ.ቁ | የስምዐ ጽድቅ ብዛት | የገንዘብ መጠን | ተጠቃሚ ሊሆኑ የሚችሉ ገዳማት ብዛት |
|---|---|---|---|
| 1 | 500 | 175.00 | 10 |
| 2 | 1000 | 350.00 | 20 |
| 3 | 2000 | 700.00 | 40 |
| 4 | 3500 | 1225.00 | 70 |
| 5 | 5000 | 1750.00 | 100 |
| 6 | 7500 | 2625.00 | 150 |
| 7 | 10000 | 3500.00 | 200 |

ለማን መስጠት እንዳለብዎት የሚያውቁ ከሆነ አድራሻ ይስጡን ካልሆነ ግን "ለማን እና እንዴት መላክ ይቻላል?" ብለው አይጨነቁ:: ሙሉ ኃላፊነቱን ወስደን የሚፈልጉት ቦታ ላይ እናደርሳለን::

*ማስታወሻ፤*

ለአንድ ገዳም ቢያንስ 50 ስምዐ ጽድቅ ጋዜጣ ቢደርሰው ተብሎ ታሳቢ ተደርጓል::


በመሆኑም በዚህ የተቀደሰ ዓላማ በመሳተፍ እነዚህን ገዳማት መርዳት የምትችሉ ምዕመናን ሁሉ፡-

*በስልክ ቁጥር 011 124 61 81/82/84 ወይም*
*ሞባይል 0911 71 30 96*
*ፖ.ሳ.ቁ 800*

# ጋብቻ

የሰው ዓለም ሦስት ነው፤ መገርመሪያ ዓለም ሚስት፣ ኹለተኛ ዓለም ልጆች፤ ሦስተኛ ዓለም ወዳጅ ናቸው:: ነገር ግን፤ የመዠመሪያው ዓለም የጸና ከኾነ፣ የቀረው ዓለም ትርፍ ነው:: ቢቀርም አያስጎዳም:: ባልና ሚስት በሞት የተለያዩ እንደ ኾነ ግን፣ ጭራሽ የሰው ጉዳቱ ያን ጊዜ ነው:: እኽል ቢበሉት አይጣፍጥም፤ ልብሱ ቢለብሱት አይሞቅም፤ ቤቱ ቢያስጌጡት አይደምቅም፤ ይልቁንም ባንድ ልብ ኾነው ሥጋ ወደሙ የተቀበሉ፤ ነዳያንን፣ እንግዶችን፣ እስረኞችን በሽተኞችን ያገለገሉ የኾኑ እንደ ኾነ፣ የነዚህ በሞት መለያየት እጅግ ያሳዝናል:: አዳምም አለ:: አኹን ይህች ዐፅንት ካፅንቴ ናት፤ ሥጋም ከሥጋዬ ናት፤ ይህች ሴት ትባል፤ ከወንድ ተገኝታለችና:: ስለዚህ ሰው አባትና እናቱን ይተዋል፤ ሚስቱን ይከተላል፤ ኹለቱም አንድ ሥጋ ይኾናሉ:: /ዘፍጥ.፪:፳፫-፳፬/ እግዚአብሔር አንድ ያደረገውን ሰው አይለየው:: /ማቴ.፲፱:፮/ ...





ልባም ሴትን ማን ሊያገኛት ይችላል? ዋጋዋ ከቀይ ዕንቍ እጅግ ይበልጣል:: የባልዋ ልብ ይታመንባታል÷ ምርኮም አይጐድልበትም:: ዕድሜዋን ሙሉ መልካም ታደርግለታለች÷ ክፉም አታደርግም:: የበግ ጠጕርና የተልባ እግር ትፈልጋለች÷ በእጆችዋም ደስ ብሎአት ትሠራለች:: እርስዋ እንደ ነጋዴ መርከብ ናት፤ ከሩቅ አገር ምግብዋን ትሰበስባለች:: ገና ሌሊት ሳለ ትነሣለች ለቤትዋም ሰዎች ምግባቸውን÷ ለገረዶችዋም ተግባራቸውን ትሰጣለች:: እርሻንም ተመልክታ ትገዛለች፤ ከእ ጅዋም ፍሬ ወይን ትተክላለች:: ወገብዋን በኃይል ትታጠቃለች÷ ክንድዋንም ታበረታለች:: ንግድዋ መልካም እንደ ሆነ ትመለከታለች፤ መብራትዋ በሌሊት አይጠፋም:: እጅዋን ወደ አመልማሎ ትዘረጋለች÷ ጣቶችዋም እንዝርትን ይይዛሉ:: እጅዋን ወደ ድሀ ትዘርጋለች÷ ወደ ችግረኛም እጅዋን ትሰ ድዳለች:: ለቤትዋ ሰዎች ከበረዶ ብርድ የተ ነሣ አትፈራም÷ የቤትዋ ሰዎች ሁሉ እጥፍ ድርብ የለበሱ ናቸውና:: ለራስዋም ግብረ መርፌ ስጋጃ ትሠራለች፤ ጥሩ በፍታና ቀይ ግምጃ ትለብሳለች:: ባልዋ በአገር ሽማግሌ ዎች መካከል በሸንጎ በተቀመጠ ጊዜ በበር የታወቀ ይሆናል:: የበፍታ ቀሚስ እየሠራች ትሸጣለች፤ ለነጋዴም ድግ ትሸጣለች:: ብርታትና ክበሬታ ልብስዋ ነው፤ በኋላም ዘመን ላይ ትስቃለች:: አፍዋን በጥበብ ትከፍታለች፤ የርኅራኄም ሕግ በምላስዋ አለ:: የቤትዋን ሰዎች አካሔድ በደኅና ትመለከታለች÷ የሀኬትንም እንጀራ አትበላም:: ልጆችዋ ይነሣሉ÷ ምስጋናዋንም ይናገራሉ፤ ባልዋ ደግሞ እንዲህ ብሎ ያመሰግናታል:: መልካም ያደረጉ ብዙ ሴቶች አሉ÷ አንቺ ግን ከሁሉ ትበልጫለሽ:: ውበት ሐሰት ነው÷ ደም ግባ ትም ከንቱ ነው፤ እግዚአብሔርን የምትፈራ ሴት ግን እርስዋ ትመሰገናለች:: ከእጅዋ ፍሬ ስጡአት÷ ሥራዎችዋም በሸንጎ ያመስ ግኑአት:: /ምሳ.፴፩:፲/::♦

*የለቅሶ ዜማ ከተባለው ከብላቴን ጌታ ሕሩይ ወ/ሥላሴ መጽሐፍ የተወሰደ*

## ስንት ይሆን ኪሎዬ?

በሕይወት መስመር ላይ በኑሮ ጎዳና፣
ጉዞዬ ከሆነ ውሃ አልባ ደመና::
ፍቅር ካልቋጠርኩኝ በልቤ ስልቻ፣
ዘንግቼ ከወጣሁ የፍቅር እንጎቻ::
ተስተካክሎ ቢቆም ልብስና ሥጋዬ፣
በነፍስ ሚዛን ላይ ስንት ይሆን ኪሎዬ?

*ይታይሽ አዲስ*
*ደቡብ ወሎ ኮምቦልቻ*

## መልካም ፍሬ አፈሩ

በአንድ ልብ ሆነው ሳይከፋፈሉ፣
በኢየሩሳሌም በፅናት ቢቆዩ፤
በሃምሳኛው ዕለት ወርዶ መንፈስ ቅዱስ፣
ቋንቋን አደላቸው ወንጌል እንዲዳረስ::
ታዲያ ብልሆቹ የተግባር ምሁራን፣
ሥራቸው ያማረ የተቃና እንዲሆን፣
ከጉዞአቸው በፊት አስቀደሙ ጾምን፤
ጾምና ጸሎትን ስንቅ ቢቋጥሩ፣
ቃሉን ለመመስከር መች መከራን ፈሩ፤
መልካም ዘርን ዘርተው
መልካም ፍሬ አፈሩ::

*መ/ርት ፀደቀወርቅ አሥራት*

## ዋዜማ ቅኔ

ምንት ይበቁዓ
ለእመ ዓለመ ረብሐ ልሳነ እንግሊዝ ሥጋነ
እስመ ነፍስ ፌደለ ሀገር ዘማሰነት ብነ
ባሕቱ ኢንንዝን በኢትዮጵያ እምነ
እምጣነ ዛቲ ወሀበት ዘወለደት ለነ
ወበዝንቱ ነሐዩ ኩልነ

*ዘመምህር ደሴ ቀለብ*
*መጋቢት ፳ ቀን ፳፻፩ ዓ.ም*

## ትርጉም

*/በሊቀጠበብት ሐረገወይን አገዘ/*

የእንግሊዝኛ ቋንቋ ሥጋችን ዓለምን ሁሉ ቢገዛ ምን ይጠቅማል የሀገራችን ፊደል ነፍስ ጠፍታብናለችና፤ ነገር ግን በኢትዮጵያ እናታችን አንዘን እሷ የወለደችውን ሰጥታናለችና፤ ስለዚህም ሁላችን እንድናለን::

## ሩጫ

ማልያህን ታጠቅ
ቀበቶህን አጥብቅ
ጫማህን አጠባብቅ
መስመርህን ጠብቅ
አትይ ወደኋላ
ተብሎ ተነግሮን
ጀምረን ሩጫ
ለመቀበል ዋንጫ
እኛ ዞረን ስናይ
እነሱ ፈጠኑ
ከሽልማት ጌታ ጽዋም ተቀበሉ::

## ክርስትና

ክርክር ከሰብእና፣
ሰርክ ሙግት ከህሊና፤
ሁሉን ጥሎ አንድ ብቻ፣
የሚያስመርጥ እንበለ አቻ፣
እሱን በልቶ እንደ እንግቻ፤
እጅ ባዶ እሱኑ ስንቅ፣
አልቦ ጋሻ እሱኑ ትጥቅ፤
አድርገነው እንድንጓዝ፣
ናቅ አድርገን ሌላውን ጓዝ፤
ቃላችን ቃሉን ገብቶ፣
እንዲያገኘው ሰርክ ተግቶ::

*አሻግሬ አምጤ*



www.eotcmk.org

# በክህነት መያዝ፣ መሻርና ውግዘት መካከል ያለው ልዩነት ምንድን ነው?

*በመ/ር ለማ በሱፈቃድ*



*ከክህነት ጋር በተያያዘ ግልጽ ያል ሆኑልኝ አንዳንድ ጉዳዮች አሉ። ከእነዚህ አንዱ የአንድ ካህን ክህነት ተያዘ ሲባል ምን ማለት ነው? ክህነት ተያዘ ማለት ከተሻረ ይለያል? ከተለየ በምን? ክህነት የሚያዘው ካህኑ ምን ሲሆን /ሲያደርግ/ ነው? ውግዘትስ ከላይ ከተጠቀሱት ከሁለቱ በምን ይለያል?።*

*ሌላው ደግሞ ክህነትን የተቀበለ አንድ ሰው የክህነት ሥልጣኑን ሊመልስ ይችላል? ለምሳሌ የአካል ጉዳት ቢደርስበት፣ በክ ህነቱ ለመሥራት ጊዜ ባይኖረው?.. ወዘተ እባካችሁ በዚህ ላይ የተወሰነ ማብራሪያ ስጡኝ።*

*ሰላምነህ አባቢ*
*ከጊናገር*

## መግቢያ

ክህነት ተክህነ፣ አገለገለ ከሚለው የግዕዝ ግሥ የወጣ ነው። ክህነት የአገል ግሎቱ ስም ሲሆን ካህን ደግሞ አገልጋዩ ነው። ካህን አገልጋይ ነው ሲባል መን ፈሳዊ አገልግሎት ማለታችን ነው። የክ ህነትም ደረጃዎች ሦስት ናቸው፤ እነሱም ዲቁና፣ ቅስናና ኤጲስ ቆጶስነት ናቸው። በክህነት ማገልገል የተጀመረው ከአባታ ችን አዳም ጀምሮ ነው። በዘመናት ሲከ ፋፈል በሕገ ልቡና፣ በሕገ ኦሪት እና በሕገ ወንጌል እንደ ወቅቱ ሥርዓት የክህነት አገልግሎት ይሰጥ ነበር። በሕገ ልቡና የክ ህነት አገልግሎት ጀማሪው አዳም ሲሆን በሕገ ኦሪት ደግሞ የሌዊ ወገን ብቻ ለሆኑት ለእነ አሮን እንዲሆን እግዚአ ብሔር አዟል። /ዘፀ.፳፰፥፩/ «አንተም ወን ድምህን አሮንን ከእርሱም ጋር ልጆቹን ከእስራኤል ልጆች መካከል ለይተህ ካህ ናት ይሆኑልኝ ዘንድ ወደ አንተ አቅ ርብ» በማለት እንደተገለጸው ተግባራዊ ይሆን ነበር። በሕገ ወንጌል ደግሞ የሐ ዲስ ኪዳንን የክህነት ሥርዓት የዘረጋው ጌታችን አምላካችን ኢየሱስ ክርስቶስ ነው። ይህችም የሐዲስ ኪዳን ክህነት በሕገ ልቡና እና በሕገ ኦሪት ከነበረው በኃይ ልና ክብሯ ትበልጣለች። /ማቴ.፳፰፥፲፱/

የክህነት ሥልጣን ሰዎች ስለፈለጉ ብቻ የሚገኝ ሳይሆን የእግዚአብሔር ምርጫም ነው። ስለሆነም በሓላፊነቱ ከባድ ነው። ጌታችን መድኃኒ



ታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ሥልጣነ ክህነትን ለሐዋርያት በሰጣቸው ጊዜ የሰጣቸው ሓላ ፊነት ከባድ መሆኑን በመጽሐፍ ቅዱስ ተጽፏል። /ዮሐ.፳፩፥፲፭-፲፯/ ክህነት በጉቼን ጠብቅ በማለት የመጠበቅ የማስተዳደር ከፍተኛ ሓላፊነት የተሰጠበት ነው። በመ ሆኑም ክህነት ሲሰጥ ሥርዓትና ሕግ አለው። ቤተክርስቲያን ስለ ካህናት አገልግሎት በግልጽ የሚያስረዱ ቅዱሳት መጻሕፍት አሏት። ከእነዚህ መካከል አንዱ ፍትሐ ነገሥት ነው።

ይህ መጽሐፍ ስለ ካህናት ዲያቆናት እና ኤጲስ ቆጶሳት የአመራረጥ መስፈርትና እንዴት እንደሚሻሩም በዝርዝር ያቀርባል።

የክህነት ደረጃዎች የሚባሉት ሦስት ናቸው። እነሱም፡- ጵጵስና፣ ቅስና እና ዲቁና ናቸው። /ማቴ.፳፭፥፲፬ ትርጓሜ ውን ተመልከት/። ከዚህ ውጭ ያሉት ለምሳሌ ሊቀ ዲያቆናት፣ ሊቀ ካህናት፣ ሊቀ ጳጳሳት የመሳሰሉት የክህነት ደረጃዎች ሳይሆኑ የአስተዳደር ሹመት ናቸው። በሚሾሙበትም ጊዜ፤ ዲቁና ሲሾሙ ጳጳሱ እጅን በተሿሚው ራስ ይጭንበታል። ቅስና እና ጵጵስና ግን በንፍሐት /እፍ በማለት/ ይፈጸማል። /ዮሐ.፳፥፲፱/ ጵጵስና ሲሾም ግን በፓትርያርኩና ሌሎች ከሁለት በላይ የሆኑ ጳጳሳትና ምእመናን ሊሰበሰቡ የግድ ያስፈልጋል። ኤጲስ ቆጶሳት የሚባሉት ጵጵስና ለመሾም የታጩ የተዘጋጁ በድ ንግልና የመነኮሱ አበው ናቸው። እነዚ ህም ኤጲስ ቆጶሳት በተለይ በቀድሞው ሥርዓት ከጳጳሱ ሥር በአውራጃ /በዞን ደረጃ ሲያገለግሉ ጳጳሱ ደግሞ በሀገረ ስብከት /በክፍለ ሀገር አጠቃላይ ያገለግል ነበር። ሊቀ ጳጳሱ /የጳጳሳት አለቃ/ ግን በሲኖዶሱ በጳጳሳት ስምምነት የተመረጠ አንድ ጳጳስ ማለት ነው።

### *«ክህነት ተያዘ» ሲባል ምን ማለት ነው?*

ሐዋርያው ቅዱስ ጳውሎስ እንደተናገ ረው፤ ክህነት ሲሰጥ መስፈርት አለው፤ /፩ጢሞ.፫፥፩/። ሲያዝም መሥፈርት አለው። የክህነት መያዝ እና መሻርም ልዩነት አላ ቸው። ክህነት ተያዘ ሲባል ለጊዜው ነው። የሚይዘውም ጳጳሱ ብቻ ነው። ጳጳሱ በቃል ወይም በደብዳቤ ክህነቱን ለተወሰነ ጊዜ መያዝ ይችላል።







www.eotcmk.org

የአንድን ጳጳስ ክህነት መያዝም ሆነ መሻር የሚችለው በሲኖዶስ /በጳጳሳት ምልዓተ ጉባኤ/ ከተወሰነ በኋላ ብቻ ነው::

የቄሱን፣ የዲያቆኑን ክህነት ግን ጳጳሱ ብቻውን መያዝና መሻር ይችላል:: ቄሱ ግን የቄሱንም የዲያቆኑንም ሥልጣነ ክህነት መያዝና መሻር አይችልም:: ለጳጳሱ ያቀርባል እንጂ::

ሥልጣነ ክህነትን በአግባቡ ያላገለገለበት ካህን ቢኖር እንደ ገብረ ሐካይ /ክፉ ባርያ/ ይቆጠራል:: ክህነቱም ይወሰድበታል:: /ማቴ.፳፭÷፲፬/ በተገለጸው የፍትሐ ነገሥት አንቀጽ በተራ ቁ.፩ የካህን ክህነት ሲያዝ እንዴት እንደሆነ፣ በምን ምክንያት እንደሚያዝ እና መያዝ ሲባል ምን ማለት እንደሆነ ለመጥቀስ ሞክሯል::

### ክህነቱ የሚያዝበት ምክንያት

- የሥነ ምግባር ጉድለት ሲኖርበት፣
- ካህኑን ምእመናን በተለያዩ ጉዳዩች ሲከሱት እስኪጣራ፣
- ካህኑ የፈጸመው ጥፋት ካለ በጳጳሱ አማካይነት የተሰጠውን ቀኖና እስኪጨርስ ድረስ ክህነቱ ይያዛል::

እነዚህና የመሳሰሉት አነስተኛ ጥፋቶች በካህኑ ላይ ከተገኙ ጉድለቶቹን እስኪያስተካክል ድረስ በጳጳሱ አማካይነት የሚሰጠውን ቀኖና ጨርሶ፣ ዳግም ላለማጥ[illegible] ወስኖ በጳጳሱ አማካይነት ው[illegible] ክህነቱ [illegible]መ[illegible] [illegible]ይተላል::

### «ከክህነቱ ተሻረ» ሲባል ምን ማለት ነው?

የክህነት መያዝ ለጊዜው መሆኑን ከላይ ጠቅሰናል:: ካህኑ ደግሞ ከሥልጣኑ ይሻራል ሲባል ካህኑ በሥልጣኑ የሚሰጠው አገልግሎት ሙሉ በሙሉ ይወገዳል ማለት ነው:: ካህን የነበረው ሰው ከክህነቱ /ከሥልጣኑ/ እንደተሻረ ሊቀጳጳሱ ለሚመለከተው ሁሉ በደብዳቤ ያሳውቃል:: ያን ጊዜ ያ ሰው ከክህነቱ ተሻረ ማለት ነው:: እንደ ምእመናንም ሆነ ማለት ነው::

ካህን የተሰጠውን ሓላፊነትና አደራ በአግባቡ ካልተወጣ በወንጌል ያተርፉ ዘንድ መክሊት እንደተቀበሉ ሦስቱ ሰዎች ከእነርሱም መካከል ባለአንድ መክሊቱ ባለማትረፉ መክሊቱን እንደተነጠቀው ለሌላውም ብዙ ላተረፈው እንደተጨመረለት የክህነት የመሻር ሥርዓትም በዚያ አግባብ ይፈጸማል:: /ማቴ.፳፭÷፲፬/ በሚሻሩት በእነዚህ ምትክ ሌሎች ይሾማሉ:: «በጐቼን በትናችኋል፤ አልጐበኛችሁም የሚጠብቁ እረኞችንም አስነሣለሁ::» በማለት በነቢዩ ቃል እንደተነገረ:: /ኤር.፳፫÷፩/

### የሽረቱ ምክንያት

«በእንተ ምክንያት እንተ ታውድቆ ........» ከሹመቱ የሚሻርበትን ምክንያት የሚናገረው ፍትሐ ነገሥት አንቀጽ ፮ ቁጥር ፪፻፳፬ ሲሆን ከሽረቱ ምክንያቶች ጥቂቶቹ ደግሞ

- ሁለት ሚስት ያገባ /ሁለት ጊዜ ያገባ/፣
- ዝሙት የፈጸመ፣
- ነፍስ የገደለ፣
- ጉቦ በመቀበል የታወቀ፣
- ሁልጊዜ በሐሰት የሚመሰክር፣
- የንስሐ ልጆቹን የኀጢአት ኑዛዜ የማይቀበል፣
- እያወቀ ክፉ ሥራን ብቻ የሚያዘወትር፣
- ሁል ጊዜ ስካር የማያበዛ፣
- ባክህነቱ ሥ[illegible]አ[illegible] ነን ማገልገል [illegible] ማገልገል የማይፈልግ፣
- የሃይማኖት ህጸጽ ያለበት፣
- ሥርዓተ ቤተክርስቲያንን እያወቀ የማይጠብቅ፣
- ጥፋቱን ያሻሽል ዘንድ በጳጳሱ የተወሰነለትን ቀኖና ሲጨርስ በድጋሚ ወደ ጥፋቱ የሚመለስና ማሻሻል የማይፈልግ ከሆነ ከሥልጣነ ክህነቱ ይሻራል::

ክህነቱን ለመያዝም ሆነ ከክህነቱ ለመሻር የሚችለው ግን ካህኑ ያለበት የሀገረ ስበከቱ ጳጳስ ብቻ ነው:: ይህንን ተግባራዊ ለማድረግ ግን የሚከተሉት ቅድመ ሁኔታዎች መሟላት አለባቸው::

- ካህኑ የፈጸመውን ጥፋት በተመለከተ በቂ መረጃ መሰብሰብ፤
- /በጥፋቱ ላይ ሪፓርት ያቀረቡት/ ካህኑን ስለጠሉ ብቻ የሚከሱ ሰዎች አለመሆናቸውን ማጣራት፤
- እንደ ጥፋቱ ሁኔታ ታይቶ ምክርና ቀኖና መስጠት፤
- ከምክሩ በኋላ ጥፋቱን ማሻሻሉን ማረጋገጥ ጥና የመሳሰሉትን፤ ቅድመ ሁኔታዎች ተግባራዊ ከሆኑ በኋላ ጳጳሱ ከክህነት ሥልጣኑ መሻር ይችላል::

በአጠቃላይ ካህን ሥልጣነ ክህነቱ የሚያዝበትና የሚሻርበት ምክንያቶች የተለያዩ ቢሆንም ተቀራራቢና ተመሳሳይነት አላቸው:: መሻርና መያዝ ግን ከላይ እንደገለጽነው ልዩነት አላቸው::

### ክህነትን የተቀበለ አንድ ሰው ሊመልስ ይችላል?

ሥልጣነ ክህነት ሲፈልጉ የሚገኝ /የሚወሰድ/ ሳይፈልጉ ሲቀር ደግሞ የሚመለስ አይደለም:: ከላይ እንደተጠቀሰው ባጠፋው ጥፋት መሠረት ሊወሰድበት ይችላል እንጂ የራሱን ምክንያት በማቅረብ መመለስ አይችልም::


### ሰውየው አካላተ ጉደሎ ቢሆንስ? ጊዜስ ባይኖረው?

የክህነት አገልግሎት ዘርፈ ብዙ ነው:: አንድ ካህን ካህን ስለሆነ ብቻ ሊተገብረው የሚገባ ሓላፊነት አለው እነሱም


- ማስተማር
- ማጥመቅ
- ማቁረብ እና የመሳሰሉት ናቸው::

ይህን ባያደርግ ተጠያቂ ይሆናል:: «የማስማርያዬን በጐች ለሚያጠፋና ለሚበትኑ እረኞች ወዮላቸው» በማለት ነቢዩ የካህናትን ድርሻ በተመለከተ ጽፏል:: /ኤር.፳፫÷፩-፫/

ከዚህ የተነሣ አካላት ጉደሎ ሆኖ መቀደስ የሚችል ከሆነ መቀደስ ይችላል፤ ካልቻለ ግን ሌሎቹን አገልግሎቶች



ለአገልግሎቱ ሾሞኝ
ታማኝ አድርጎ ስለቆጠረኝ
ኃይል የሰጠኝን
ክርስቶስ ኢየሱስን ጌታችንን አመሰግናለሁ
/፩ኛ ጢሞ.፩:፲፪/





www.eotcmk.org

ተግባራዊ ያደርጋል፡፡ ማስተማር፣ መባረክ የመሳሰሉትን የአገልግሎት ዓይነት ከቤ ተሰቦቹ ጀምሮ ማገልገል ይችላል፡፡ /ፍት. አንቀጽ.፱፥፳፮-፱/

ጊዜ ባይኖረውስ ለሚለው ደግሞ የሰው ልጅ ምድራዊ አገልግሎቱን የሚያቆመው ሲሞት ብቻ ነው፡፡ አገልግሎት የሚጀምረው እራስን ከማገልገል ነው፡፡ ጊዜውም የተፈጠረልን እግዚአብሔርን ልና ገለግልበት ነው፡፡ ለእያንዳንዱ ተግባር የተከፋፈለ ጊዜ እግዚአብሔር ሰጥቶናል፤ «ለሁሉም ጊዜ አለው» ተብሎ እንደ ተጻፈ፡፡ /መክ.፫፥፩/ ስለዚህ የክህነት አገልግሎት ጊዜ የሚያሳጣ አይደለም፡፡ በሔዱበት ሁሉ ማገልገል ይቻላልና፡፡ በተለያዩ የሥራ ዘርፍ የተሰማሩ ካህናት አባቶች በሚሠሩበት የሥራ ቦታቸው /መሥሪያ ቤታቸው/ የሥራውን ሒደት በማያስተጓጉል መልኩ ምእመናንን ማገልገል ይችላሉ፡፡

## ውግዘት

ውግዘት የሚለው ቃል የግዕዝ ሲሆን ትርጉሙ መለየት ማለት ነው፡፡ አንድ ምዕመን ከሃይማኖት ወጥቶ ከበጐ ምግባር ተለይቶ ከሃይማኖቱ ዶግማና ቀኖና ውጪ ሆኖ ሲገኝ በሥልጣነ ክህነት የሚፈጸም መንፈሳዊ ቅጣት ነው፡፡ ይህን ቅጣት ተግባራዊ የሚያደርጉት ጳጳሳትና ቀሳውስት ናቸው፡፡ ውግዘትን ለማስተላለፍ የራሱ የሆነ ሒደት አለው፡፡ ያጠፋው ካህንም ሆነ ምእመን ስለጥፋቱ አስቀድሞ ይመከራል፡፡ በጉባኤ መካከልም እንዲመከር ይደረጋል፡፡ እስከ ሦስት ጊዜ ያህል ተመክሮ እምቢ ካለ በኋላ ይወገዛል፡፡ ምክንያቱም ሥልጣነ ክህነት ያስራልና ነው «በምድር ያሰራችሁት በሰማይም የታሰረ ይሆናል፤ በምድር የፈታችሁት በሰማይም የተፈታ ይሆናል» ተብሎ ለካህናት ሥልጣን ተሰጥቷቸዋልና ነው፡፡ /ማቴ ፲፰፥፲፰/

ሥልጣነ ክህነቱ የተያዘበት፣ የተሻረ ካህንና የተወገዘ ካህን ልዩነት አላቸው፡፡ ሥልጣነ ክህነቱ የተያዘበትና የተሻረበት ካህን እንደ ምእመን ሆኖ በሃይማኖት ውስጥ ሊኖር ይችላል፡፡ የተወገዘ ከሆነ ግን በሃይማኖት ከቤተክርስቲያን አንድነት የተለየ ይሆናልና ነው፡፡ ይሁን እንጂ ያለ በቂ ምክንያት በጥቃቅን ጉዳዮች ያለ ውይይት፣ ያለ ምክር ማውገዝም የተከለከለ ነው፡፡ ምክንያቱም ማውገዝ ማለት ከቤተክርስቲያን አንድነት ይለያልና፤ በፍትሐ ነገሥት ያለ አግባብ ማውገዝ እንደማይገባ ተጽፏል፡፡ «አኮ በግዘት ኢይእሥር ወኢያውግዝ ዘእንበለ ርትዕ.. ሎቱ ይኩን ውእቱ እሡረ ወውጉዘ እምኀበ እግዚአብሔር፤ በማይገባ አያውግዝ፣ በማይገባ ቢያውግዝ እሱ እራሱ የተወገዘ ይሆናል» ይላልና፡፡ /ፍትሐ ነገሥት አንቀጽ ፭-፩፻፹፬/ ከማውገዝ በፊት /ቅድመ ውግዘት/ ሒደቶቹን በአጽንኦት መመልከት ያስፈልጋል፡፡

> **ጥፋቱ በግልጽ የታወቀ ካህን ሥልጣኑ ያለ መያዙና ያለ መሻሩ ጉዳይ የካህናትን ብቃት እና አስፈላጊነት ዝቅ ሊያደርገው ይችላል፡፡ የካህናት አገልግሎት ጥራትንም በተመለከተ መነሻና መድረሻው እንዳይጠፋና ተተኪውን ትውልድ በአግባቡ ሊመራ የሚችል ካህን ለማፍራት የሚቻለው ያጠፋው እየተቀጣ፣ የተቀጣው እየተስተካከለ ሲሔድ ነው፡፡**

በቤተክርስቲያን ታሪክ ውስጥ እንደ ምናገኘው የሊቀ ጳጳሳት መዓርግ የነበረው ንስጥሮስ የሃይማኖት ህፀፅ ስለተገኘበትና ከክህደቱ አልመለስ ሲል በጉባኤ ኤፌሶን በ፬፻፴፩ ዓ.ም ፫፻ ሊቃውንት ተሰብስበው ከቤተክርስቲያን አንድነት ለይተውታል፡፡ ይህ የሆነበት ምክንያት ንስጥሮስ ተወግዞ በይፋ መለየቱን ያላወቁትን ምእመናን እንዳያሳስት ሊቃውንቱ ከቤተክርስቲያን ለይተውታል፡፡ ሀብተ ክህነቱም ይወሰድበታል /የቤተክርስቲያን ታሪክ በዓለም መድረክ፣ ገጽ.፻፴፩/

አንዱ ጳጳስ ያወገዘውን ሰው ሌላው ጳጳስ ዝም ብሎ አይፈታውም፤ እራሱ ይፈተዋል እንጂ፡፡ ጳጳሱ ያወገዘውን ካህኑ መፍታት አይችልም፡፡ ጉዳዩ ታውቆ ግለሰቡ ከጥፋቱ ከተመለሰ ያወገዘው ጳጳስ ካለ እራሱ ይፈታዋል፤ በሕይወት ከሌለ ግን ሌላ ጳጳስ ይፈታዋል፡፡ ካህን ያወገዘውን ጉዳዩ ከተጣራ በኋላ ጳጳስ መፍታት ይችላል፡፡ /ፍትሐ ነገሥት አንቀጽ ፭-፩፻፶፯/

በአጠቃላይ ውግዘት ያለ ምክንያት የሚተላለፍ ስላልሆነ በጥንቃቄ ታይቶ ከብዙ ሒደት በኋላ የሚከናወን ቅጣት ነው፡፡ ስለሆነም ካህናቱም ሕዝቡም በአጠቃላይ በትዕግሥትና በፍቅር ቤተክርስቲያንን ማገልገል ይገባቸዋል፡፡

## ማጠቃለያ

ጥፋቱ በግልጽ የታወቀ ካህን ሥልጣኑ ያለ መያዙና ያለ መሻሩ ጉዳይ የካህናትን ብቃት እና አስፈላጊነት ዝቅ ሊያደርገው ይችላል፡፡ የካህናት አገልግሎት ጥራትንም በተመለከተ መነሻና መድረሻው እንዳይጠፋና ተተኪውን ትውልድ በአግባቡ ሊመራ የሚችል ካህን ለማፍራት የሚቻለው ያጠፋው እየተቀጣ፣ የተቀጣው እየተስተካከለ ሲሔድ ነው፡፡

ይህ ካልሆነ ግን ምእመናን በአግባቡ የሚሠራ ካህን በመጠየቅ ብቻ ዘመናትን ሊያሳልፉ ይችላሉ፡፡

ክህነት ሰማያዊ ሥልጣንና ጸጋ በመሆኑ በአግባቡ መያዝ የማይችል ካህን ካለ ይወሰድበታል፡፡ የአገልግሎቱን ታላቅነት ተገንዝቦ ሓላፊነቱን የሚወጣ ካህን ደግሞ ስለ አገልግሎቱ ሰማያዊ ዋጋ ያገኛል፡፡ የክህነት አገልግሎት የነፍስን የሥጋን ችግር የማስወገድ ኃይል አለው፡፡ ይህ ውጤታማ የሚሆነው ካህኑ የተሰጠውን በክህነት የማገልገል ጸጋውን በአግባቡ ይዞ የተሰጠውን ድርሻ ለመወጣት ቁርጠኛ ሐሳብ ሲኖረው ብቻ ነው፡፡

✠





www.eotcmk.org

# ጽናት

ፍሬሕይወት ግዛቸው

ከንጋቱ ዐሥራ ሁለት ሰዓት አካባቢ ነው:: መንጋቱን ለማብሰር አዕዋፍ መንጫጫት ጀምረዋል:: ከበላይ ዘለቀ ትምህርት ቤት ትንሽ ወረድ ብሎ ከሚገኙት መደዳ የቀበሌ ቤቶች መካከል አንዷ የሳምራዊት ነች:: ወደ ቤቱ ውስጥ ሲዘልቁ ከበሩ በስተግራ አነስተኛ አልጋ ተዘርግቶ በላዩ ላይ አንዲት ከስምንት ዓመት የማይበልጣት ልጅ በጀርባዋ ኺ ብላ ተኝታለች:: ፊቷ ገርጥቶ የትልቅ ሰው ይመስላል:: ፀጉሯ ተንጨፍርሯል:: ከራስጌዋ በዳንቴል የተሸፈነች ምስለ ፍቁር ወልዳ ሥዕል ተሰቅላለች:: ከምስሉ አጠገብ ከተለጠፈ ረጅም ጊዜ እንደሆነው በቀለሙ መደብዘዝ የሚያስታውቀው ጥቅስ ተለጥፏል:: በሌላው ግድግዳ ላይ የባለቤቷ ፎቶ ግራፍ ይታያል:: ሳምራዊት ልጇ ከተኛችበት አልጋ አጠገብ በተዘረጋች ትንሽ ፍራሽ ላይ ኩርምት ብላ እንደተቀመጠች እንቅልፍ ወስዷታል:: የተጎሳቆለው ሰውነቷ ኑሮ እንዳልተመቻት ከማሳበቁም በተጨማሪ ፊቷ በማድያት በልዟል:: የልጇ የማቃሰት ድምፅ ከእንቅልፏ አባንናት፣ እንቅልፍ ያልጠገቡት ዐይኖቿ ቀልተው አብጠዋል::

«ሚጥዬ... ሚጥዬ... ሚጡ...» ብላ ተጣራች:: ምንም መልስ የለም:: ከተቀመጠችበት ብድግ ብላ ሔዳ ሰውነቷን ዳሰሰቻት:: ሌሊቱን ሙሉ እንደእሳት ይነድ የነበረው ሰውነቷ መቀዝቀዝ ጀምሯል:: ያለማቋረጥ «እህ...እህ... እህ...» የሚ ለው ማቃሰቷና የሰውነቷ መቀዝቀዝ ተደማምረው ሳምራዊትን የምትይዘው፣ የምትጨብጠውን አሳጧት:: ጥብቅ አርጋ አቅፋ ወደ ደረቷ እያስጠጋቻት::

«ወይኔ ልጄ... እንዴት ላድርግሽ?... ይሔ ሁሉ ስቃይ ለኔ ይሁን... አዎ ለእኔ... ለእኔ ለእናትሽ...» መናገር አቃታት:: ቀና ብላ የባለቤቷን ፎቶ ግራፍ አየችና እንባዋ ገደቡን ጥሶ በጉንጮቿ ላይ ፈሰሰ::

ባለቤቷ በላይ የሞተው ከሁለት ዓመት በፊት ነበር:: ጡረታውን አስከብራ በምታገኛት አነስተኛ ገንዘብ ጠዋት ከቁሩ፣ ከሰዓት ከፀሐዩ፣ ማታ ከብርዱ ጋር እየታገለች ጉልት ነግዳ ልጇን ታሳድጋለች:: በዚህ መሐል ነው እንግዲህ ምክንያቱ ባልታወቀ ሁኔታ ልጇ በሽተኛ የሆነችባት:: ያለምንም መሰልቸት በየጠበሉ ይዛት ብትንከራተትም ምንም አልተሻላትም:: ይልቁንም ሕመሙ ከቀን ቀን እየባሰባት ሔደ:: በእቅፏ ላይ ያለችውን ልጇን አተኩራ ተመለከተቻት:: ወዘናዋ ጠፍቶ ማስፈራሪያ መስላለች:: በማቃሰቷ ብቻ በሕይወት እንዳለች ታስታውቃለች እንጂ ሰውነቷ የሙት ነው የሚመስለው:: ማስታመሙን ለብቻዋ ታግላዋለች:: ዛሬ ግን ሰው እንደሚያስፈልጋት ተገነዘበች:: ግድግዳ የሚለያቸውን ጎረቤቷን ወ/ሮ አቻምየለሽን ጮክ ብላ «ወ/ሮ አቻምየለሽ፣ ወ/ሮ አቻምየለሽ... እባክዎትን ድረሱልኝ! ... ድረሱልኝ! .. .ልጄ!... ልጄ!.. .» ብላ ስትጣራ እንባዋ ቀደማት:: ልጇን የበለጠ አጥብቃ እያቀፈቻት ተንሰቅስቃ አለቀሰች:: ወዲያው ደግሞ አልጋው ላይ አመቻችታ አስተኛቻትና ብርድ ልብሱን አለበሰቻት:: ወገቧ ተንቀጠቀጠባት ብርክ ያዛት ባለችበት መሬቱ ላይ ዘፍ ብላ ተቀመጠች:: በሩ በኃይል ተንኳኳ እንደምንም ተነሥታ እየተውተረተረች ሔዳ ከፈተችው:: ጎረቤቶቿ ወ/ሮ አቻምየለሽና መድኃኒት ዐይናቸውን እያሻሹ በር ላይ ቆመዋል::

ወዲያው ወ/ሮ አቻምየለሽ ሳምራዊትን ምንም ሳይጠይቋት አልፈው ወደ ሚጡ አልጋ ተጠጉ:: መድኃኒትም ተከተለቻቸው:: የለበሰችውን ብርድ ልብስ ገለጥ አድርገው ሰውነቷን ዳሰሷት:: ድንጋጤ መላ ሰውነታቸውን ሲያርደው ሳያስቡት «እንዴት? ... እንዴት ነው ነገሩ? ... »ዐይናቸውን ወደ ሳምራዊት እያፈጠጡ:: በሩን ተደግፋ ውጪ ውጪውን ትመለከት የነበረችው ሳምራዊት «ምን? ... ምነው?... ምን ሆኑ?... ልጄ... በቃ...» አለች ትንፋሽ እያጠራት ወደሳቸው እየተንደረደረች:: «አይዞሽ አትደንግጪ! ... ሳሚ ማለቴ ትኩሳቷ ጥፍት ብሏል... እና...» የሚናገሩት ሲያጡ ዝም ብለው ተመለከቷት:: ምንም መልስ አልመለሰችላቸውም እርዱኝ በሚሉ ዐይኖቿ ለመነቻቸው::

«ልጄ ... እህ... ሳምርዬ... እንግዲህ ለዚህች ልጅ አንድ መላ መፍጠር አለብን::...» አሉ እጆቿን ይዘው ዐይን ዐይኗን እየተመለከቱ::

«እስቲ እርሶ ምን እናድርግ ይላሉ:: እኔስ ደከምኩ:: ሁሉን ሞከርኩ አቃተኝ» አለች ግሽግሽ እያደረጋት::

«ቆይ ልጄ ነገሩ ቀላል ነው... እዚህ ያች አንድ አዋቂ አሉ እሳቸው ጋር ብንወስዳት አፍታም አትቆይም ይሻላታል::» አሉ:: በዝምታ ነገሩን ሁሉ ስትከታተል የቆየችው መድኃኒት::

«እኔ ኮ... ገና ስትታመም ጀምሮ ይጸለይላት ብለሽ አምቢ ብልስ ከሀገር ሀገር ስታንከራትቻት ይኸው ለዚህ በቃች:: አሁንም ሊጸለይላት ይገባል» አለች ኮስተር ብላ::

ወ/ሮ አቻምየለሽ ቁጣቸው ገነፈለ::

«ኤዲያ የምን ጸሎት ነው:: ለጸሎት ለጸሎት የኛ ቄሶች መች አነሱ:: ይልቁኑ ሳምርዬ ልብሷን አለባብሿትና አንድ አፍታ ደረስ ብለን እንምጣ::» አሉ በልምምጥ:: ሳምራዊት ነገሩ ሁሉ ተምታታባት:: የልጇ ሕመም፣ ከልጅነቷ ጀምሮ የምታምንበት እምነቷና የጎረቤቶቿ ውትወታ አጣብቂኝ ውስጥ ከተታት:: የቱን እንደምትመርጥ ቸገራት:: ለጊዜው በእነት ከማይጣጣሟት ሰዎች ርቃ ለእምነቷ ቀናኢ መሆኗ እንደሚያዋጣት ወሰነችና «አይሆንም! ... አይሆንም!... ሁላችሁም በምትሉት አልስማማም:: ይልቁኑ ሌላ... አዎ ሌላ ልጄን ማዳኛ ዘዴ ፈልጉ::» አለች እየተወራጨች::

ወ/ሮ አቻምየለሽ በቁጣ:: «ምን ታወራለች ይህቺ? ልጅሽ ብትሞት ከአፈር ምን ታገኚያለሽ:: ባልሽንም በዚህ ድርቅናሽ ነው ከአፈር ያገባሽው... እ... » ብለው ሊናገሩ የጀመሩትን ሳይጨርሱ ሳምራዊት ጣልቃ ገብታ «እንደዚህ አይበሉኝ ወ/ሮ አቻምየለሽ::. . . እንጣላለን እንደዚህ አይበሉኝ::» አለች ምርር ብላ:: መድኃኒት እቅፍ አድርጋ እያረጋጋቻት «አይዞሽ ሳምሪ.. . ያለፈ አልፏል. .. አሁን ማሰብና ለማዳን መጨነቅ ያለብን የሚጥዬን ነፍስ ነው:: ... እባክሽ እሺ በይኝና ይጸለይላት:: ... እስቲ ተመልከቻት እየደከመች እኮ ነው::» አለቻት በትሕትና:: ዞር ብላ ልጇን ተመለከተቻት አሁን ከቅድሙ የባሰ ጣረ ሞት መስላለች:: ድምፏም ከበፊት አሁን በጣም እየቀነሰ ነው:: የልጇ ሞት እውን መሆኑ ታወቃት:: በምንም መንገድ ይሁን በምንም ልጇን ማዳን እንዳለባት ውሳኔ ላይ ደረሰች:: ከልጇ የሚበልጥ ነገር እንደሌላት ራሷን አሳመነችው:: ግን ደግሞ እግዚአብሔርን እንደምታስቀይም ታወቃትና ስቅስቅ ብላ አለቀሰች:: ወ/ሮ አቻምየለሽ «ሳምርዬ... እባክሽን ይህቺን ልጅ አንድ በያት:: ... »አሉ መድኃኒትን ገልመጥ እያደረጉ:: ግራ ገባት አወጣች አወረደችና እንደ እብድ እያደረጋት «... ሂዱ... ሂዱ ምንም ነገር አድርጋችሁ ልጄን... አዎ ልጄን አድኑልኝ! ... » አለች እየተንዘፈዘፈች:: ያልጠበቁት መልስ ስለነበር እርስ በእርሳቸው ተያዩ:: ዐይኗን አፍጥጣ እያየቻቸው «እኮ... በሉ ልያችሁ ልጄን አድኑልኝ::... » አለች ወደ ልጇ ሔዳ እጆቿን ይዛ እያሻሸቻት ወ/ሮ አቻምየለሽ «መጣሁ ቤቴ ደረስ ብዬ:: ልብሷን አለባብሰሽ ጠብቂኝ::. . . » ብለው እየተጣደፉ ሲወጡ፣ መድኃኒት ወደ ሳምራዊት ጠጋ ብላ

«ሳምሪ ዝም በያት ይህቺን የዲያብሎስ ፈረስ:: አንድ ወንድማችን እዚህ ከኛ ቤት በታች ካለው ቸርች ስላለ እሱን ይገፉ መጥቼ ይጸልይላታል:: የትም





www.eotcmk.org




ይዘሻት እንዳትሔጂ።... እሺ ሳምሪ?.. » አለቻት። ወደ ፕሮቴስታንቱ መድኃኒት።

«ነገርኳችሁ እኮ መድኃኒት። እኔ ግራ ቀኙ የተዛወረብኝ ሰው ስለሆንኩ ልጄ ትዳንልኝ እንጂ የትም እሔዳለሁ። ...» አለች እዝን ብላ። መድኃኒትም ምንም መልስ አልመለሰችላትም እየሮጠች ወጣች። ከወዲያ ወዲህ ተንቆራጠጠች። የምታደርገው ብታጣ እግዚአብሔር የፈጸመችውን ነገር ከጥፋት እንዳይቆጥረው እያለቀሰች ልትነግረው ግድግዳ ላይ ባለው ምስል ሥር ተንበረከከች። ዐይኗ ግን ከምስሉ ላይ ሳይሆን አጠገቡ ከተለጠፈው ጥቅስ ላይ ዐረፈ። ደብዛዛ ቀለሙ ደምቆ ታያት። «እስከ መጨረሻው የሚጸና እርሱ ይድናል። ማቴ.፳፬፥፲፫» ይላል። ደነገጠች መላ ሰውነቷን የሆነ ነገር ወረራት። «እኔስ. . . እኔስ. . . እኔስ. . .» ብላ ሳታስበው ደጋግማ ጮኻ አልጋው ጠርዝ ላይ ተደፍታ ማሰብ ጀመረች። በመጽሐፍ ቅዱስ ላይ አብርሃም ልጁን ለእግዚአብሔር መሥዋዕት አድርጎ ያቀረበው ትዝ አላት። ታዲያ የእኔ ልጅ ከእርሱ ልጅ ትበልጣለች እንዴ አለች በሐሳቧ። «ኧረ በፍጹም... ኧረ በፍጹም...» እያለች ተነሥታ ወደ ዕቃ ቁምሳጥኑ ሔዳ ከፈተችና የጠበል ጀሪካን ይዛ ወደ ልጇ አልጋ ተጠግታ በቁሟ በልጇ ላይ አንደቀደቀችባት። ወዲያው ደግሞ ዕቃውን በቁሟ መሬት ላይ ወርውራ የልብስ ሳጥኗን ከፍታ መቀነት አውጥታ አጥብቃ ታጠቀችው። ውጪ ስትወጣ የምትለብሳትን የክት ነጠላዋን አውጥታ አዘቅዝቃ ለበሰችና በአልጋው ጠርዝ ላይ ቁጭ ብላ የልጇን ሞት ትጠባበቅ ጀመር።

አሁን የሚጡ ድምፅ በጣም ቀንሷል። ዐይኖቿ አሁንም እንደተከደኑ ሲሆን፣ ሰላማዊ እንቅልፍ የተኛች እንጂ በበሽታ የምትሰቃይ አትመስልም። ፊቷ ላይ ሰላም ሰፍኗል። ሳምራዊት ግን እንደበፊቱ ልትዳስሳት ልታቅፋት ምንም ፍላጎት የላትም። ቆርጣ ወደ መቃብር ልትሰዳት ወስና ዝም ብላ ውጪ ውጪውን እያየች ቁጭ ብላለች። ምንም ዓይነት የሐዘንም ሆነ የመረበሽ ስሜት አይስማትም ብቻ በድን ሆናለች። በዚህ ሁኔታ ላይ እንዳለች መድኃኒት ከአንድ መልከ መልካም ወጣት ጋር፣ ወ/ሮ አቻምየለሽ ደግሞ ቄጤማ በእጃቸው እንዳንጠለጠሉ ተከታትለው ገቡ። ሁሉም የሳምራዊትን የተዘቀዘቀ ነጠላ ሲመለከቱ በቆሙበት የጨው ዓምድ ሆነው ቀሩ።

ወ/ሮ አቻምየለሽ ራሳቸውን እንደምንም አረጋግተው «ምነው ልጅ ዐረፈች እንዴ?» አሉ በእጃቸው የያዙትን ቄጤማ በቁማቸው እየለቀቁት። መድኃኒትና ልጁ ወደ አልጋው እየተጠጉ «በኢየሱስ ስም ሞተች!» አሉ። ሳምራዊት ግን ረጋ ብላ «አልሞተችም። ግን መሞቷ ስለማይቀር ተዘጋጅቼ ልጠብቃት ብዬ ነው። ስላለፋዋችሁ ይቅርታ አድርጉልኝ። ከአሁን በኋላ ልጄን የትም ይገፍ መሔድም ሆነ እንዲጸለይላት አልፈልግም። በእሷ ሥጋ እቀበር ይመስል ከእምነቴ መናወጥ አል ፈልግም። አምላክ ፍጠራት ብዬው ሳይ ሆን እርሱ ራሱ ፈጥሯታል አሁን ደግሞ ሊወስዳት ከፈለገ ይውሰዳት... ንብረቱ ነች።» አለች እንባዋ በጉንጮ ኮለል እያለ።

በአልጋው አጠገብ ቆመው ሲመለከቷት የነበሩት መድኃኒትና ወጣቱ ልጅ መተንፈሷን ሲመለከቱ «ልንጸልይላት ይገባል» ብለው በአልጋው አጠገብ ተንበረከኩ። «በጭንቅ አማላጁ ይገፍ ያአችኋለሁ ከልጄ አጠገብ ተነሡ... ተነሡ...አለዚያ ልጮኽ ነው።...»ብላ ልብሳቸውን ይዛ ጎትታ አስነሣቻቸውና እንደ እብድ እያደረጋት ሳታስበው «ኡ...ኡ... ኡ...» ብላ ጮኸች። በጩኸቷ የተደናገጠችው አልጋ ላይ የተኛችው ሕፃን ተንቀሳቀሰችና ዐይኗን ገለጥ አድርጋ « እማ... ም ... ምን... ሆንሽ?...» አለች። ሳምራዊት ዞር ብላ ተመለከተቻት። የሚጡ ዐይኖች ተገልጠዋል። ማመን አቃታት። በደመ ነፍስ ወደ ልጇ አልጋ ተንደርድራ እላይዋ ላይ ተደፋች። ሁሉም በመገረም ዝም ብለው ተመለከቷት። የእግዚአብሔርን ድንቅ ሥራና የእሷንም ጽናት እያደነቁ።♦


# የቪሲዲ /ሲዲ የቴፕ ካሴት መሸጫ ዋጋ

| የማኅበሩ /የውጪ | ባለ 1 ዲስክ | | ባለ 2 ዲስክ | |
|---|---|---|---|---|
| | ችርቻሮ | ጅምላ | ችርቻሮ | ጅምላ |
| ሲዲ/ቪሲዲ | 15.00 | 11.00 | 20.00 | 15,00 |
| የማኅበሩ /የውጪ የቴፕ ካሴት | 9.00 | 7.00 | | |
| $MP_3$ የስብከት ሲዲ | 25.00 | 20.00 | | |


የጅምላ ዋጋ፣ ለአዟሪ ለመዝሙር ቤት፣ ለማዕከላት፣ ለወረዳ ማዕከላት ለሰንበት ት/ቤቶች ከአምስት በላይ ሲሆን ከላይ በተጠቀሰው መሠረት ይሆናል።

አድራሻ፡-
በማኅበረ ቅዱሳን ማከፋፊያዎች

# ከቅዱሱ ሐይቅ በረከቶች

ዲ/ን ብርሃኑ አድማስ

ባለፉት ሁለት እትሞቻችን የጣናን ታሪካዊ መላምቶች መነሻ በማድረግ ጣና ቂርቆስን፣ ምጽሊ ፋሲለደስንና ሬማ መድኃኔዓለም ገዳማትን ተመልክተን የጀልባ ጉዞአችንን መስመር በመከተል ወደ ደብረ ማርያም በማቅናት ላይ ሳለን ትረካውን ማብቃታችን ይታወሳል። በዚህ ዕትም ደግሞ ደብረ ማርያምንና የዛራ ሚካኤልን ጉዛ ከፊል ገጽታ እናያለን።



ደብረ ማርያም እንተ ይእቲ ሙጽአ ግዮን እም ጣና

### ሙጽአ ግዮን /የዓባይ መውጫ/

ወደ ደብረ ማርያም ስንደርስ ማዕበሉ ጸጥ እያለ እየቀነሰ ነበር። ደብረ ማርያም የጣና ደቡባዊ ጫፍ ላይ የምትገኝ ደሴት ናት። ዓባይ ወንዝ ከጣና የሚወጣው ከደብረ ማርያም ግራና ቀኝ ነው። ከሁለቱ አቅጣጫ ወጥቶ ከተገናኘ በኋላ ዓባይ ይባላል እንጂ ጣና አይደለም። ካፒቴናችን ዘመኑ ይህን ሁኔታ ለማሳየት ሲል ከሬማ እንደመጣን በቀጥታ ወደ ገዳሟ ደሴት ማምራቱን ትቶ ዓባይ የሚወጣበትን ሁኔታ ለማሳየት ከገዳሟ በስተ ምሥራቅ በኩል ካለው ትልቁ መውጫው ጀምሮ ከመኻኛው አድርሶ በሁለተኛው የዓባይ መውጫ አዙሮ ወደ ገዳሟ አደረሰን። ዓባይ ከጣና ሲወጣ ለማየት የነበረንን ፍላጐትም በዐይናችን አይተን አረጋገጥን። ውኃው ከጣና መውጣት ሲጀምር እየተናደ ወይም እየተፈረካከሰ የሚሔድ ይመስላል። የጣና ክፍል የሆነው ውኃ ደግሞ የቆመ ወይም የረጋ መስሎ ልዩነቱን በድንበር ቁልጭ አድርጎ ያሳያል። በዚህ እየተደነቅን ጀልባችን ወደ ደብረ ማርያም ተጠጋች።

### ደብረ ማርያም

ደብረ ማርያም ገዳም በጥንቱ አከፋፈል በበጌምድር ግዛት አሁን ደቡብ ጎንደር ዞን በሚባለው/፣ በደራ ወረዳ፣ የዘንዘልማ ሹም አቦ ቀበሌ ገበሬ ማኅበር በአሁኑ ደግሞ በባሕርዳር ልዩ ዞን ባሕርዳር ዙሪያ ወረዳ የዘንዘልማ ደብረ ማርያም ቀበሌ ገበሬ ማኅበር ውስጥ የምትገኝ የደሴት ገዳም ናት። በደሴቷ ላይ የሚገኙት ነዋሪዎች ከሃምሳ አባወራዎች አይበልጡም። አብዛኛው የደብሯ ተገልጋዮችም ጀርመድ እየተባለ በሚጠራው መንደር የሚኖሩ ገበሬዎች ናቸው። ጀርመድ ዓባይን /ጣናን/ በታንኳ ወደ ጎንደር አቅጣጫ ከተሻገሩ በኋላ የሚገኝ የገጠር መንደር ሲሆን በባሕርዳር ዙሪያ ካሉት የገጠር ቀበሌዎች አንዱ ነው። በአሁኑ ጊዜ በማዶው መንደር ላሉት የመድኃኔዓለም ቤተ ክርስቲያን ተተክለውላቸው በየዕለቱ በታንኳ መመላለስ ቀርቶላቸዋል። ይሁን እንጂ አሁንም ሁለቱ /ደብረ ማርያምና ገድሮ ደብረ መድኃኒት መድኃኔዓለም/ በአንድ ሰበካ ጉባኤ ሥር ይተዳደራሉ።

የጀርመድ፣ የገድሮና ደብረ ማርያም ያለችበት ሹም አቦ አሁንም ዘንዘልማ ደብረ ማርያም የሚባለው ቀበሌ ገበሬ ማኅበር መንደሮች ናቸው።

የደብረ ማርያም ገዳምን አመሠራረት የሚተርኩት የገዳሟ ሊቃውንትም ገዳሟ በጻድቁ አቡነ ታዴዎስ፣ በዐፄ ይኩኖ አምላክ ዘመነ መንግሥት እንደተመሠረተች ይናገራሉ። የገዳሟ መሥራች አቡነ ታዴዎስ መሆናቸው ልዩነት የሌለባት ቢሆንም ዘመኑን ግን በዐፄ ዓምደ ጽዮን ዘመነ መንግሥት እንደሆነ የሚናገሩም አሉ።

አቡነ ታዴዎስ ከሰባቱ ከዋክብት አንዱ እንደ መሆናቸው መጠን ጊዜው በ፲፬ኛው ክ/ዘመን እንደሆነ ይታመናል። የቦታዋ ሊቃውንት እንደሚገልጹት ሰባቱ ከዋክብት የሚሏቸው፤ በጣና ዙሪያ ገዳማትን በማቅናትና ስብከተ ወንጌልን በማስፋፋት የተጉትን አባቶች ነው። እነዚህም ታዴዎስ ዘደብረ ማርያም፣ ዘዮሐንስ ዘክብራን ገብርኤል፣ በትረማርያም ዘዘጌ፣ ያፍቅረነ እግዚእ ዘጉጉቤ፣ ያሳይ ዘመንዳባ፣ ዘካርያስ ዘገሊላ እና ሂሩተ አምላክ ዘዳጋ ናቸው። በርግጥም የእነዚህ አባቶች ገዳማት አሁንም አሉ። ገዳማቱም በጣና ደሴቶች ውስጥ ይገኛሉ። የሂሩተ አምላክ ዘዳጋ አንጻራዊ በሆነ መልኩ ወደ ባሕሩ በትንሹ ገባ ያለ ደሴት ሲሆን፤ የዮሐንስ ዘክብራንም ባሕርዳር ከተማ ሆኖ እጅግ በቅርበት የሚታይ ደሴት ነው። የሌሎቹ ግን ጣናን በሁሉም አቅጣጫ ከብበውና መነሻ አድርገው ወደ ገጠሩ እየወጡ የሚያስተምሩባቸውን ገዳማት መሥርተዋል። በትረ ማርያም ዘዘጌ፣ ጎጃምን እና ዘዮሐንስ ዘክብራን፤ በተለይም በአሁኑ ጊዜ ምዕራብ ጎጃምና አዊ ዞን የሚባለውን ሲያስተምሩ፤ ታዴዎስ ዘደብረ ማርያምና ጣና ቂርቆስ ፊት ለፊት ገዳማቸውን ያቀኑት ያፍቅረነ እግዚእ ዘጉጉቤ ደግሞ ከደራ ወረዳ ተነሥተው በጌምድርን ያስተምሩ ነበር። ዘካርያስ ዘገሊላ እና ያሳይ ዘመንዳባ ደግሞ አሁን ሰሜን ጎንደር የምንለውን የጥንቱን ሰሜን ክፍል የሆነውን የጣና ዙሪያ፣ ደንቢያንና የአካባቢውን ወረዳዎች አስተምረዋል። በርግጥ ወደ እነዚህ ገዳማት ከመግባታቸው በፊት ሁሉም በተለያዩ ብዙ ቦታዎች አስተምረዋል። ለምሳሌ ዘዮሐንስ ዘክብራን በትግራይ ያስተማሩትን መጥቀስ ይቻላል። በዚሁ መሠረት ደብረ ማርያም ገዳም ከጥንታውያን ገዳማት አንዷና ታሪካዊቷ ናት።


የደብረ ማርያም ገዳም መነኮሳት እጅግ ታዋቂዎችም ነበሩ። በተለይ በዐፄ ዘርዐ ያዕቆብ አደባባይ ከፍተኛ ክብር እንደ ነበራቸው ይነገርላቸዋል። /የቤተ ክርስቲያን መረጃዎች፣ ገጽ.፩፻፵፮/ በኋላም በጎንደር ዘመነ መንግሥት፤ ይልቁንም በዐፄ አድያም ሰገድ ኢያሱ /፲፮፻፸፩-፲፮፻፺፫/ ገዳሟ የብዙ ሊቃውንት መሰባሰቢያና የመመካከሪያ ሥፍራ ነበረች።

ወደዚህች ታሪካዊት ገዳም ስንገባ የገዳሟን አስተዳዳሪና ሌሎች ጥቂት አገልጋዮችን አግኝተን ነበር። ይሁን እንጂ እጅግ መሽቶ ስለነበር ዕቃ ቤቱንም ሆነ ቤተ ክርስቲያኑን ገብቶ ለማየት አልተቻለም። ላቀረብኩላቸው ጥያቄዎች ግን ምላሻቸውን





www.eotcmk.org



የደብረ ማርያም አስተዳ/

አልነፈጉኝም:: ጻድቁ አቡነ ታዴዎስ ዘደብረ ማርያም ወደ አካባቢው በመጡበት ወቅት በደራ ወረዳ /የደቡብ ጎንደር ዞን ወስጥ ያለ ሉአሁኗ ባሕርዳር ከተማ የሰሜን ምሥራቅ አዋሳኝ ወረዳ/ መዊጥ የሚባል መክንን ነበር። ጻድቁ ይህን ሰው አሳምነው አጥምቀዋል፣ የሞተ ልጁንም አሥነስተውለታል:: ይህም ለዚህ አካባቢ አገልግሎታቸው ታላቅ በር ከፋች ነበር::

ከዚህ በኋላ ገዳማቸውን መሥርተው በሰባኤ እየተጉ በገድል እየተቀጠቀጡ በእግዚአብሔር ፈቃድም ወጥተው በማስተማር ሕዝቡን ነባዕድ አምልኮና ከምግባረ ብልሽነት እየመለሱ ተጋድሎአቸውን ቀጠሉ:: በዚህም ምክንያት ብዙ መናንያንና መነኩሳት ወደ እርሳቸው ጐረፉ። ጻድቁም አሠረ ፍኖታቸውን የተከተሉ ለጽድቅ የሚጋደሉ መናኞችንና ታላላቅ ሊቃውንትን አፈሩ::

ነገር ግን እነዚህንና የመሳሰሉትን ነገሮች በዝርዝር የሚነግር ታሪክ በአሁኑ ጊዜ ሊገኝ አልቻለም:: የዚህም ምክንያቱ ገዳሟ በተቃጠለችበት ጊዜ ብዙ ቅርሶቿ በተለይም መጻሕፍቱ ስለወደሙ ነው:: ይሁን እንጂ አሁንም አንዳንድ ንዋያትና የክብር ዕቃዎችን ይዛለች:: የገዳሟ አገልጋዮች እንደገለጹልኝ ከጥንታውያን የብራና መጻሕፍት አርባዐቱ ወንጌል፣ ዳዊትና ተአምረ ማርያም እንዲሁም ከንዋያተ ቅድሳት የአቡነ ታዴዎስ የእጅ መስቀል፣ የቅዱስ ላሊበላ መስቀል፣ ዐፄ ዮሐንስ የሰጡት ሰን /ባለርግብ/ እና ሌሎችም በገዳሟ ይገኛሉ::

ገዳሟ ከነበራት ታላቅነት የተነሣ ዐፄ ዐምደ ጽዮን ቀዳማዊ /፲፪፻፺፱-፲፫፻፲፱/ ሃምሳ ደብሮችን ቅፈፍ /የተለያዩ ግብሮችን የሚሰጡ/ አድርገው ሠርተውላት ነበር:: አሁን ያለውን ቤተ ክርስቲያን ከቃጠሎው በኋላ ዐፄ ቴዎድሮስ ያሠሩት እንደሆነ ይነገርለታል:: ይህም ግን በቅርቡ በ፲፱፻፹ዎቹ በወ/ሮ አጸደ ወይን በቀለና እማ ዘውዴ በተባሉ እናቶች እንደታደሰ የቤተ ክርስቲያኗ አባቶች ገልጸዋል::

ገዳሟ እና ዐፄ በዕደማርያም /ወልደ ዘርዐ ያዕቆብ/ ክርስትና የተነሡባት እንደሆነችም ይመሠክርላታል:: ይህችን ጥንታዊት ደብር ከውጭ በኩል ተዟዙረን ከጐበኘን በኋላ የጉዞአችን ፍጻሜ ሆነና ወደ ባሕርዳር ተመለስን:: ታሪኳም በዚሁ ምክንያት አጭር ሆነ::

## ክፍል ሁለት ጉዞ

አሁን ደግሞ በባሕር ላይ የተደረገው ጉዞ አብቅቶ በየብስ ጉዞ ያየኋቸው ጥቂት ገዳማት ላስተዋውቃችሁ:: አንዳንዶቹ የሕዝብ ማመላለሻ መኪናዎች የማይደርሱባቸው ስለነበሩ ለዚሁ አገልግሎት ከፍተኛ ርዳታና እገዛ ያደረገልኝን አቶ አማረ ዳኜን ሳላመሰግን አላልፍም:: የመጀመሪያው የየብስ ጉዞዬ ቅኔንና መጻሕፍትን በአንድነት እያስተማሩ በምናኔ ሕይወት የሚኖሩት የኔታ ጥበቡ ወደሚገኙበት ደብር ዛራ ሚካኤል ነበር::

## ዛራ ሚካኤልና የኔታ ጥበቡ

ዛራ ሚካኤል ከባሕርዳር ወደ ጎንደር በሚወስደው መንገድ ፴፭ ኪሎ ሜትር ያህል እንደተጓዝን ከሐሙሲት ከተማ ወጣ ብሎ ከመንገድ በስተግራ በኩል የሚገኝ ጥንታዊና ታሪካዊ ደብር ነው:: የሐሙሲት ከተማ በሰሜን ዛራ ሚካኤል፣ በደቡብ ወንጨት ሚካኤል በሚባሉ አብያተ ክርስቲያናት መካከል ያለችና ሁለቱን አድባራት ጠብቆኝ ብላ የምትማጸን የምትመስል ከተማ ናት:: ከባሕርዳር ስንጓዝ መጀመሪያ ያገኘነው ወንጨት ሚካኤልን ሲሆን ደብሩ አቡነ ሰላማ /ፍሬምናጦስ/ ጣናን ባርኰ የአካባቢውን ሕዝብ ካጠመቀ በኋላ ለአካባቢው ምእመናን በ፫፻፴፬ ዓ.ም የተከለው ደብር እንደሆነ ይነግረለታል:: የአቡነ ሰላማ የእጅ መስቀልና የመሳሰሉትን ጥንታዊ ቅርሶች የያዘው ይህ ደብር ጥንት ገዳም እንደነበርና እጅግ ብዙ መነኩሳት እንደነበሩበት ይነገርለታል:: ቅድስት ወለተ ጴጥሮስ ከተጋደ ለችባቸው ሰባት ገዳማትም አንዱ ይኸው ወንጨት ሚካኤል ነው:: ወንጨትን ቀርበን ሳንሳለም በቅርብ ርቀት እያየነውና ጥቅጥቅ ባለደን የተከበረውን አስደሳች ገጽታውን እያየን አለፍነው:: ሐሙሲትን አቋርጠን ወደ ዛራ ሚካኤል ደረስን::


የዛራ ሚካኤል ደንም እጅግ ማራኪ ነው:: ዋንዛው፣ ዝግባው፣ ኮሽሙ፣ ዋርካውና የመሳሰሉት ዛፎች ጥቅጥቅ ብለው ከብበው ታል:: በጫካው ውስጥ ለው ስጥ ባለች ሰርጥ ወደ የኔታ ጥበቡ ጉባኤ ቤት አመራን:: እጅግ ብዙ የሣር ጐጆዎች ተደርድረዋል፡ ደቀመዛሙርት በየጐጆአቸው ውስጥና በየበሩ ሁለትና ሦስት ሆነው ይማማራሉ:: ቅጸላ ይሉታል::



የኔታ ጥበቡ በቤተ ገብረሥላሴ



www.eotcmk.org



ደብረ ማርያም

በወንበር /በመደበኛው ክፍለ ትምህርት/ የተማሩትን የሚያጠኑበት ማለት ነው። በቅኔ ቤት ግሥ ያጠናሉ፤ የቆጠሩትን ቅኔ እየነገሩ ወይም በወንበር የተነገረውን እያስታወሱ ሞያ /የቅኔውን አገባብና እያንዳንዷ ቃል በቅኔው ውስጥ ያላትን ሰዋሰዋዊ አገልግሎት/ እያወጡ ያጠናሉ። ለእነርሱ ሰላምታ እየሰጠን በማለፍ ወደ የኔታ ቤት አመራን፤ እሳቸው ግን በቤታቸው አልነበሩም። በሕመም ምክንያት ለሕክምና ደቀ መዛሙርቶቻቸው ወደ ባሕርዳር ወስደዋቸው ኖሮአል።

ሐዘን እየተሰማን ጉባኤ ቤቱን ተዟዙረን ከተመለከትን በኋላ በዕቅዳችን ለመመራትና ቀኑን ላለማባከን የኔታ ይገኙበታል የተባለውን አድራሻ ጠይቀን ወደ ባሕርዳር ገሰገሥን።

## ቤተ ገብረሥላሴ

ባሕርዳር ከተማ እንደገባን የኔታ ጥበቡ ይገኙበታል ወደተባለው ቤት አመራን። በፈለገ ገነት ቅዱስ ጊዮርጊስ ቤተ ክርስቲያን ዙሪያ የየራሳቸውን ትንንሽ መጠለያ ሠርተው የሚኖሩ የቤተ ክርስቲያን ሰዎች አሉ። የኔታ ያረፉት ገብረሥላሴ በሚባሉ አንድ ሰው ደከም ያለች ጐጆ ውስጥ ነው።

ወደ ቤታቸው እንዳገባሁ የኔታ ጥበቡ የጭቃ መደብ ላይ ተኝተዋል። የቤቱ ባለ ቤት ገብረ ሥላሴ ደግሞ ዳቦ ገዝተው፣ ሻይ አፍልተው የኔታን ይለምናሉ። «ይነሡ ሻይ ይጠጡና መድኃኒቱን ይውሰዱ» እያሉ። በሁኔታው በጣም እያዘንኩ እንደምንም ተረጋግቼ የኔታን ሰላም አልኩኝ። እርሳቸውም ከመኝታቸው ተነሥተው ሰላምታ ሰጡኝ። «እርሳቸውን የመሰለ አባት በአንዲት ሰሌን ላይ መደብ ላይ ተኝተው የተገኙትውን ደረቅ ዳቦ በልተው እንዴት ይድናሉ?» እያለ ውስጤ ይሞግተኛል። የኔታ ግን ይህችንም የከተማ የቅንጦት ምግብ አድርገዋት «እንቢ» እያሉ ይገለገላሉ። ከብዙ ክርክር በኋላ ከዳቦው ትንሽ ጐርሰው የታዘዘላቸውን መድኃኒት ዋጡ። በሁኔታው በጣም ስለተነካሁ «የኔታ ለመሆኑ የሚያሳክምዎት ማን ነው?» አልኳቸው።



የየኔታ ጥበቡ የቅኔ ጉባኤ ቤት ከፊል ገጽታ

እርሳቸውም እንደልማዳቸው ፈገግ እያሉ «ገብረ ሥላሴ» አሉ፤ የጐጆውን ባለቤትና ሻይ አፍልተው ያቀርቡትን አባት።

የኔታ ገብረ ሥላሴ በጃንሆይ ጊዜ ጎጃም ቅኔ ቤት /አዴት ውስጥ/ በነበሩበት ወቅት ታምመው ጓደኞቻቸው ለሕክምና ወደ ባሕርዳር አምጥተው ፈለገ ሕይወት ሆስፒታል ካስገቧቸው በኋላ፤ በዚያው አካባቢ ላሉ ተማሪዎች አደራ ሰጥተዋቸው ሔዱ። ሆስፒታሉ ለተወሰነ ጊዜ ካከማቸው በኋላ ያስወጣቸውና መንገድ ላይ ይወድቃሉ። ከአንድ ዓመት በኋላ የቤተ ክርስቲያን አባቶች ወደ ቤተ ክርስቲያን አስጠግተው ያድኗቸዋል። ተመልሰው ቅኔ ቤት እንዳይሔዱም ይከለክሏቸዋል። ከዚያን ጊዜ ጀምሮ በዚህ ቤተ ክርስቲያን ለራሳቸው ጐጆ አዘጋጅተው ራሳቸውን በራሳቸው እየረዱ ይኖራሉ። እሳቸው እንደገለጹልኝ እዚህ ቦታ ብቻ ለ፴፬ ዓመታት ኖረዋል። እኔም የማሳከም አቅም እንዴት እንደኖራቸው ለማወቅ የኔታ ገብረ ሥላሴን «ገቢዎት ምንድን ነው?» ስል ጠየቅኋቸው። ገቢያቸውን የሚያገኙት በከተማው ጫፍ ላይ ከሚገኘው የቅዱስ ሚካኤል ገዳም ወደብ ሔደው ከዘጌ የሚመጣ የማገዶ እንጨት ከገበሬዎች ከገዙ በኋላ ያችን ከተማ አምጥተው በመሸጥ ከሚያገኟት ትርፍ ብቻ ነው። በዚህች ገቢ ራሳቸውን ያኖራሉ፤ እነ የኔታን የመሰሉ አባቶች ይቀበላሉ፤ ሲታመሙም ያሳክማሉ፤ እግዚአብሔርን እያመሰገኑ ይኖራሉ፤ በቃ የርሳቸው ሕይወት ይህ ነው።

መገረሜን አላቋረጥኩም። ሁለቱንም ከዚህ በፊት ባውቃቸውም ዛሬ የማየው ደግሞ ልዩ ነው። የኔታም ከአዲስ አበባ ተጉዤ ቦታቸው ላይ ስላጣኋቸው እያዘኑ ቁጭ ብለው ምንም እንዳልታመመ እኔን ማስተናገድ ጀመሩ። የኔታ ገብረ ሥላሴም «ምን ላቅርብ?» ይላሉ። ከእነርሱ ማዕድ ተካፈልኩና ወደ ሔድኩባቸው ጥያቄዎች አመራሁ። ቃለ መጠይቅ ያደርግሁት በጨዋታ መልክ ቀስ በቀስ ስለነበር በዚያው መንገድ ስለየኔታ ጥበቡ እጅግ በትንሹ ካስተዋወቅሁ በኋላ ወደ ቤተ ክርስቲያኑ ታሪክ እመለሳለሁ።

## የየኔታ አፍ መፍቻ

የኔታ ስለራሳቸው ትምህርት ከመንገር ይልቅ ስለ መምህራቸው መናገር ይቀናቸዋል። መምህራቸው ጎንደር /ስሜን ጎንደር/ ውስጥ ተንከል ደቢጋ ሚካኤል በሚባል ደብር ቅኔና መጻሕፍትን በማስተማር ስመ ጥር የነበሩት የኔታ አክሊሉ ናቸው። ታዲያ የኔታ ከእርሳቸው እንደተማሩ ከገለጹ በኋላ፤ አከታትለው የሚናገሩት መምህራቸው የኔታ አክሊሉ የተማሩባቸውን አብያተ ጉባኤያት ነው። እርሳቸው እንደገለጹልኝ መምህራቸው የኔታ አክሊሉ ዜማውን በወገራና በፋርጣ ከተማሩ በኋላ፤ ለቅኔ ጎጃም ተሻግረው ብቸና ጊዮርጊስ ከመምህር ውብሸት እስከ ዘረፋ እና እስከማስነገር ደረሱ። ከዚህ በኋላ ከመምህር ያሬድ ዘንድ እንደገና ከተማሩ በኋላ ለሦስተኛ ጊዜ አረፋ መድኃኔዓለም ከግጨው ገብሬ ወርደው ቅኔውን ጠነቀቁ ከዚህ በኋላ ጐጃም ውስጥ አንድ ደብር ላይ ወንበር ተክለው ሲያስተምሩ ቆይተው ቅኔ ዘራፊዎችን ካደረሱ



www.eotcmk.org



*ወላዴ ሊቃውንት የኔታ ጥበቡ*

በኋላ አንዱን ዘራፊ ወንበራቸው ላይ ተክተው፣ አንዱን ይዘው ወደ ዋድላ በመሔድ ወገደት ቂርቆስ ከመምህር ገብረ መስቀል የቅኔውን የዋድላ መንገድ /መንገድ የሚ ባለው የተለየ ዓይነት ወይም በእንግሊዝኛ another approach ነው/ መቀጸል ጀመሩ:: ከእርሳቸው የሚያገኙትን ካሰባሰቡ በኋላም ላስታ አሸተን ማርያም /ላሊበላ አጠገብ/ ወጥተው ተማሩ:: ወደ ደሴ ሔደውም መምህር ቡሩኬ ዘንድ የቀራቸውንና ሌሎችንም ዕውቀቶች ቀሰሙ:: ከዚያም ያስተምሩበት ወደ ነበረው ደብር ተመልሰው ትንሽ ጊዜ ካስተማሩ በኋላ ጎንደር ማኅደረ ማርያም ገቡ:: በዚያ እያሉ ፈተና ገጠማቸው:: በቦታዋ የነበሩ አገልጋዮች ከተማሪዎቻቸው ጋር ተጋጭተው ሲደባደቡ አንድ ተማሪ ሞቶ ሌሎች ቆሰሉባቸው:: በዚህ ጊዜ ቦታውን ለቅቀው እንደገና ጎጃም ዲማ ጊዮርጊስ ወረዱና የሐዲስ ኪዳንና የፍትሐ ነገሥት ትርጓሜን ደብረ ሊባኖስ ተሻግረው ደግሞ ዝማሬ መዋሥዕት፣ ባሕረ ሐሳብ /አቡሻኽር/ ትርጓሜ ተማሩ:: አሁንም እንደገና እዚያው ሰላሌ ስሬ መድኃኔዓለም ወጥተው ከየኔታ ጥበቡ ገሜ አዲስ ዕውቀት ባገኝ ብለው ከጠየቁ በኋላ ወደ አዲስ አበባ ወረዱ:: አዲስ አበባ ደርሰው ብፁዕ ወቅዱስ አቡነ ባስልዮስ ዘንድ እጅ ነሥተው ቦታ ጠየቁ:: እርሳቸውም በትልቅ ደስታ ተቀብለው «መምህራን የሌሉበት አካባቢ ልላክህ» ቢሏቸው መምህር አክሊሉ «ጎንደር ብቻ ይፈቀድልኝ» አሉ:: ወዲያው ፍትሐ ነገሥት ትርጓሜው ታትሞ ስለነበር እርሱን ጠየቁ:: በወቅቱ ከነበሩት አባቶች አንዱ አቡነ ሉቃስ መጽሐፉን ገዙላቸው:: ከዚያ በኋላ ወደ ጎንደር ተመለሱና ደበጋ ሚካኤል ወንበር ተከሉ፤ «እኔም የተማርኩት ከእርሳቸው ዘንድ ነው» ይላሉ የኔታ ጥበቡ ዘዛራ ሚካኤል::

የኔታ ከመምህራቸው ዘንድ ያለውን ሁለገብ ዕውቀት ጊዜ ወስደው ቅኔውን፣ ሐዲስ ኪዳኑንና ፍትሐ ነገሥቱንም ተመርቀው በታል:: እንደ እርሳቸው ገለጻ የኔታ አክሊሉ ዘንድ በነበሩበት ጊዜ ሐሳባቸው ለቦታው ቅርብ ወደነበሩት ገዳማት ማኅበረ ሥላሴ እና እማማ ገዳም ገብቶ መመነን ነበር:: ነገር ግን ለጣዕም /ለቅድስና፣ ለብቃት፣ ለመንፈሳዊ መገለጥ/ የደረሱት መምህራቸው እየተቆጡአቸው ትምህርቱን ሁሉ አስተምረው ሁሉንም ነገር አሳውቀው ለመምህርነት አበቋቸው::

የኔታ ጥበቡ አሁን ባሉበት ቦታ ወንበር የተከሉት በ፲፱፻፶፰ ዓ.ም ነው:: በዚህ መሠረት ሳያቋርጡ በማስተማር ፴፬ኛ ዓመታቸውን ይዘዋል:: በዚህ ጊዜ ውስጥ እጅግ ስመ ጥርና ታዋቂ መምህራንን እንዲሁም እጅግ ብዙ ደቀመዛሙርትን አፍርተዋል:: በአሁኑ ጊዜ እንኳን /ቃለመጠይቁን ባደረግሁበት ወቅት/ ከ፪፻፶- ፫፻ /መጨመር መቀነስ ስላለ/ ተማሪዎች በጉባኤ ቤቱ ይገኛሉ:: ከእነዚህ ውስጥ ፲፪ የቅኔ ዘራፊዎች ከዚሁ ያላነሡ አስነጋሪዎች፣ አሥር የሚያህሉ ደግሞ የሐዲስ ኪዳንና የፍትሐ ነገሥት ትርጓሜ ተማሪዎች አሉአቸው:: ከየኔታ ጥበቡ ከወጡት መካከል የጎንደር መንበረ መንግሥት መድኃኔዓለም የአራቱ ጉባኤያት መጻሕፍት መምህር የሆኑት ሊቀ ሊቃውንት ዕዝራ ሐዲስ፣ የሰዋስወ ብርሃን ቅዱስ ጳውሎስ ከፍተኛ መንፈሳዊ ኮሌጅ የሐዲስ ኪዳን ትርጓሜ መምህር የሆኑት መጋቤ ሐዲስ ስቡሕ አዳምጤ እንዲሁም በቅድስት ሥላሴ መንፈሳዊ ኮሌጅ የዜማና የቅዳሴ መምህር የሆኑት መምህር ሐዲስ ትኩነህን እንደ ምሳሌ ማንሣት ይቻላል:: በየገጠሩ ወንበር የዘረጉና በአዲስ አበባ አድባራት በተለያየ መዓርግ ቤተ ክርስቲያንን የሚያገለግሉትን ቤት ይቁጠራቸው::

እንግዲህ እኚህ ታላቅ ሰው ናቸው እንጨት እየሸጡ ራሳቸውን በሚረዱ መምህር ቤት መደብ ላይ ተኝተው ሲረዱ ያገኘኋቸው:: የኔታን የሚያሳክም ሰው ጠፍቶ አልነበረም:: ቢሰሙ በትምህርት ከወለዷቸው አንዱ እንኳ ይበቋቸው ነበር:: እርሳቸው ግን ይህንንም እንደ ብዙ ርዳታ ያዩታል:: ሌላውንም አይመኙትም:: ለዚህም የበቁት ግን እጃቸው ላይ ምንም ገን ዘብ ባለመኖሩ ብቻ ነው:: የየኔታ ወርኃዊ ደመወዝ በብፁዕ ወቅዱስ አቡነ ተክለ ሃይማኖት ጊዜ ብፁዕ አቡነ ቄርሎስና ብፁዕ አቡነ መርቆሬዎስ ቦታቸውን አይተው ከተመለሱ በኋላ ያስወጡላቸው ስድሳ አምስት ብር ብቻ ናት:: ለየኔታ ይህችውም የምትገኘው በሦስትና በአራት ወራት ውስጥ ነው:: ስትመጣም ለመጽሐፍ መግዣ እንኳን አትበቃቸውም::

በቀድሞው ጊዜ የነበሯቸውን መሬቶች ደግሞ ደብሩን የሚያገለግሉ ካህናት በኑሮ ሲቸገሩ አይተው ለእነርሱና ከምእመናንም በጣም ለተቸገሩት አከፋፍለው ሰጥተዋቸዋል:: ከዚያን ጊዜ ጀምሮ ለበረከት ትንሽ እህል የሚሰጥ ገበሬ ካለ ከዚያች ካለበለዚያም ተማሪዎቻቸው በልመና የሚ ያመጧትን እየተካፈሉ ይኖራሉ:: ይህም ሆኖ እንግዳ መቀበል የማይታጐለው ሥራቸው ነው:: በተገኘው ነገር ያስተናግዱታል:: ቢጠፋ ቢጠፋ እነርሱም እንደ ሠርከ ኅብስት የሚያዩትን በቤተ ክርስቲያኑ ዙሪያ ያለውን የእሸ /ፍሬው የሚበላ ትልቅ ዛፍ/ ፍሬ ለቅመው አፉን ያብሱለታል:: ከዚያም የተማሪዎቻቸው ኮቸሮ ይከተላል::

በአሁኑ ጊዜ ግን ጉባኤ ቤታቸው ታላቅ ፈተና ተጋርጦበታል:: ተማሪዎቻቸው እንደ ዱሮው በልመና መኖር አልተቻላቸውም:: ስለዚህ ብዙዎቹ ወደ ፎገራ ወርደው የቀን ሥራ ሠርተው ጥሬ ሸምተው ቢማሩም የሚዘለቅ አልሆነላቸውም:: ስለዚህ ብዙው ተማሪ ረሀቡ ሲያስቸግረው እየሾለከ ከጉባኤ ቤት እየጠፋ ይሔዳል:: የኔታም ሆኑ ለማስታመም ተከትለዋቸው የመጡት የፍትሐ ነገሥት ትርጓሜ ተማሪያቸው የኔታ ነቢዩ «ትልቁ ችግራችን ምግብና መጠለያ ነው» ይላሉ:: የኔታ ጥበቡ ይህም ሆኖ «ደመወዝ አነሠኝ፣ የምበላው የለኝም» አይሉም:: ደመወዛቸው ስድሳ አምስት ብር እንደሆነ ከገለጹልኝ በኋላ «ይበቃዎታል?» ስላቸው «ምን አደርገዋለሁ?» ነበር መልሳቸው:: ተማሪያቸው የሆኑት መምህር ነቢዩ ግን አኗኗራቸውን ስለሚያውቁት «የንሰኛልስ ቢሉ ምን ያገኛሉና» በማለት የችግራቸውን ጽናት ለስለስ አድርገው ይናገራሉ::

ከእነ የኔታ ጋር የሕይወት ውጣ ውረዳቸውንና የጉባኤ ቤቱን ነገር ስንጨዋወት ከቆየን በኋላ ቀስ እያልኩና ብርታታቸውን እየገመገምኩ የአካባቢውን ገዳማትና አድባራት በተመለከተ ጥያቄዎችን ማቅረብ ቀጠልሁ:: የኔታ አንዱ የሚታወቁበት ጸጋቸው መጻሕፍትን በማንበብ ነው:: ሰው እንዲሰጣቸው የሚጠየቁት ነገር ካለ መጽሐፍ ብቻ ነው:: ገንዘብም ካገኙ ማረፊያዋ መጽሐፍ ነው:: ስለዚህ ብዙ ታሪኮችን ያውቃሉና እኔም ከደብራቸው ዛራ ሚካኤል ጀምሮ ስለሌሎቹም ገዳማት አነጋግሬያቸዋለሁ:: ለመጽሔቱ ያህል ግን የዛራንና የአቡነ ሐራን እንዲሁም የወለተ ጴጥሮስን ገዳምን የተመለከቱትን ብቻ እንመለከታለን::



www.eotcmk.org

# ጥብርያዶስ

ንጉሤ ስሜ

## የስሙ አሰያየምና የሚገኝበት ቦታ

«ጥብርያዶስ» የሚለው ስም በፊት በዕብራይስጡ ጌንሴሬጥ /ኬኔሬት/ ወይም የገሊላ ባሕር በመባል ለሚታወቀው በሰሜናዊ እስራኤል ለሚገኝ ሐይቅ የተሰጠ ነው። /ዘኁል.፴፬፥፲፩፣ ሉቃ.፶፫፥፩-፲፩፣ ማር.፩፥፲፯/ ይህን እጅግ ውብ የሆነ ሐይቅ «ጥብርያዶስ» በማለት እንዲጠራ የወሰነው ሄሮድስ አንቲጳ ነው። ሄሮድስ አንቲጳ ከ፲፱-፳፪ እ.ኤ.አ ውስጥ ከዚህ ባሕር ዳርቻ በስተምዕራብ በኩል አዲስ ከተማ ከቆረቆረ በኋላ ለጢባሪዮስ ቄሳር መታሰቢያ ትሁንልኝ ብሎ ጢባሪያ /Tiberia/ በማለት ጠራት። ስለዚህ ከከተማዋ ዳርቻ ላይ የሚገኘውንም ሐይቅ ጥብርያዶስ በመባል እንዲጠራ ይህች ከተማ ምክንያት ሆነች። ይህ ሐይቅ በገሊላ አውራጃ የሚገኝ በመሆኑና ለናዝሬትም የቀረበ ስለነበር ጌታችን መድኃኒታችን አምላካችን ኢየሱስ ክርስቶስ ከልጅነቱ ጀምሮ በደንብ የሚያውቀውና ያደገበት ቦታ ላይ የሚገኝ ነበር።

በሐይቁም ዙሪያ መግደሎን፣ ቅፍርናሆም፣ ጌንሴሬጥ /ምድረ ገሊላ/፣ ቤተሳይዳና ጌርጌሴኖን የሚባሉ ከተሞችና መንደሮች ይገኛሉ። የጥብርያዶስ ሐይቅ ፳ ኪሎ ሜትር ርዝመትና ፲፪ ኪሎ ሜትር ስፋት ያለው ሲሆን ከባሕር ጠለል በታች በ፪፻፲፪ ሜትር ዝቅ ይላል /ሊቀ ጠበብት ሐረገወይን አገዘና ቀሲስ ስንታየሁ አባተ፤ የመጽሐፍ ቅዱስ ጥናት(አዲስ አበባ፡፲፱፻፺፯) ገፅ.፻፴፮/ ከነዚህም በተጨማሪ ሌሎች ብዙ መንደሮች በጌታችን ዘመን በሐይቁ ዙሪያ ይገኙ ነበር።

የጥንት የእስራኤል ገዢዎች በሮማውያን ተሸንፈው ለሮማውያን ሎሌ የነበሩ መሪዎች ከተሰየሙበት ከመጀመሪያው ሄሮድስ ሐንዳፊር ዘመነ መንግሥት ጀምሮ ከተሞች፣ተራሮችና ባሕሮች /ሐይቆች/ ለብዙ ዘመን ይጠሩበት የነበረውን ስያሜ እየለወጡ አዲስ መስጠት እየተለመደ መጥቷል። ይሔ ሄሮድስም አዲስ ከተማ ቆርቁሮ 'ቂሳርያ' በማለት ከጠራት በኋላ ለአውግስጦስ ቄሳር መታሰቢያ እንዲሆንለት በጀመረው ልማድ የተፈጸመ ነው። /ማቴ.፲፮፥፲፫/።

ዛሬም ቢሆን የጥብርያዶስ ከተማ በነበረበት ቦታ ላይ እስራኤላውያን ብዙ ሕዝባቸውን በማስፈርና ከተማውን በዘመናዊ መንገድ በመገንባት ይኖሩበታል። ዛሬ ላይ ይህች ከተማ በዕብራይስጥ «ቲቬሪያ» በመባል ትጠራለች። ይህም ከጢባርያ ወይም ጢባርዮስ /ጥብርያዶስ/ ጋር ተመሳሳይ ነው። ባሕሩም «ኪኔሬት» ወይም «ባሕረ ገሊላ» እየተባለ ይጠራል። ዛሬ በዚህች ከተማ ላይ ታላላቅ ሆቴሎች፣ ት/ቤቶች፣ ኢንዱስትሪዎች የእርሻ ማዕከሎች /ኪቡትዝ/ ተደራጅተውበታል። /አማከለ ገበየሁ፣ ቅድስት ሀገር (አዲስ አበባ፣፲፱፻፺፪) ገፅ.፻፴፫/



የጥብርያዶስ አካባቢ

## በጥብርያዶስ ሐይቅ ላይ አምላካችን ያስተማረው ትምህርት

አምላካችን ጥብርያዶስንና ከእርሱ ጋር ተያያዥ በሆኑት ነገሮች ላይ ምሳሌ እየመሰለ ብዙ ትምህርቶችን አስተምሮበታል። ይህ እንዴት ይታወቃል ቢሉ ጌታችን ባሕረ ገሊላን /ጥብርያዶስን/ እንደ ዓለም በውስጡ የነበሩ ዓሣዎችን እንደ ሰው፤ ሐዋርያትን እንደ ዓሣ አጥማጆች፣ መረባቸውን እንደ ቃለ ወንጌል መስሎ ባስተማረው ቃል ይገለጣል። ይህንን በሉቃ ፭-፲፩ ላይ 'ሰውን አጥማጆች አደርጋችኋለሁ' ባለው አምላካዊ ቃል እናውቀዋለን።

### ታላቅ ፀጥታ ሆነ /፬፡፴፮/

ጥብርያዶስ የሐዋርያት ትምህርት ቤት ነበረች። ወንጌል እንደሚገልጸው ሐዋርያት በአንድ ወቅት ይህችን ባሕር ሲያቋርጡ በማዕበሉ ብርታት ተጨንቀው ለጌታችን «ስንጠፋ አይገድህምን?» ብለው ከተኛበት ቀስቅሰውታል። እርሱም «እናንተ እምነት የጎደላችሁ፣ስለምን ትፈራላችሁ» በማለት ከገሠጻቸው በኋላ ገና በዓለም ማዕበል/ፈተና/ ትፈተናላችሁ የሚለውን ነገር ገልጾ «ከቶ አትጨነቁ አንዳች ነገር ብትፈልጉ ወደ እኔ ጸልዩ» ብሎ የነገራቸውን ትምህርት በገሃድ ከፈተና ጋር አዋሕዶ አስተምሮአቸዋል። /ማቴ.፰፥፳፯፣ሉቃ.፲፪፥፲፯፡፲፪፥፳፪-፴፬/

ከዚያም ወዲያው ተነሥቶ ነፋሳቱን እና ማዕበሉን ገሠጻው እርሱም ጸጥ አለ። ይህንን ያዩ ደቀ መዛሙርትም እጅግ ፈሩ፤ «ንፋስና ባሕር የሚታዘዙለት ይህ ማን ነው?» አሉ። በእርግጥም ነፋሳትና ማዕበል የሚታዘዙለት ከአምላክ በቀር ማን አለ! ሌሎች ነቢያት ዝናብ ቢያዘንቡ ባሕር ቢከፍሉ ስመ እግዚአብሔርን ጠርተው ነው። አምላካችን ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ግን በሥልጣኑ አዘዘው። እርሱም ቃሉን ሰምቶ ታዘዘለት። ሐዋርያትም በጥብርያዶስ ታዛዥነት ተምረዋል። ይህ ትምህርት ከዓለም መርጦ የጠራቸው የሰማይና የምድር አምላክ መሆኑን የሚያስረዳ ነው።

በሌላኛውም ጊዜ አምላካችን ኢየሱስ ክርስቶስ በዚህች በጥብርያዶስ ሐይቅ ላይ ሐዋርያት ብቻቸውን በጀልባ ሆነው እንዲያቋርጡ አዘዛቸው። እነርሱም ብቻቸውን በሌሊቱ ክፍል ሐይቁን እያቋረጡ ሳለ ከባድ ነፋስ ከጀልባዋ ፊት ለፊት መጥቶ ማዕበል አስነሣ። ጀልባም መሔድ አልቻለችም። ነፋሱ ሸራዋንና





www.eotcmk.org

መወጠሪያውን ወደ ኋላ እየገፋ ያንገላታት ነበር፡፡ ከትንሽ ጊዜ በኋላ ዐውሎው አይሎ ንፋሱም ማዕበሉን ወደ ጀልባው ውስጥ ይጨምረው ነበር፡፡ ውኃውም እንደ ሣር ክምር እየተቆለለ ጀልባዋን የሚገለብጣት እስኪመስል ድረስ ያነሣታል፡፡ ሐዋርያትም ከማዕበሉ የተነሣ ተጨነቁ፤ ተሰቀቁም፡፡ ከሌሊቱ በዘጠኝ ሰዓት ሲሆን አምላካችን በባሕሩ ላይ እየተራመደ መጣ፡፡ ይህንን ያዩ ደቀ መዛሙርትም ታወኩ፡፡ ነገሩ ምትሐት እንጂ እውነት አልመሰላቸውም ነበር፡፡ ይህንን ባስተዋሉ ጊዜ «እውነት አንተ የእግዚአብሔር ልጅ ነህ ብለው ሰገዱለት» /ማቴ.፲፬፥፳፯፥፴፫/፡፡ በዚህች በባሕረ ገሊላ ወይም ጥብርያዶስ ላይ አምላክ ከተፈጥሮ ሕግ በላይ የሆነና ለተፈጥሮ ሕግና ሥርዓትን አበጅቶ የሰጣቸው፤ የሠራላቸውም እርሱ እንደሆነ አሳይቶበታል፡፡

## እግዚአብሔር ያደረገልህን ታላቅ ነገር ንገር /ሉቃ.፰፡፴፱/

ጌታችን የጥብርያዶስን ባሕር ማዕበልና ንፋሳቱን ከገሠጸ በኋላ በንጋቱ ወደ ጌርጌሴኖን ሀገር መጣ፡፡ በዚያም ሀገር ላይ የነበሩ ሕዝቦች ከተማ ሠርተው ተቀምጠው ነበር፡፡ በመንጋም በገዙዩ የሚኖር እርያ ሁላቸውም እያረቡ ይህንን እርያ ለሥጋውና ለወተቱ እያሉ እጅግ ይጠብቁት ነበር፡፡ ከዚያችም ከጌርጌሴኖን ከተማ ዳርቻ ላይ ደግሞ የመቃብር ሥፍራቸው ነበር፡፡ በዚያም ሥፍራ ሁለት ጋኔን ያሳበዳቸው ሰዎች እርቃናቸውን ሆነው ይኖሩ ነበር ጋኔኑም እጅግ ክፉ ስላደረጋቸው ሰው ሁሉ በዚያ በኩል አይሔድም፡፡

በቀትር ጊዜ ራሳቸውን በድንጋይ ያቆስሉና ይጮሩ ነበር፡፡ ሰውንም ባለፈ ጊዜ ድንጋይ እየወረወሩ ይመታሉ፡፡ የከተማው ሰዎች ጋኔኑ እንዲርቅላቸው ብለው በእግር ብረትና በሰንሰለት ያስሯቸው ነበር፡፡ አጋንንቱ ግን እግር ብረቱንና ሰንሰለቱን እየሰበረ ወደ መቃብሩ ቦታ ይነዳቸዋል፡፡ ጌታችን ግን ከታንኳዋ በወረደ ጊዜ ወዲያው ጋኔን ያደረባቸው ሰዎች ወደ እርሱ መጡ፡፡

«ኢየሱስ ሆይ፣ የእግዚአብሔር ልጅ ከአንተ ጋር ምን አለን… ጊዜው ሳይደርስ ልታሰቃየን ወደዚህ መጣህን?» አሉት ተሰማርተው ወደ ነበሩት እርያዎች እንዲገቡም ለመኑት፡፡ ይህንን ያሉት ግን እርያዎቹን ወደ ባሕር /ጥብርያዶስ/ ለማስጠምና በዚያ ምክንያት የከተማው ሕዝብ እንስሳቶቻችንን አጠፋህብን ብለው እንዲጣሉት እርኩስ ዘዴ በመወጠን ነው፡፡ አምላክም ሁሉን አዋቂ ነውና «ግቡ» አላቸው፡፡ በዚያን ሰዓት ወደ እርያዎቹ ገቡ፡፡ እርያዎቹም ጥቂት የደመ ነፍስ አእምሮ ነበራቸውና ያንን አጥተው ወደ ገደል ተወርውረው ወደ ባሕር ሰጥመው አለቁ፡፡ አምላካችን ኢየሱስ ክርስቶስም ከባሕሩ በታች ያለች መሬት ተከፍታ አጋንንቱ ወደ ሲኦል እንዲገቡ አደረጋቸው፡፡ ይህንን ማድረግ ዓላማው አድርጎ ወደ ጌርጌሴኖን የመጣው አምላክ አጋንንቱን «ወደ እርያው ግቡ» ሲላቸው ጥፋታቸው እንደደረሰ የማወቅ ችሎታ አልነበራቸውም፡፡ ከአጋንንት ሥቃይ የዳነውን ሰው ግን ልብስ አለበሰው፡፡ «ሂድ ወደ ትውልድ ሀገርህ ግባ ጌታ ያደረገልህንም አውራ?» አለው፡፡ ያልታደሉት የጌርጌሴኖን ሰዎች ግን ከሀገራችን ሒድልን ብለው ለመኑት፡፡

ባሕረ ገሊላ ወይም ጥብርያዶስ አጋንንት የሰጠሙባት/ወደ ሲዖል/ በመሆንዋ አምላክ ታላቅ የሆነ ድኅነትን ፈጽሞባታል፡፡ ባለፉት ዘመኖች ለቃሉ ተገዝታ ከማዕበልና ከነፋሳት ጸጥ እንዳለች እርኩሳን አጋንንትም ወደ ሲዖል እንደወርዱ አድርጋለች፡፡ በዚህም የምጽአትን መጭ ጊዜ የትንቢት መስታወት ሆና ለኛ ታንጸባርቃለች፡፡ ሰው በውኃ መልኩን እንዲያይ ጥብርያዶስም ላይ ጌታ የፈጸመው ተአምር ምጽአትን እንድናይ ያደርጋል፡፡ ይህ እንዴት ነው ቢሉ እርያዎቹ የአይሁድ ምሳሌዎች ናቸው፡፡ በእነርሱ ላይ አድረው አምላክን አስቀለዋልና፡፡ ከዚያም ደግሞ አሕዛብ ሮማውያን እንዲጣሉት ምክንያት ሆነዋል፡፡ በዚህም ሥራቸው እነርሱና ያደረቦቸው ጋኔንን/ሠሪውንና አሠሪውን/ ሁለቱንም አምላካችን በምጽአት ፈርዶ በሲዖል ያሰጥማቸዋልና የምጽአት ፍርድን ያስታውሰናል፡፡ /አንድምታ ወንጌል ዘማቴዎስ ፣ዘሉቃስ/ ይህንን አምላካችን ሲገልጽ ሥጋን የሚገድሉትን አትፍሩ ይልቁንም ከገደለ በኋላ ወደ ገሃነም ለመጣል ሥልጣን ያለውን ፍሩ ብሏል፡፡ /ሉቃ.፲፪፥፬-፭/

**በእውነትም ዛሬ ከጥብርያዶስ ዳርቻዎች የቆመ ሰው ቢኖር አምላክ ደቀ መዛሙርቱን ሲጠራ እንዲሁም ከትንሣኤ በኋላ ለሐዋርያነት ሲያጸና የቆመበት አለመሆኑን እንዴት እርግጠኛ መሆን ይችላል?**

## ጌታችን በጥበርያዶስ ምን ምን ተአምራትን አደረገ

### ፩. በዓሣ ሰራቂዎች ላይ ፈረደ

በዚህ ሐይቅ ላይ ጌታችን መድኃኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስ እጅግ ብዙ ተአምራትን አድርጓል፡፡ ጌታችን ገና ወጣት ሳለ በተአምረ ኢየሱስ ላይ እንደተጻፈው ግሩም የሆነ ተአምርን በዚህ ሐይቅ ዳርቻ ላይ አድርጓል፡፡ በዚሁ መጽሐፍ ተአምር ሃያ ስምንት ላይ እንዲህ የሚል ተጽፎአል፡፡

«ጌታ ኢየሱስ በጥብርያዶስ ባሕር ዳርቻ ቆሞ ነበር… [መርከበኞች መጡና] … አንድ ሰው [ከመርከበኞቹ መሐል] እየጮኸ ወደ እርሱ መጥቶ. . . 'በዛሬይቱ ሌሊት የአሠገርኩትን ዓሣ ሁሉ ጓደኞቼ ሰርቀውኝ እነሆ ባዶ እጄን ቀርቼ ለድህነት ዳረጉኝ' ብሎ ተናገረ… [ዓሣውን ሰረቁኝ ያላቸውም ሰዎች መጡ]… [ጌታንም ባዩ ጊዜ 'እርሱ በመካከላችን ይፍረድ' አሉ ጌታም በተሰረቀው ሰው መርከብ ቆሞ] «የተሰረቅህ ዓሣ ሆይ ወደ አጠመደህ መርከብ ግባ ባለ ጊዜ ዓሣዎቹ ከሌላኛው መርከብ እየተወረወሩ ጌታ ወደነበረበት፣ ወዳቆመው መርከብ ገቡ» በማለት ይገልጸዋል፡፡

### ፪. ሐዋርያትን ጠራ

ጌታችን ከዚህ በኋላ ለመጀመሪያ ጊዜ ሐዋርያትንም የጠራበት ሐይቅ ይህ የጥበርያዶስ ባሕር ነው፡፡ በዚህ ባሕር አጠገብ ጌታችን ሲያልፍ ስምዖንና እንድርያስ ዓሣ ለማጥመድ መረባቸውን ሲጥሉ ተመለከተ ወዲያውም ጌታችን «ሰዎችን አጥማጆች አደርጋችኋለሁና መረባችሁን ጥላችሁ በኋላዬ ተከተሉኝ» አላቸው እነርሱም መጡ፡፡ ከነርሱም ትንሽ ፈቀቅ ብሎ ዘብዴዎስና ሠራተኞቹ ከልጆቹ ከያዕቆብና ከዮሐንስ ጋር እንዲሁ ዓሣ ሊያጠምዱ መረባቸውን ያዘጋጁ ነበር፡፡ አምላካችንም «ተከተሉኝ» አላቸው፡፡ እነርሱም አረጋዊውን አባታቸውን፣ ከባሕር የጨመሩትን መረባቸውንና ያሠግሩበት የነበረውን ታንኳ ጥለው ተከተሉት፡፡ በዚህም ጌታችን የዓለም ሰዎች ወንጌልን ይማሩ ዘንድ መምህራን አድርጎ የመረጣቸውን ሐዋርያትን የጠራበት፣ የመጀመሪያውንም የወንጌል ሥራውን የፈጸመበት በዚህ ቅዱስ ሐይቅ ላይ ነው፡፡ /ሉቃ. ፭-፲፩/

በገሊላ ባሕር ዳርቻ ሕዝብ ጌታችንን ከብቦ ነበርና ቦታ ሲያጣብቡት ጊዜ የስምዖን የነበረች ጀልባ ላይ እንዲወጣ



www.eotcmk.org

ስምዖንን ጠየቀው፡፡ ከዚያም ስምዖንን ከዳርቻው ጀልባውን ጥቂት ፈቀቅ ያደርግ ዘንድ ለመነው፡፡ ይህንን ካደረገ በኋላ ጌታችን በጀልባዋ ላይ ሆኖ ሕዝቡን አስተማራቸው፡፡ ሕዝቡም ትምህርቱን ሰምተው ወደየቤታቸው ከሔዱ በኋላ ስምዖንን መረብህን ወደ ባሕሩ ጣለው አለው፡፡ ስምዖን ግን «ጌታ ሆይ ሌሊቱን ሁሉ ስንለፋ አድረን አንዳች አላገኘንም ነገር ግን ይህን አድርግ ብለህ ካዘዝከኝ ስለ ትዕዛዝህ/ቃልህ/ ስል መረቡን እጥላለሁ» አለው፡፡ ይህንንም ባደረገ ጊዜ መረቡ እስኪበጠስ ድረስ ዓሣ ያዘ፡፡

ዮሐንስና ያዕቆብም ጥቂት ፈቀቅ ብለው በጀልባቸው ነበሩ እነርሱንም ጠራቸው በጀልባቸው ዓሣውን ገልብጠው ረዱአቸው፡፡ ስምዖን ግን ጌታ ያደረገው ተአምራት ገብቶት እግሩ ላይ ወድቆ «አቤቱ እኔ ኃጢአተኛ ሰው ነኝና ከእኔ ተለይ» ብሎ አዘነ፡ ክርስቶስ ግን «አትፍራ፤ ከዛሬ ጀምሮ ሰውን አጥማጆች አደርጋችኋለሁ» አለው፡፡ ከዚያን ጊዜ ጀምሮ ያላቸውን ሁሉ ትተው ተከተሉት፡፡

## ፫. ከሐዋርያቱ ጋር ሆኖ የሠራቸው ሌሎች ተአምራት

ከባሕረ ገሊላ ተነሥተው ከጌታችን ጋር በመላዋ ምድረ እስራኤል ለሦስት ዓመት ከሦስት ወር አብረው ዞሩ፡፡ በነዚህም ዘመናት በዚህች ባሕር ላይ አምላካችን ብዙ ተአምራትን ገልጿል፡፡ ከነዚህም መካከል የባሕሩን ማዕበልና ነፋሳቱን በመገሠጽ ጸጥ እንዲሉ አድርጓቸዋል /ማቴ.፰÷፳፫/ በተቀደሱት እግሮቹም በዚህ ባሕር ላይ እየተራመደ በማዕበሉና በነፋሱ ብርታት የተነሣ ተጨንቀው ወደ ነበሩት ሐዋርያት በመምጣት እንዲረጋጉ አምላክነቱንም እንዲገነዘቡ ያደረጋቸው በዚህችው በጥበርያዶስ ባሕር ላይ ነው፡፡

## ፬. ከዓሣ ሆድ የነበረ ስጣጢራን አውጥቶ ለግብር ማቅረቡ

በሌላ ጊዜ አምላካችንም በቅፍርናሆም ከተማ ላይ በደረሰ ጊዜ ለቤተ መቅደሱ እንደ ሙሴ ሕግ ግብር ይገብር ዘንድ የሚቆጣጠሩት አይሁድ ወደ ቅዱስ ጴጥሮስ ቀርበው መምህራችሁ ሁለቱን ዲናር አይገብርምን? ብለው ጠየቁት፡፡ እርሱም «አዎን» አላቸው፡፡ ወደ ጌታችንም በተመለሰ ጊዜ «ወደ ገሊላ ባሕር ሒድ መረብህን ጣል መጀመሪያ የወጣው ዓሣ አፍ ውስጥ ለእኔና ለአንተ የሚበቃ «ስጣጢራ» የሚባል ሣንቲም ታገኛለህ፡፡ ሔደህ ይህንን ስጣቸው» አለው እርሱም ጌታችን እንዳለው አደረገ /ማቴ.፲፯÷፳፯/፡፡ በዚህም የኦሪት ግብር የሚገባው አምላክ መሆኑን ገልጾ የሰውን ሥጋ ፍጹም እንደ ተዋሐደም ሲያጠይቅ የኦሪቱን ሕግ ፈጸመ፡፡

## ፭. ትንሣኤ እግዚእ እና ጥብርያዶስ

ጌታችን በትንሣኤ ከተነሣ በኋላ ከተገለጠባቸው ቦታዎች መካከል አንዷ ይህችው የገሊላ ባሕር ነበረች፡፡ ሐዋርያት ከጌታችን ስቅለትና ትንሣኤ በኋላ ሐዘን የአእምሮአቸውን ጸጥታ እንደ ማዕበል እየመታው ይኖሩ ነበር፡፡ በአንደኛው ቀን «አምላካችን ካደረበት እያደርን፣ ከዋለበት እየዋልን፣ የእጆቹን በረከት እየበላን፣ የቃሉን ትምህርት እየሰማን ኖረን ነበር፡፡ አሁን ግን አይሁድ ሰቀሉት፤ በሦስተኛውም ቀን ተነሣ፡፡ ከዚህ በኋላ ግን እኛ ምንም ተስፋ የለንም፡፡ ስለዚህ ወደ ቀድሞ ኑሮአችን እንመለስ» ብለው ወደ ገሊላ ባሕር/ጥብርያዶስ/ ሔዱ፡፡ ሌሊቱን ሁሉ ሲለፉ አደሩ፤ ምንም አላገኙም፡፡ በነጋም ጊዜ በባሕሩ ዳርቻ ጌታ ቆሞ ነበር፤ እነርሱ ግን አላወቁትም፡፡

ወደ ሐዋርያነት የጠራቸው አምላክ ሲጠራቸው ለመጀመሪያ ጊዜ በዚህችው ባሕር እንዳደረገው አሁንም በቀቢጸ ተስፋ የነበሩትን ሐዋርያት እርሱ መሆኑን ያውቁ ዘንድ በዚያው ዓይነት ሁናቴ ተገልጦ አናገራቸው፡፡ «ልጆች አንዳች የሚበላ አላችሁን» አላቸው፡፡ እነርሱም «ሌሊቱን ሁሉ ስንለፋ አደርን ግን ምንም አልያዝንምና የለንም» አሉት፡፡ «መረባችሁን በቀኝ ጣሉት ታገኛላችሁ» አላቸው፡፡ እንደ ትእዛዙም አደረጉ፤ መረባቸውም በዓሣ ተሞልቶ ስበው ማውጣት አቃታቸው፡፡

በዚህን ጊዜ ይህንን ታሪክ ከዚህ ቀደም ኖሮ ያለፈበት ዮሐንስ ዓይነ ልቡናው በራ፡፡ ወደ ሐዋርያትም የጠራው አምላኩ ወደ ሕይወቱ የመጣበት ቀን ጠርቶ ታየው፡፡ ያች ቀን ትዝ ብላው ከዛሬዋ ጋር ገጠመች አስተዋለም፡፡ ቀና ብሎ ቢመለከት አምላኩ ለመጀመሪያ ጊዜ ሲጠራው ያደረገውን ተአምር እየደገመና እያስተማረው እንደሆነ ተረዳ፡፡ አይቶም አወቀው፡፡ ለቅዱስ ጴጥሮስም «ጌታ እኮ ነው» ብሎ ቀስ ብሎ ነገረው፡፡ ቅዱስ ጴጥሮስም እንደ ዮሐንስ ያለፈው ሕይወቱ ሁሉ ትዝ አለው፡፡ ወደ ባሕሩም ውስጥ እርቃኑን ሊሸፍን ገባ፡፡ ልብስ ከለበሰ በኋላ ወደ አምላኩ መጣ፡፡

ሐዋርያት ከአሁን በኋላ ዳግመኛ ተስፋ የሚቆርጡ አይሆኑም፡፡ ከትንሣኤው በኋላም ደግሞ አምላክ «ኑ ተከተሉኝ ሰዎችን አጥማጆች አደርጋችኋለሁና» ያለው ቃል በልቦናቸው አስተጋብቷልና፡፡ እነርሱም ባሕረ ገሊላን ለአንዴና ለመጨረሻ ጊዜ ተለዩአት፡፡ አምላካቸውን እስከ ዓለም ዳርቻም ተከተሉት፡፡ በውቅያኖሱና በባሕሩም ማዕበል /አላውያን ከሐዲያን ባመጡባቸው መከራ ሥጋ/ አልተሰቀቁም፤ ዓሣን /ሰዎችን/ የሞሉባቸው መረባቸውም /ቃለ ወንጌል ትምህርታቸው/ አልተበጠሰም፡፡ ከባሕሩ ባሻገር ወደነበረችውና ጌታም ቆሞባት ወደነበረች ሰላማዊ ወደብ/ዳርቻ/ ግን መንግሥተ ሰማያት ለዘላለም ተሻግረው ገብተዋል፡፡



ሐዋርያት በጥብርያዶስ ዓሣ ሲያጠምዱ

ወደ ገጽ ፴፱ ዞሯል



www.eotcmk.org

# የሴቶች አለባበስና አጋጊያጥ በቅዱስ ዮሐንስ አፈወርቅ ትምህርት

ኃይለኢየሱስ መርሻ

ቅዱስ ጳዉሎስ ግን ከሴቶች የበለጠ የሚጠበቅ የሚፈለግ ነገር አለ ይላል:: ራሳቸውን የሚያስጌጡበት «ሴቶች በሚገባ ልብስ፣ ከእፍረትና ራሳቸውን ከመግዛት ጋር ሰውነታቸውን የሸልሙ፤ እግዚአብሔርን እንፈራለን ለሚሉት ሴቶች እንደሚገባ መልካም በማድረግ እንጂ በሽሩባና በወርቅ በዕንቁ ወይም ዋጋው እጅግ በከበረ ልብስ አይሸለሙ::» /፩ጢሞ.፪ ÷ ፲/

'የሚገባ ልብስ' ማለት ምን ማለት ነው? እንዲህ ዐይነቱ ልብስ ያማሩ ቢያስመስላቸውም ባያስመስላቸውም የተጋነኑ ጌጣጌጦች ሳይጨመሩበት በሚገባ ይሸፍናቸዋል:: ታዲያ የሚገባ ልብስ ምን ማለት ነው? ሥነ ምግባሩስ ምንድን ነው?

እግዚአብሔርን ለጸሎት ስትቀርቡት ፀጉራችሁን በመሠራትና በወርቅ ጌጣጌጦች ነውን? የመጣችሁት ዳንስ ቤት ነውን? ሰርግ ቤት ነውን? ግብረ ሰዶማዊያን በዓል ላይ ነውን? በዚያ ፀጉርን መሠራት፣ ውድ ልብሶችን መልበስ የተለመዱ ወቅታዊ ጉዳዮች ናቸው:: እዚህ ግን አንዱም አይፈለግ:: የመጣችሁት ለመጸለይ፤ በታላቅ ትሕትና ኃጢአታችሁ ይሠረይ ዘንድ ልመናችሁን ለማቅረብ ነው:: በደላችሁን በጥልቀት ለመንገር፤ በተስፋም ለወደፊቱ እግዚአብሔርን ደስ ለማሰኘት ነው::

ራሳችሁን ለምን አታስጌጡም? ይህ በትሕትና ልመናውን የሚያቀርብ ሰው ዓይነት ልብስ /ቀሚስ/ አይደለም:: በጥልቀትስ እንዴት ድምፃችሁን፣ ሕማማችሁን፣ ሐዘናችሁን ማሰማት ትችላላችሁ? እንዴትስ ማልቀስ ትችላላችሁ? ልዩ በሆነ ሁኔታ ለብሳችሁ እንዴትስ በተመስጦ መጸለይ ይቻላችኋል? ካለቀሳችሁም እንባችሁ በሌሎች ዘንድ አስቀያሚ ነው:: በጸሎት ወቅት የምታለቅስ ሴት ወርቅ ማድረግ አይገባትም:: እንዲህ የሚያደርጉ ግን አሉ:: ይህ ግን ማስመሰል ነው:: በምኞትና ከሚገባው በላይ ገንዘብን ማውጣት ከለመደ አባካኝ ነፍስ እንደሚወጣ እንባ አይደለምን? ከማስመሰላችሁ ጋር ወግዱ! እግዚአብሔር አይሾፍበትም፤ አይቀለድበትም!

ይህ በመድረክ ላይ እንደሚያሳዩ የደናሾችና የተዋንያን ልብስ ነው:: እንዲህች ዓይነቷ ሴት በምንም መልኩ በማስተዋልና በማፈር ልትጌጥ እንደሚገባት ትሑት ሴት ልትሆን አትችልም::

ስለዚህ ሴተኛ አዳሪዎችን አትኮርጁ:: በዚህ አለባበሳቸው ብዙ አፍቃሪዎቻቸውን ማርከዋል:: በዚህ ብዙዎች ከጸጋው ተራቁተዋል:: ከጌጣጌጦቻቸው አንዳች ጠቀሜታ ከማግኘታቸው ይልቅ ብዙዎችን በዚህ ጠባያቸው አቁስለዋል:: በዚያች በፍርድ ቀን የሰዎችን ሁሉ ምስጢር በሚገልጠውና በሚፈርደው ጌታ ፊት ዘማዊቷ ሴት የትሕትና ጠባይ ሊኖራት ቢችልም ከዚህ ጠባዩዋ ምንም ጥቅም አታገኝም:: ስለዚህ ትሑቷ ሴት በዘማዊነት አለባበሷ ከቀጠለች ያላትን ንጽሕና ታጣለች:: በዚህ አስተያየት ብዙዎች ተጎድተዋል:: «ሌላው ሰው ቢጠረጥረኝ ምን ላደርግ እችላለሁ?» ትላላችሁ:: እናንተ ግን ሁኔታችሁን በአለባበሳችሁ፣ በአተያየችሁና በሰውነታችሁ እንቅስቃሴ ትገልጡታላችሁ::

ሣራ ብእሲቱ ለአብርሃም



በዚህ ምክንያት ነው ቅዱስ ጳውሎስ ስለአለባበስ፣ ራስን ስለመከናነብ ራስን ስላለማራቆት በአጽንኦት የሚናገረው:: የሀብት መገለጫ የሆኑትን እንደወርቅ የአንገት ጌጥና ውድ ማራኪ ጌጦችን የመሳሰሉ ቅዱስ ጳውሎስ የሚከለክል ከሆነ ምን ያህል በተጠና መልኩ ለጌጥ እንደተዳረጉ የሚያመለክቱትን/ የሚያሳብቁትን/ አንገትን እያሰገጉ መሔድን፤ አጥፊ በሆነ መልኩ በዐይን እየጠቀሱ፣ በእግራቸው እያረገዱና እያማቱ የሚሔዱትን፤ በተኮረጀ ድምፅ የሚያወሩትን፣ የሚቅለሰለስና የመባባት ገጽታ የሚያሳዩትን፣ ዐይን የሚያቀልሙትን/ መኳኳልን/፣ ካባንና ቦዲ ሲለበስ የሚደረገው ልዩ ጥንቃቄ፣ በልዩ ሁኔታ የሚሠራው የሐር መጎናጸፊያ ልብስና ውጥርጥር የሚያደርገው ጫማማ እንዴት መወገድ አይገባቸው ይሆን?

«በሚገባ ልብስና በእፍረት» ብሎ ሲናገር እነዚህን ሁሉ በመነካካት ነው:: እነዚህ ነገሮች ለሴት ክርስቲያኖች ሕይወት አሳፋሪና የማይገቡ ናቸውና::

አጥብቄ ከልብ እማልዳችኋለሁ እባካችሁ ታገሱኝ:: በቀጥታ የምወቅሳችሁ እናንተን ለማቁሰል ወይም ለማሳመም አይደለም:: የኔ ዓላማም አይደለምና:: ዳሩ ግን ከበጎቼ የማይገቡ ነገሮችን ለማስወገድ እንጂ:: እነዚህ ክልከላዎች ባል ላላቸው ሀብታምና ቅንጡ ሴቶች ከሆኑ፤ ድንግልና አላቸው ተብለው ለሚታወቁ ምንኛ የበለጠ ይገባ ይሆን? ዳሩ ግን ፀጉሯን የምትሠራና በወርቅ የምታጌጥ ምን ዐይነት ድንግል ናት ልትሉ ትችላላችሁ? ውድ ባልሆነ አለባበስ ጌጠኛ እንደሆኑ ሊያስቡ ይችላሉ:: እነዚህ በራሳቸው ምንም ማለት ባይሆኑም::

«ለእናንተም ጠጉርን በመሸረብና ወርቅን በማንጠልጠል ወይም ልብስን በመጎናጸፍ በውጭ የሆነ ሽልማት አይሁንላችሁ:: ነገር ግን በእግዚአብሔር ፊት ዋጋው እጅግ የከበረ የዋህና ዝግተኛ መንፈስ የለውን የማይጠፋውን ልብስ ለብሶ የተሰወረ የልብ ሰው ይሁንላችሁ»
፩ኛ ጴጥ.፫÷፫



www.eotcmk.org

በእርግጥ በወርቅ የሰውነት ገጽታቸውን ካስጌጡት ይልቅ በተራ ልብስና አለባበስ ያሉትን ልታጠና ትችላለህ:: በወርቅ በጣም ጥቁር በሆነ በኅብረ ቀለማት ባሸበረቀ ገመድ በጡታቸው መታጠቂያ አጠገብ ዙሪያ /በመድረክ ዳንሰኞች በልዩ ሁኔታ እንደሚለብሱት/ በታጠቁ ጊዜ በዚህ አለባበሳቸው ልብሱ ወይ ስፋት ያለው አልያም ተሸብሽቦ /ተጨማዶ/ በጣም አጭር አይደል፤ ግን በእነዚህ መካከል ነው:: ደረት ላይ የሚለበሰው ልብስ ብዙ ቦታ ተጣጥፎ የሚደረግ መሆኑ ከማንኛውም የሀር መታጠቂያ የበለጠ ምስጢራዊ በሆነ መልኩ የሚስብ ሆኖ ለመታየት አይደለምን? ከጥቁረቱ የተነሣ የሚያብረቀርቀው ጫማ ሹልና ተቀብቶ የተዋበ እንዲመስል

> «የምንጌጠው ለዝሙት አይደለም» ልትሉ ትችላላችሁ:: አዎ ምናልባትም ላይሆን ይችላል:: ግን ለመደነቅ ነው:: ለመደነቅ ስትሉ ይህን ማድረጋችሁ አያሳፍራችሁምን? እናንተ ግን አሁንም መልሳችሁ «በእርግጥ ነው፤ ግን በቃ ዕድሌ ነው፤ በደንብ ለብሻለሁ፤ ለዚህ ዐይነቱ ስሜት ግን አይደለም» ትላላችሁ:: ለኔ ያላችሁትን እግዚአብሔር ያውቃል::

ነው:: በመሆኑም የጫማውን ሶል /መረገጫ/ ለማየት እንኳ አዳጋች ነው:: ምንም እንኳ ፊታችሁን በእርግጥ ባትቀቡትም ፊታችሁን እስኪያማችሁ ድረስ በመታጠብ ጊዜ ታጠፋላችሁ:: እንዲሁም ንጣቱ ከፊታችሁ ንጣት የበለጠውን ዐይነርግቡን በግንባራችሁ ላይ ታደርጋላችሁ፤ በላዩ ላይም የራስ ማሰሪያውንም ትደርባላችሁ፤ ነጩ ከጥቁሩ ጋር እንዲሔድላችሁ:: በዚህ ሁሉ መሀል የቀሚስ ከንቱነት የለምን? እርሱ ብቻውን ምን ጠቀመ? በማያቋርጥ ሁኔታ ዐይናችሁን እያንከባለላችሁ ስትታዩ፣ የሐር መጎናጸፊያችሁን ስትለብሱ ጥበባዊ በሆነ መልኩ አንዳንዴ ስትሽኮረመሙ /ስትደበቁ/ አንዳንዴ ደግሞ የመጎናጸፊያውን ቁልፍ ስትከፍቱና ስትዘጉ ያየ አንድ ሰው ምን ሊል ይችላል?

ለዚህም ደግሞ የሐር መጎናጸፊያውን ልዩ ውበት ለማሳየት የራስ ልብሱን ሙሉ በሙሉ በራሳችሁ ላይ ትጠመጥሙታላችሁ:: ከማንኛውም የወርቅ ጌጥ የበለጠ ስለ አካሔዳቸውና ስላሏችሁ ሌሎች የማስመሰያ ሥልቶች ልንናገር እንችላለን::

የተወደዳችሁ ልጆቼ እግዚአብሔርን እንፍራው:: ስለውጫዊው ጌጦቻቸው በጣም ስለሚጨናነቁት የዕብራውያን ሴቶች ነቢዩ የተናገረውን እንስማ፦ «በመታጠቂያ ፈንታ ገመድ፤ ፀጉርንም በመንቀስ ፈንታ ቡሃነት በመጐናጸፊያ ፈንታ ማቅ ይሆናል::» /ኢሳ.፫÷፳፬/ እነዚህ ነገሮችና ሌሎች ብዙ ጌጣጌጦች ማለትም ለመታያና ለመማረኪያ ብቻ የሚፈለሰፉ ጌጦች ከወርቅ ጌጥ የበለጠ በስውር የመታየትን ነገር አጉልተው ያሳያሉ:: እነዚህ ጥቃቅን ስሕተቶች አይደሉም:: እግዚአብሔርን የማያስደስቱም ጭምር ናቸው እንጂ:: እነዚህ በድንግልና ራስን ጠብቆ የመኖርንም ነገር ሁሉ ለማጥፋት በቂ ናቸው::

አንቺ ልጃገረድ /በድንግልና ያለሽ/ ሆይ ስለምን የሰው አፍቃሪ ለመማረክ ትፈልጊያለሽ? ሙሽራሽ ክርስቶስ አለልሽ:: ያንን ብታደርጊ እንደዘማዊት ሴት ሊፈርድብሽ ይችላል:: እርሱን በሚያስደስተው ጌጥ በንጽሕና፣ በመታዘዝ በተከበረ ልብስና በማፈር በማስተዋልም ለምን አትጌጪም?

ይህ ማራኪ የሚመስለው ጌጣችሁ እውነተኛ ዋጋ እና ክብር የሌለው ነው:: በእንዲህ ዓይነቱ ያልተረጋጋ ስብእና እየባሱ ከሔዱ ሴተኛ አዳሪንና ደናግላንን ከእንግዲህ መለየት አንችልም:: የልጃገረድ ቀሚስ በተጠና መልኩ የሚዘጋጅና ለመታየት የሚዘጋጅ መሆን የለበትም:: ልሙጥና ለማስጌጥ ብዙ ያልተደከመበት መሆን አለበት እንጂ:: አሁን ግን ቀሚሶቻቸው /አለባበሳቸው/ እንዲታይላቸው ብዙ ሰው ሠራሽ ጌጦች አሏቸው::

አንቺ ሴት ሆይ ይህን አስቀያሚ ሥራሽን አቁሚ:: ይህን ጥንቃቄያችሁን ወደ ውሳጣዊው ውበት ወደ ነፍሳችሁ አሻግሩት:: ለውጫዊው ጌጥ ብዙ ወጪ የሚያስወጣችሁ ገንዘብ የውስጣችሁን ውበት አያመጣውም:: ለውጫዊ ውበት ትኩረት የሚሰጥ ሰው ውሳጣዊ ውበትን ይንቃል:: ለአፋዊ /ለውጫዊ/ ውበት ትኩረት የማይሰጥ ከሆነ የትኩረቱን አቅጣጫ ሁሉ ወደ ውስጥ ያደርጋል::

«ያሳዝናል! መናኛ ልብስ፣ የቆሸሸ ጫማና የማይገባ ልብስ ለብሻለሁ፤ በእነዚህ ልብሶች ላይ ምን ዐይነት ጌጦች አሉ?» አትበይ:: ራስሽን አታታይ:: ቀደም ብዬ እንደተናገርኩት ገጽታን በጥናት /አስበውበት/ ለመለወጥ /ለማስዋብ/ በውድ ልብስ ካጌጡት ይልቅ ያላጌጡት የባሱ ናቸው::

በኋላ ደግሞ ራሳችሁ ለራሳችሁ ይቅርታ ብላችሁ ወደ'ኔ ትመጣላችሁ:: ዳሩ ግን እነዚህን ነገሮች ስታደርጉ ልባችሁንና መንፈሳችሁን የሚመረምርና የሚያውቅ እግዚአብሔርን ምን ልትሉት ነው? «የምንጌጠው ለዝሙት አይደለም!» ልትሉ ትችላላችሁ:: አዎ ምናልባትም ላይሆን ይችላል:: ግን ለመደነቅ ነው:: ለመደነቅ ስትሉ ይህን ማድረጋችሁ አያሳፍራችሁምን? እናንተ ግን አሁንም መልሳችሁ «በእርግጥ ነው፤ ግን በቃ ዕድሌ ነው፤ በደንብ ለብሻለሁ፤ ለዚህ ዐይነቱ ስሜት ግን አይደለም» ትላላችሁ:: ለኔ ያላችሁትን እግዚአብሔር ያውቃል:: በግልጽ መናገር የሚገባችሁ ግን ለእኔ ነው? በድርጊታችሁ ጊዜ ለነበረው ብቻ አይደለም፤ ኋላም አንድ ቀን ለሚጠይቃችሁና ሁሉም ነገር በፊቱ ግልጥ ለሚሆነው ለእግዚአብሔር::

አሁን ተው እያልን አጥብቀን የምንመክራችሁ የእኛ ፈቃድ ለዚያ አስፈሪ ፍርድ ተላልፋችሁ እንድትሰጡ ስላልሆነ ነው:: እግዚአብሔር በነቢዩ አድሮ ለኢየሩሳሌም ሴቶች የተናገራቸው የግሣጼ ቃላት ይደርሳችሁ ዘንድ እግዚአብሔርን እንፍራው:: «አንገታቸውን እያሰገጉ፣ በዐይናቸውም እያጣቀሱ ፈንጠርም እያሉ፣ በእግራቸውም እያቃጨሉ ይሔዳሉና» /ኢሳ.፫÷፲፮/

በታላቅ ውድድር ላይ የሚፈለገው ጌጥ አይደለም:: በትግሉ ሜዳ ላይ የሚጠብቃችሁ መዝናናትና ዕረፍት አይደለም:: በጨዋታው ላይ ተወዳዳሪዎቹንና ታጋዮቹን ተመልከቱ ስለአለባበሳቸውና ስለአረማመዳቸው ትኩረት ሰጥተው ይጨነቃሉን? በፍጹም:: ነገር ግን እነዚህን ሁሉ ንቀውና ልብሶቻቸውን ወርውረው የሚመለከቱት አንድን ነገር ብቻ ነው:: በትግሉ ሜዳ ላለመቁሰል ወይም ለመቁሰል:: ዲያብሎስ እናንተን በማንኛውም መንገድ ለማጥፋት ጥርሱን እያፋጨ ይቆማል:: እናንተ ግን ሳትገነዘቡ ትቀራላችሁ:: አልያም ትኩረታችሁ ለዚህ ሰይጣናዊ ጌጥ ብቻ ይሆናል::

ወደ ገጽ ፵ ዞሯል





www.eotcmk.org

ይህ ዓምድ በሥርጭቱ ፍጥነትና በጥቃቱ ስፋት አሳሳቢ ደረጃ ላይ የደረሰውን ኤች.አይ.ቪ/ኤድስን በመከላከልና በመቆጣጠር ረገድ ማኅበረ ቅዱሳን ከኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን ልማ ትና ክርስቲያናዊ ተራድዖ ኮሚሽን እና ከብሔራዊ ኤች.አይ ቪ/ኤድስ መከላከያና መቆጣጠሪያ ጽ/ቤት /HAPCO/ ጋር በመተባበር የሚያከናውነው ሰፊ ሥራ አካል ነው::

# «በመታመሜ ደካማነቴን፤ በመፈወሴ ሃይማኖቴን አውቄአለሁ»

ዲ/ን ማለደ ዋስይሁን

**ሐ**መር፡- ስለ ራስህ ብታስተዋውቀን::

*አቶ ዓለም ብርሃኔ፡-* ስሜ ዓለም ብርሃኔ ይባላል:: ተወልጄ ያደግኩት በአ ዲስ አበባ ከተማ በአሁኑ ቂርቆስ ክፍለ ከተማ ቀበሌ 08/09 በቀድሞ ወረዳ 20 ቀበሌ 29 ቡልጋሪያ ማዞሪያ አካባቢ ሲሆን የአንደኛ ደረጃ ትምህርቴን በዕውቀት ምንጭ አንደኛ ደረጃ ት/ቤት የሁለተኛ ደረጃ ትምህርቴን በከፍተኛ 20 ሁለተኛ ደረጃ ት/ቤት የተማርኩ ሲሆን የነበረኝ ውጤት ለከፍተኛ የትምህርት ዕድል አጥጋቢ ስላልነበር ሕይወትን በተለያየ አቅጣጫ ለማሸነፍ መሮጥ ጀመርኩ:: ከልጅነት ዕድሜዬ ጀምሮ ለሥነ ጽሑፍ የነበረኝ ፍቅር እጅግ ከፍተኛ ነበር:: የሥነ ጽሑፍ ፍቅሬ አድጎ ከሁለተኛ ደረጃ ትምህርቴ በኋላ የሙዚቃ ግጥምና ዜማዎችን ማዘጋጀት እና መስጠት ጀመርኩ መንፈሳዊ ሕይወቴን በተመለከተ የነበረኝ ክርስትና የመሔድና የመምጣት እንጂ:: የሕይወት ክርስትና አልነበረም::

*ሐመር፡-* ቫይረሱ ደምህ ውስጥ መኖሩን እንዴት አወቅህ? ስታውቅስ ምን ዓይነት ስሜት ተሰማህ?

*አቶ ዓለም ብርሃኔ፡-* በሕይወትህ ውስጥ ክርስትና የሚገለጽባቸው ወቅቶች አሉ:: በእምነት ስትኖር ይገለጻል:: እኔ ግን እኖርበት የነበረው ዓለማዊ ሕይወቴ እጅግ ለእግዚአብሔር የማይመች ነበር:: ከብዙ ሴቶች ጋር ዝሙት እፈጽም ነበር:: ሰይጣን በእኔ ላይ የነበረው ዓላማ ጉድጓዴን ጥልቅ፤ አሟሟቴን የሚያሳቅቅ ማድረግ ነበርና:: በአንድ ጤና ጣቢያ የኤች አይ ቪ ቫይረስ በደሜ ውስጥ እንዳለ ከተነገረኝ በኋላ ራሴን ድንግል ማርያም እቅፍ ውስጥ ነው የከተትኩት:: ሌላ ምን አለኝ:: በኃጢአቴ በበደሌ ስለመጣብኝ ጸጸት አደረብኝ:: ብቻዬን ነገሬን በልቤ ይዤ መብሰልሰል ጀመርኩኝ:: ከነበረኝ ክብደት ላይ ወደ ዐስራ አራት ኪሎ ቀነስ:: ሰውነቴ እጅግ ተጎዳ:: ስለዚህ የነበረኝና ያለኝ ተስፋ የቃና ዘገሊላ ሰዎችን ገመና የሸፈነች እናትን መማጸን ነበር::

*ሐመር፡-* ወደ እንጦጦ መጠመቂያ ሥፍራ እንዴት ልትሔድ ቻልክ?

*አቶ ዓለም ብርሃኔ፡-* ይኼ የሚገርመኝ ታሪክ አለው:: በወቅቱ በእጄ አንዳች ሳንቲም አልነበረኝም:: ወደ ማኅደረ ስብሐት ቅድስት ልደታ ለማርያም ቤተ ክርስቲያን ሔጄ ድንግል እናቴን እንዲህ ብዬ ለመንኳት:: ቤተሰቦቼ እንዳያውቁ ሸሽገሽኝ አንቺ ሁሉን አመቻችተሽ ምራኝ ብዬ ወጥቼ ሔድኩኝ:: አንድ ጓደኛዬ በሦስተኛው ቀን ደውሎ ይጠራኝና እንጦጦ ግማሹን ዐቢይ ጾም እንኳ እንውጣ ብሎኝ፤ ቀለብና ቤት ኪራይ ችሎኝ ወደዚያ ወጣን::

*ሐመር፡-* በእንጦጦ ስለነበረህ ቆይታ ትንሽ ብታብራራልን::

*አቶ ዓለምብርሃኔ፡-* በእንጦጦ ለአንድ ወር ያህል ቆይቼአለሁ:: በዚያ የነበሩ እኅቶች ጠበል እየተጠመቅን ንስሓ መግባት፣ የተሰጠንን ቀኖና መጨረስ እንዳለብን ስለተነገረ ያንን በማድረግ መጠበል ጀመርኩ:: የሚገርመኝና የእግዚአብሔርን የሥራውን ድንቅነት መረዳት የጀመርኩት በመጀመሪያው ሳምንት ውስጥ ነው:: ጠበል መጠመቅ እንደጀመርኩ ወዲያውኑ ከፍተኛ ሕመም አጋጠመኝ:: ከሆዴ ብዙ ነገር ይወጣ ነበር:: በብዙም ላብ እዘፈቅ ነበር:: ጓደኛዬ ምን ያመኝ እንደነበር ስለማያውቅ እየተገረመ «ቢያምህም በሽታው ግን እየወጣልህ ነው» ይለኝ ነበር::

ከሰባት ቀን በኋላ ግን ስለነበረኝ ለውጥ እስከ አሁን ሳስበው እገረማለሁ:: ከፍተኛ አካላዊና ሥነ ልቡናዊ ለውጥ ተሰማኝ:: ከዚያ በኋላ እውነተኛ ሰላም በውስጤ ሰፈነ፡ መረጋጋቴ ለእኔም ለሌሎችም ይታወቅ ነበር:: የስውነት አቅሜ የተሻለ እየሆነ በመምጣቱ የሌሎችን ጠበል መሸከም ሌሎችንም ሲጠመቁ መደገፍ መርዳት ጀመርኩ ደስታ በውስጤ ሰፈነ፡፡ በእንጦጦ በሁዳዴ ውስጥ የነበረኝን ቆይታ አጠናቅቄ



«በጠበል መዳን ይቻላል»



www.eotcmk.org

ከወር በኋላ ወደ ቤቴ ተመለስኩ::

*ሐመር፡-* ቀድሞ የነበረህ የክርስትና ሕይወት እንዴት ይገለጻል?

*አቶ ዓለምብርሃኔ፡-* ቀድሞ የነበረኝ ክርስትና የየዋህነት ብቻ ነበር:: መንፈሳዊ ሕይወትን ጠልቆ ከማወቅ ዳር ላይ ሆኜ መሔድ እወድ ነበር:: ነገር ግን የድፍረት ኃጢአት ከፉኛ ይፈታተነኛል:: ሳላውቅ ያጠፋሁት አንዳች ነገር የለም:: እኔ ያጠፋኋቸውን ጥፋቶች ትክክል አለመሆናቸውን ለማወቅ በጊዜው አቅም አላጣሁም ነበር::

*ሐመር፡-* የሥነ ልቦናና አካላዊ ለውጥ ብታይም መፈወስህን ግን እንዴት አወቅህ? ያንንስ በተረዳህ ጊዜ ምን ተሰማህ?

*አቶ ዓለም ብርሃኔ፡-* መፈወሴን ያወቅሁበትን ሁኔታ ስትጠይቀኝ እኔ እግዚአብሔርን ያወቅሁበት ቀን ብለው ይቀለኛል:: ለካ እግዚአብሔር ከቶ አይተወንም:: በእውነት እግዚአብሔር ከኔጋ መሆኑን ያወቅሁት ያኔ ነው:: በእግዚአብሔር ቸርነት በእናቱ ፍቃድ ጻድቃኔ ማርያም ሔድኩኝ:: ቦታው ላይ ስደርስ አንዲት እኅት አዲስ እንግዳ መሆኔን አውቃ ስለ ቦታው ሥርዓት ነገረችኝ ስለ ሱባኤ ባላውቅም እንደ ምእመኑ መጾም፣ መስገድ እና መጸለይ ጀመርኩ:: ቀን ቀን ከገዳሙ ጀርባ ዛፎች ሥር መዋልና መማጸን፣ ማታ ወደ ማደርያዬ መሔድ ጀመርኩ:: በሦስተኛው ቀን ከሰዓት በኋላ ላይ አንድ ራእይ ተሰጠኝ:: በፍርሀትና በድንጋጤ ስለዚህ ራእይ አባቶች ጠየቅሁ:: በአጋጣሚ የጠየቅኋቸው አባት ከሌላ ገዳም ለሱባኤ የመጡ ታላቅ አባት ነበሩ:: አንዳች ሳላዋያቸው የተያዝኩት በዘመኑ በሽታ እንደሆነ አሁን እንደዳንኩ ሲነግሩኝ ምን የምደብቀው አለ:: እውነት መሆኑን ነግሬያቸው፤ ምስጢር የገለጹላቸውን አምላክ አመስግኜ፤ በእውነት ተመክሬ ለምርመራ ወደ አዲስ አበባ ተመለስኩ:: ከበሽታው ነጻ መሆኔን በምርመራ ሳረጋግጥ ደስታዬ ወደር አልነበረውም:: ከልጅነቴ ጀምሮ በልቤ ያለችው ድንግል አማለደችኝ:: እንጦጦ በቆየሁበት ጊዜ እንደዳንኩ ስለተነገረኝ እንጦጦ ማርያም ምስክርነቴን ሰጠሁ::

*ሐመር፡-* መፈወስህ ለሃይማኖትህ ጥንካሬ ምን አስተዋጽኦ አደረገልህ?

*አቶ ዓለም ብርሃኔ፡-* ምን ይጠየቃል:: የእግዚአብሔርን ፍቅር፣ የድንግል ማርያምን ድንቅ ቃል ኪዳን፣ አማላጅነቷን በእውነት አውቄአለሁ:: እየሔድኩበት የነበረውን ሕይወት ማዳመጥ ጀመርኩ:: ፄዘወትር ጸሎቴ መዘመር፣ ከዘፋኝነት ኑሮ መውጣት ለዚያም ቀዳዳውን መፈለግ ነበር:: እግዚአብሔር ቢፈቅድ ስለሃይማኖቴ እየጠየቅሁ፤ እያነበብኩና እየተማርኩ ያንን ቀንበር ጥዬ ለመዘመር ጌታን እየለመንኩ ነው:: ስለዚህ በመታመሜ ደካማነቴን በመፈወሴ ሃይማኖቴን አውቄአለሁ::

*ሐመር፡-* አሁን ኑሮህን በምን ሁኔታ ላይ ነው?

> በሥጋ ለተፈወስነውም ቢሆን አንድ ታላቅ አደራና ሓላፊነት አለብን፤ ያም ነፍሳችንን ማደን ነው:: ንስሓ ገብተው ነገር ግን በሥጋ ያልተፈወሱ ሰዎች የነፍስ ድኅነታቸውን ያገኛሉ:: በሥጋ የተፈወስነው እኛ ግን እግዚአብሔር ብዙ ይፈልግብናል:: ቀሪ ዘመን ስላለን «ዳግም እንዳትበድሉ» ብሎናል:: ካጠፋንም ከቀደመው የከፋ ነገር ስለሚገጥመን ነፍሳችንን የማደን ሓላፊነታችንን መወጣት ይገባናል::

*አቶ ዓለም ብርሃኔ፡-* አሁን ሥራ ተቀጥሬ እየሠራሁ ነው:: አግብቼም የአንዲት ሴት ልጅ አባት ሆኜአለሁ:: እግዚአብሔር ይመስገን::

*ሐመር፡-* በእንጦጦ አካባቢ ባለው የጠበል መጠመቂያ አሉ የምትላቸው ችግሮች ወይም መጠናከር አለባቸው የምትላቸው መልካም ጅምሮች ካሉ?

*አቶ ዓለም ብርሃኔ፡-* እኔ እጠመቅ ከነበረበት ጊዜ አንሥቶ እስከ አሁን ድረስ የእንጦጦ ማርያም ጠበል ታላላቅ የፈውስና የተአምራት ቦታ ነው:: በአካባቢው አሉ የሚባሉት ችግሮች የተወሰኑ ናቸው:: ምእመኑ በተለይ ኤች አይ ቪ ፖዘቲቭ ሆነው የሚመጡ ጠበልተኞች ቦታው ላይ ሲደርሱ የቦታውን ሥርዓት ጠበል ቦታ በር ላይ ሲደርሱ ይነገራቸዋል:: በተነገራቸውም አግባብ ይኖራሉ:: ነገር ግን ታማሚው ጥያቄ ካለው፣ መንፈሳዊ ዝለት ሲገጥመው፣ ፈተና ሲበረታበት የሚታነጽበት የማታው የስብከት መርሐ ግብር በቂ አይደለም:: በአካባቢው በእንጦጦ ብቻ ሳይሆን በሌሎችም ታላላቅ የጠበል የፈውስ ቦታዎች መንፈሳዊ የምክር ማዕከላት ቢቋቋሙ ለዚህም ማንኛውም የቤተ ክርስቲያን ልጅ የሆነ እገዛና ድጋፍ ቢያደርግ መልካም ነው:: በተጨማሪም በስንቅ ማለቅ የፈውሳቸውን ጊዜ አቋርጠው የሚሔዱ ሰዎች የሚደገፉበት ማዕከል ያለመኖር ዋና ችግር ነው:: በእርግጥ በጠበል ቦታ ያሉት የንስሐ አባቶች እና የወጣቶች አገልግሎት እጅግ የሚያደስደንቅና ሊበረታታ የሚገባው ነው::

*ሐመር፡-* አሁንም ጠበል እየተጠመቁ ፈውስን ከእግዚአብሔር ተስፋ ለሚያደርጉ ምእመናን ምን ትላለህ?

*አቶ ዓለም ብርሃኔ፡-* የእግዚአብሔር ቸርነት ቅርብ ናት፤ የኛ ልብ ነው ሩቅ:: ይህንን ለማለት ምክንያት አለኝ:: ፈውሳችን ሲፈጥንም ሲዘገይም እዳ አለብን:: ልባችን ላይ ያልገረዝነው ወይም ያልተሰናበትነው ኃጢአት ካለ ድነን ተመልሰን ወደ ጥፋት ልንገባ ወደ ትፋታችን ልንመለስ እንችላለን:: ወደአለፈው ኃጢአታችን ላለመመለስ ወስነናል? ልባችን ላይ የቀረ የሰወርነው ያልተናዘዝነው ኃጢአትም ካለ ፈውሳችን ይርቃል:: ፈጥነንም ስንድን እዳ አለብን መዳናችን የምሥራች ነው:: ግን ወደ ጥፋታችን እንዳንመለስ ምን ወሰንን? ምንስ ተማርን? ከሁሉም ግን ፍጹም ንስሓ፣ ፍጹም እንባ እና ክርስቲያናዊ ትዕግሥትና ጽናት እንደ ሠለስቱ ደቂቅ ሊኖረን ይገባል:: ሰይጣንን አንተ በኃጢአቴ ምክንያት ሞትን ብታመጣብኝና አምላኬ ባያድነኝ እንኳ ዳግም ወደ ኃጢአት አልመለስም እንበለው:: አሁኑኑ እንወስን፤ የሚላችሁን ስሙት ያለች እናት አምላካችን የሚለንን ከሰማን አሁኑኑ ታማልደናለች:: የሚወደን እርሱ ዳሰሰን የመጣውም እኛን ለመፈለግ ነውና አይዟችሁ እመኑ እንጂ እንድናለን::





www.eotcmk.org

በጠበሉ ይዳስሰናል፤ መዳንም እንችላለን::

*ሐመር፡-* ሌሎች በቫይረሱ ተይዘው ነገር ግን በቤታቸው ተስፋ ቆርጠው ላሉስ ምን ትላለህ?

*አቶ ዓለም ብርሃኔ፡-* ስንት ጊዜ እንሞታለን ክርስቲያኖች? ሀገራችን እኮ ሰማያዊ ናት:: ተስፋችን በእግዚአብሔር ነው:: ሰው ለአንድ ትንፋሽ እንኳን ከእግዚአብሔር እንዴት ይለያል ነፍሳችን የሱን እስትንፋስ እየኖረች ለምን? ደግሞስ እስከ መቼ ከእግዚአብሔር እንርቃለን:: ንስሐ የተሠራው እኮ ለእኛ ነው:: ወደ አባቶች እንቅረብ፤ እንናዘዝ፤ ካህናት አባቶች የፈጣሪ ዓይኖች ናቸው፤ በእነርሱ ውስጥ እኛን ያየናልና:: እናንተም ኑና እንደኛ መስክሩ:: አምላክ ቅዱሳን ደግሞ ይፈልጋችኋል፤ ያድናችኋልም:: እንደውም በእናንተ ላይ ያለችው ዓላማ ልዩ ናት:: በመመለሳችሁ ታላቅ ደስታ ይደረጋልና::

ምክንያት ዕረፍት ባደረጉ ሰዎች መካከል ያለው ልዩነት የጊዜ ነው እንጂ ሞት ለሁሉም የማትቀር ጽዋ ናት:: በሥጋ ለተፈወስነውም ቢሆን አንድ ታላቅ አደራና ሓላፊነት አለብን፤ ያም ነፍሳችንን ማዳን ነው:: ንስሓ ገብተው ነገር ግን በሥጋ ያልተፈወሱ ሰዎች የነፍስ ድኅነታቸውን ያገኛሉ:: በሥጋ የተፈወስነው እኛ ግን እግዚአብሔር ብዙ ይፈልግብናል:: ቀሪ ዘመን ስላለን «ዳግም እንዳትበድሉ» ብሎናል:: ካጠፋንም ከቀደመው የከፋ ነገር ስለሚገጥመን ነፍሳችንን የማዳን ሓላፊነታችንን መወጣት ይገባናል::

*ሐመር፡-* በዓለም ላይ መዳን አይችልም የተባለው ይህ በሽታ በቅድስት ቤተ ክርስቲያናችን ጠበል መሸነፉን ስታስብ ምን ይሰማሃል?

*አቶ ዓለም ብርሃኔ፡-* በአሁኑ ወቅት የዓለም ምሁራን የዚህን በሽታ መድኃኒት

# ሰይጣንን አንተ በኃጢአቴ ምክንያት ሞትን ብታመጣብኝና አምላኬ ባያድነኝ እንኳ ዳግም ወደ ኃጢአት አልመለስም እንበለው::

ለማግኘት ብዙ ቢጥሩም አልሆነላቸውም:: እግዚአብሔር አምላክ እኛን ማዳኑን በዚህች ቤተ ክርስቲያን መግለጹ አንዲት፣ ቀዳማዊት፣ በደሙ የመሠረታት እውነተኛይቱ እምነት ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ መሆኗን ያሳያል:: ለዚህም አምነው የሚጠመቁ ሁሉ የሚድኑባት እውነተኛዋ መንገድ መሆኗን ሳስብ ልቤ በደስታ ይዘላል፤ እግዚአብሔር ይመስገን::

የቀደመችውን መንገድ እናስብ፤ በፍጹም እምነት በንስሐ ተመልሶ በዚህች ቤተ ክርስቲያን የማይድን ማንም የለም:: እግዚአብሔር ሁላችንንም ለመቀበል እጆቹ እንደተዘረጉ ናቸው:: ሁላችሁንም ክርስቲያኖች ስለቤተ ክርስቲያናችን አብዝተን እንጨነቅ:: ትላንት ፊደል ያስተማረችንን ቤተ ክርስቲያን ዛሬ ብዕር ስንጨብጥ ረስተናል? ቤተ ክርስቲያን ለኛ እምነት ፊደል ታሪክ ኢትዮጵያዊነት ሰጠችን፤

እኛስ ለቤተክርስቲያን ምን አደረግንላት? ምንም፤ ራሳችንን እስኪ እንጠይቅ?

*አቶ ዓለም ብርሃኔ፡-* ቤተክርስቲያን በአስተዳደር ደረጃ ማድረግ እያለባት ያላደረገችው ምን ነገር አለ ብለህ ታስባለህ?

ቤተ ክርስቲያን ምእመናን በኑፋቄ ትምህርትና በድህነት ምክንያት እንዳይበታተኑባት መጠበቅ አለባት:: ይህ ደግሞ መንፈሳዊ ብቻ ሳይሆን ሰብአዊም ግዴታ ነው:: ስለዚህ በእኔ አስተያየት ስብከተ ወንጌልን በስፋት ማዳረስ ይኖርባታል:: ከዚህ ባልተናነሰ ምእመናንን ከጸሎት ጐን ለጐን ሠርቶ መብላትን ባሕል እንዲያደርጉ፤ ሠርተው ካገኙት ደግሞ ሌሎችንም እንዲደግፉ እነርሱንም መስለው ሠርተው እንዲጠቀሙ በፍቅር መተሳሰብን ማስተማር አለባት:: ቤተ ክርስቲያን ባላት የአስተዳደር መዋቅርና በምእመናኑ ተነሣሽነት በሀገሪቱ ኢኮኖሚ ውስጥ ከፍተኛ ተሳትፎ ሊኖራቸው ይገባል:: አስተዳደሩም ከምእመናን የሚሰበሰበውን ገቢና ቤተ ክርስቲያን በራሷ ያላት ታሪክና ቅርስ የሚያስገኝላትን ገቢ ወደ ሌሎች የልማት ክፍሎችም በማዞር በገቢዋ ገቢ ማግኘት አለባት:: እንጂ ገቢዋን ተጠቃሚ ብቻ እየሆነች እርሷና ልጆቿ ለማኝ መሆን አይገባቸውም:: በዚህ ጊዜ ሀገራችንም ትጠቀማለች::ቀ

*እግዚአብሔር ይስጥልኝ*

## ሕሊብ የጸናውን

ዓለም ስትጋደል ሰጠጣል ስትሞክር
[illegible]
አቴያው ንዴል ሸና ሙታሙን ሲጠፋ
ፍቅር ሲቀዘቅዝ ትዕቢት ሲገነፋ
ክሕቶ ኑ ሕሳት ነጥሮ የወጣውን
ሕናብርት ሳይበሉት ባህር የተፋውን
ሰድራጉን ሳይሰግድ ሞት ያልገደለውን
ደዌ ሲያማቅቀው ያመሰገነውን
ሰስት ሕሰራትን ሕንደ ክብር ቀጥሮ
ሰይፋን በሕንገቱ ያጠለቀ ደፍሮ
ዝሙትን ሲጋበዝ ያሰበ ጌታውን
የቁልቁል በመስቀል የተሰቀለውን
ሕንተም ሕንድትጸና ሕሊብ የፀናውን

*ከዲ/ን መለፍን ጽርሱ*

*ከሐዋሳ ጤና ሳይንስ ግቢ ጉባኤ*

*ሐመር፡-* በበሽታው በሥጋ ባይፈወሱ ስለሚያልፉ ሰዎች ምን ትላለህ?

*አቶ ዓለምብርሃኔ፡-* ሰዎች በንስሓ ወደ አምላካቸው ቀርበው ወደ ጠበል ሲመጡ ሁለት ዓይነት ድኅነትን ያገኛሉ:: ያም የሥጋና የነፍስ ድኅነት ነው:: ሰዎች በሥጋ ባይድኑ እንኳን በነፍስ ዘላለማዊቷን ቤት መንግሥተ ሰማያትን ይወርሳሉ:: ትልቁ ሞት እኮ ያ ዘላለማዊው ሞት ነው:: የዘላለም እሳት ከሱ በንስሓ ታጥበን ድነን መትረፍ በራሱ ለኛ ትልቅ ሽልማት ነው:: ለኛ ትልቅ አክሊል ነው:: ስለዚህ በሥጋ ባይፈወሱ እንኳን በንስሓ ከተመለሱ በቃ ትልቅ ድላቸውና ሽልማታቸው ገነት መንግሥተ ሰማያት ናት እላለሁ::

እኔ በዚህ በሽታ ሞትን እንዳልቀበል ፈቃዱ በመሆኑ ድኛለሁ እንጂ ሞቱ አትቀርም:: በሥጋ በተፈወሱትና በበሽታው



'

www.eotcmk.org

የሐመር መጽሔት ዝግጅት ክፍል የግእዝ ቋንቋ ያለውን የማይተካ ዘርፈ ብዙ ሚና በማጤንና የአንባብያንን ፍላጎት መሠረት በማድረግ ይህን *«አቡጊዳ - የግእዝ ቋንቋ ትምህርት»* የተሰኘ ዓምድ ከ፲፱፻፺፬ ዓ.ም. ጀምሮ መክፈቱ ይታወሳል:: በዓምዱ የሚቀርበው ትምህርት በአዲስ አበባ ዩኒቨርስቲ መምህራንና ተማሪዎች በሚያዝያ ወር ፲፱፻፺፯ ዓ.ም በተቋቋመው *«የልሳነ ግእዝ ወዳጆች ማኅበር»* የሚዘጋጅ ነው:: አቅራቢውም በአዲስ አበባ ዩኒቨርስቲ መምህር እና የግእዝ ተናጋሪ ቤተሰብ መሥራች ናቸው:: ማኅበሩ ለግእዝ ቋንቋ ፍላጎት ያላቸውን ሁሉ በቋንቋው ማንበብ፣ መጻፍና መናገር የማስቻል፣ በቋንቋው የተጻፉትን ዕድሜ ጠገብ መጻሕፍት በመመርመር ያካበቱትን ልዩ ልዩ ሀብት ለትውልድ የማቆየት ዓላማና ግብ አንግቦ የተነሣ ነው::

*መ/ር ደሴ ቀለብ*

# ግእዝ ከእስያ ልሳናት ጋር ሲነጻጸር

በዓለም የሥነ ልሳን ጥናት መሠረት የአካድ /የአሦር - አካዳውያን/ ቋንቋ ጥንታዊ ማንነቱ የተረጋገጠው በአንዳንድ የሥነ ጽሑፎች ቅሬት ሲሆን ይህ ቋንቋ በሥነ ልሳን ተማራማሪዎች ዘንድ የምሥራቅ ሴማዊ ልሳን ተብሎ በቅርብ ጊዜ ከተገኘው ከኤብላዊ ቋንቋ ጋር የሚመደብ ነው:: አካድ እና አሦር በመጽሐፍ ቅዱስ ክፍል በኦሪት ዘፍጥረት የተገለጹ እና ከኖኅ ዘመን በኋላ የታወቁ መካናተ ሥልጣኔ ናቸው:: በሥነ ጽሑፍ መረጃ የአካድ ልሳን ፳፭፻ ቅ.ል.ክ. እንደነበረ ይነገራል:: በኋላ በአራም የአራማውያን የተባለው ቋንቋም ራሱን የገለጸበት ጊዜ ነበር:: ይሁን እንጂ በሥነ ቅሬተ ምድርም ሆነ በሥነ ልሳን ተመራማሪዎች ዘንድ አካድ የኢኮኖሚ፣ የሕግ፣ የአስተዳደር፣ የታሪክና የሥነ ጽሑፍ መረጃዎች እንደነበረው የተረዳ ነው::

የካምም ልጆች ኩሽ፣ ምጽ/ስ/ ራይም፣ ፋጥ፣ ከነዓን ናቸው:: የኩሽም ልጆች ሳባ፣ ኤውላጥ፣ ሰብታ፣ ሬጌም /ራዕማ/፣ ሰበቅታ ናቸው:: የሬጌም ልጆችም ሳባ፣ ዮድዳን ናቸው:: ኩሽም ናምሩድን ወለደ፣ እርሱም በምድር ላይ ኀያል መሆን ጀመረ እርሱም በእግዚአብሔር ፊት ኀያል አዳኝ ነበረ፤ ስለዚህም በእግዚአብሔር ፊት ኀያል አዳኝ እንደናምሩድ ተባለ:: የግዛቱም መጀመሪያ በሰናኦር አገር በባቢሎን ኦሬክን አርካድ /አካድ/ ካሌድን /ካልኔ/ ናቸው:: አሦርም ከዚያች አገር ወጣ:: ነነዌን የረሆቦት የተባለችውን ከተማ ካለህን በነነዌና በካለህ መካከልም ዳስን ሬሴንን ሠራ:: እርስዋም ታላቂቱ ከተማ ናት ምጽራይምም ሉዲምን ኢኒሜቲምን /ዐናሚምን/ ላህቢምን ንፍታሌምን ጳጥሮስኒምን /ፈትሩሲምን/ ከእነርሱ የፍልስጥኤም ሰዎች የወጡባቸውን ከስሎሂምንና ቀፍቶሪምንም ወለደ:: /ዘፍ.፲:፮-፲፬/

አፍሪካውያንም በየዘመናቱ የሥልጣኔ ማእከሉን በወንዞች ጤግሮስ እና ኤፍራጥስ ዳር እንደ መሠረቱ ፤ አካዳውያን ፈለገ ግዮንን የራሱን ለአፍሪካውያን ሕዝቦች የሥልጣኔ መሠረት አድርጎ መቆየቱ የሚታወስ ታሪክ ነው:: አፍሪካውያን በራሳቸው ፊደል ቢጠቀሙም በተለያዩ የዓለም ዐቀፍ ተጽዕኖዎች ሥር በመውደቃቸው መሠረታዊውን ፊደለ ጽሕፈታቸውንና ቋንቋቸውን ሊያጡ ችለዋል:: ይህንን ፊደል ጠብቃ የተገኘችው ኢትዮጵያ ናት:: የኢትዮጵያ ፊደልና ቋንቋም በሥነ ጽሑፍ መረጃነት ለዓለም ከቀረቡት ልሳናት የሚታወቅባቸው ባሕርያት ሲኖሩት ከጠፋው ከአካድ ቋንቋ ይበልጥ በሥነ ጽሑፍ መረጃነቱ ራሱን ያሳደገ ሆኖ እናገኘዋለን:: ይህንም በቋንቋው ጠባዕያት ከአካድ ጋር ቢመሳሰል በራሱ ደግሞ ከአፍሮ እስያ ከቋንቋ መለየት ይህ ሴማዊና ካማዊ ብሎ ለመጠቅለል የሚያስቸግር ቢሆንም በቋንቋ ጥናት ዋና የመለያ ፍጥረት በማጥናት መመደብ የሚቻል ይሆናል:: ከዚህ አንጻር ግእዝን ሴማዊ፣ ደቡብ ሴማዊ፣ ሰሜን ሴማዊ /በኢትዮጵያ/ አድርገው የሚከፋፍሉበት:-

ልዩ ልዩ አስማተ መካናት መመሳሰል ምሳሌ - ሳባ፣ የቋንቋዎቹ የራሳቸው መመሳሰል፣ የሥነ ቅርጽ መመሳሰል ወዘተ ሲሆን ግእዝ ከነዚህ ቋንቋዎች መደብ የሚለዩት ጠባዕያት አልነበሩትም ወይም ደግሞ በእነዚህ ቋንቋዎች የተዘነጉ ጽሑፎች በግእዝ ግን አልነበሩም ማለት አይቻልም:: ለአብነትም ያህል «ተስዑቱ» የሚለው የጥንት ሥርው ምን ይመስላል የሚለው ሲጠና ከአረማይክ ይልቅ የግእዝ «ታስዕ» የሚለው ቃል ቀዳሚነት ጥንታዊነት ይኖረዋል:: በዚህም ምክንያት አረማይክ ያጣውን ግእዙ በመጠበቁ እንዴት አረማይኩ ለግእዝ በዘመኑ ያጣውን ቃል ሊያቀብለው ቻለ የሚል ጥያቄ አስነሥቷል:: ይህ ብቻ ሳይሆን ግእዝ በድምፀ ንባቡ የሌሎች የአፍሪካ ልሳናት እና የሩቅ ምሥራቅ ልሳናት የሚታወቁበትን የድጠ ምፀት ንበት በመያዝ ከአፍሪካ ልሳናት ጋር ሊያመሳስለው ይችላል::

በተጨማሪም በግእዝ ቋንቋ በቀዳማይ አንቀጽ ዝርዝር ጊዜ የአገናዛቢ ቅጥያዎችን የምንጨምር ሲሆን አካድያን ግን የስማዊነት ባሕርይን የሚያሳይ ነው::

| ቀዳማይ:- | |
|---|---|
| ግእዝ | አካድያን |
| አነ - ቀተልኩ | አቅቱል |
| አንተ - ቀተልከ | ተቅቱል |
| አንቲ - ቀተልኪ | ተቅቱሊ |
| አንትሙ - ቀተልክሙ | ተቅቱላ |
| አንትን - ቀተልክን | ተቅቱላ |
| ንሕነ - ቀተልነ | ኒቀቱላ |
| ውእቱ - ቀተለ | ተቅቱል |
| ይእቲ - ቀተለት | ኢቅቱል |
| ውእቶሙ - ቀተሉ | ኢቅቱሉ |
| ውእቶን - ቀተላ | ኢቅቱላ |

| ካልአይ - ግእዝ | አካድያን |
|---|---|
| አነ - እቀትል | አቀተል |
| አንተ - ትቀትል | ተቀተል |
| አንትሙ - ትቀትሉ | ተቀተላ |
| አንትን ትቀትላ | ተቀተላ |
| ንሕነ - ንቀትል | ኒቀተል |
| ውእቱ - ይቀትል | ኢቀተል |
| ይእቲ - ትቀትል | ተቀተል |
| ውእቶሙ - ይቀትሉ | ኢቀተሉ |
| ውእቶን - ይቀትላ | አቀተላ |
| አንቲ - ትቀትሊ | ተቀተሊ |

ጥንታዊ ቃላትን እየወሰዱ ቋንቋን በአንድ መመደብ የሚቻል ነው:: ጥንታዊ አናባቢ /ዕ/ ከአካድያን ይልቅ በግእዝ መጠበቁ ግእዝን ልዩ ያደርገዋል:: አካድያን እና ግእዝ በካልአይ የመጥበቅ ድምፅ ሲኖራቸው ጥንታዊ የደቡብ ዐረብ ልሳን ግን የሌለው በመሆኑ ግእዝን እንዴት ከሌላው ቋንቋ ከሳባ መጣ እንላለን? በተጨማሪ የግእዝን ከሌሎች ከሚመስላቸው ከማዕከላዊው ምሥራቅ ሀገራት ቋንቋዎች ስናገናኘው የጥንታዊ የቋንቋ ባሕርይ ቅርጽና ድምፅ መያዙን የምናገኝባቸውን ቃላት እንጠቀማለን::

## ግእዝ ከሌሎች ቋንቋዎች ጋር

| *ዕብራይስጥ* | *አረማይክ* | *ግእዝ* | *አማርኛ* |
|---|---|---|---|
| ዓሙድ | ዓሙድ | ዓምድ | ምሰሶ |
| አሐድ | ሐድ | አሐድ | አንድ |
| ቃዶሽ /ቂዳሽ ኪ.ክ/ | ቃዲሽ | ቅዱስ | ቅዱስ |

## ጥብርያዶስ...

ከገጽ ፴፫ የዞረ

### ጥብርያዶስ በዛሬው ዘመን ላይ

ጥብርያዶስ ወይም የገሊላ ባሕር ቅዱስ ሐይቅ ነው:: ጌታችን በዘመኑ በሂደተ እግሩ የቀደሰውና፤ በአፉ ቃል የገሠጸው ባሕር ነውና:: ዛሬም ቢሆን በዚህ ውብና አምላካዊ ተአምር የተገለጸበት ባሕር ላይ የሚጓዝ አማኝ ክርስቶስን በዓይነ ልቡናው ማዕበሉን ሲገሥጽ፣ ሞገዱንም ሰላማዊ ሲያደርግ ማየት ይቻላል:: እጅግ ውብ የሆነው ይህ ባሕር እንደሰማይ የጠራ ሰማያዊ ቀለም ተላብሶ በእርጋታና በጸጥታ ከአጽናፍ አጽናፍ ተንጣሎ ይታያል:: ነፋሱ የማይቆም ቢሆንም ሰውን የሚያቀዘቅዝና የሚያረጋጋ እንጂ የሚያውክ አይደለም:: እነ ቅዱስ ጴጥሮስ ይቀዝፏቸው የነበሩትን ጀልባዎችን የሚመስሉ ጀልባዎች ዛሬም ለአምላክ ትእዛዝ ታዛዥ ሆነው መረብን ይሞሉ የነበሩትን የዓሣ ዝርያዎች ያሠግራሉ:: ነገር ግን ከጥጦስ ጦርነትና የኢየሩሳሌም ጥፋት በኋላ ብዙ መንደሮችና ሀገሮች ከዳርቻው አሸዋ ውስጥ እንደተቀበሩ ቀርተዋል:: ዛሬ ከዚህ ሐይቅ ዳርቻ ላይ የሚገኙት ከተሞች መግደሎንና ጢባርያ ብቻ ናቸው:: መግደሎን ጌታችን ሰባት አጋንንትን ያወጣላት የማርያም ሀገር ናት:: /ሉቃ.፰፥፪-፫/ ዛሬም ድረስ ከጥንት ጊዜ ጀምሮ እስከ አሁን በጥብርያዶስ ዳርቻ የምትገኘው ይህች ታናሽ መንደር ብቻ ናት:: በእርሷ ውስጥ ግን ጌታችን ታላቅ የሆነውን የማዳኑን ሥራ ሠርቶባታል:: በሰው የተናቁትንና ታናሽ የተባሉትን የሚያከብር አምላክ ስሙ ይመስገን!

ጥብርያዶስ ግን ዛሬም ከ፳፻ ዓመታት በኋላ በእርሱ ላይ የተፈጸሙትን ድንቅና አምላካዊ ታሪኮች በውስጡ እንዳቀፈ አለ:: ማንም መንፈሳዊ ሰው ወደዚያ ሔዶ ከቦታው በረከትን ሳያገኝ፤ ብአእምሮውም የአምላካችን ፍቅር ሳይቀረጽ፤ መንፈሱም በመጽሐፍ ቅዱሳዊ ታሪክ ሳይመሰጥ አይመለስም:: በእውነትም ዛሬ ከጥብርያዶስ ዳርቻዎች የቆመ ሰው ቢኖር አምላክ ደቀ መዛሙርቱን ሲጠራ እንዲሁም ከትንሣኤ በኋላ ለሐዋርያነት ሲያጸና የቆመበት አለመሆኑን እንዴት እርግጠኛ መሆን ይችላል? «ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ እዚህ ዳርቻ ላይ ቆሞ ነበር፤ በዚህ አልነበረም» ለማለት ምስጢሩንና ታሪኩን አምላክ በሚገልጸው መጠን ማወቅ ያስፈልጋል:: ያን ምስጢር ደግሞ ሊያካፍል የሚችለው ቅዱሱ ሐይቅ ብቻ ነው::

የጌታችንና የአምላካችን ኢየሱስ ክርስቶስ ስሙ ለዘለዓለም ይመስገን አሜን::◆



www.eotcmk.org


ግእዝ ቋንቋ እና ዕብራይስጥ በየዘመናቱ ባላቸው ዕሜታዊ ግንኙነት ይታወቃሉ፡፡ ቃላቱም የበለጸጉ የሥነ ጽሑፍ ሀብት በማስቀመጣቸው ታሪካዊ እና ሃይማኖታዊ ግንኙነትን ያጠነከሩ ሆነው እናገኛቸዋለን፡፡ ይሁን እንጂ የጥንቱን መልክዕ አንዳንዴ ግእዙ አንዳንዴ ዕብራይስጡ ሲጠብቁ እናገኛለን፡፡ ለአብነትም፡-

| ዕብራይስጥ | ግእዝ | ትርጉም |
|---|---|---|
| ሽ ናይም | ሠኑይ | ሁለተኛ |
| ሻሉሽ | ሠሉስ | ሦስተኛ |
| ሽሞን | ሠሙን | ሥምንት |
| ሐረሽ | ሐረሠ | አረሠ |
| ጠቭን | ጠብን | አረዳ |
| ሳፋር | ሰፈረ | ቆጠረ |
| ካታቭ | ከተበ | ጻፈ /ከተበ |
| ሮእሽ | ርእስ | ራስ |

*__ማስታወሻ፡-__* የዕብራይስጡ ሠ እንደ ሽ ይነበባል ስንል የአማርኛውን ሽ ግን አይደለም፡፡ ግእዙ ደግሞ ከአማርኛው ሽ ይልቅ ወይም እንደ ዕብራይስጡ «ሽ?» /ሠ/ ከመነበቡ ይልቅ «ሠ»ን በ«ሴ» አመሳስሎ ያነበዋል፡፡ ምሳሌ የዕብራይስጥ ሻሎም በግእዙ ሠላም ነው፡፡ ዕብራይስጡ በጥንቱ በመጽሐፍ ቅዱሳዊ ይዘቱ የነበሩትን ብ>ፍ ድ>ት እና ክ>ሕ በመለወጥ ጠባዩ ይታወቃል፡፡ ይህ በሌላውም ልሳን ለምሳሌ በግእዝ ያለ ጠባይም ነው፡፡

## በግእዝ እንነጋገር

| *ገባሬ መንግሥት /የመንግሥት ሠራተኛ/* | *ሊስትሮ /ሐብራቴ አሣዕን/* |
|---|---|
| እፎ ኀደርከ? | እግዚአብሔር ይሰባሕ |
| ምንት ሀለወከ? | ቀለምኑ ወሚመ |
| ምን አለህ? | ቀለም ነው ወይስ?... |
| እዎ | ኪዊ ውእቱ አልብየ ካልእ |
| አዎ | ኪዊ ነው ሌላ የለኝም |
| በል ቅብዖ | እሆ |
| በል ቀባው | እሺ |
| ተማሃሪኑ አንተ? | እዎ |
| ተማሪ ነህ? | አዎ |
| እስፍንቱ? | ሣልሳይ |
| ስንት? | ሦስተኛ |
| እስከናሁ! | እፎ |
| እስከአሁን | እንዴት? |
| እስፍንቱ አዝማኒከ? | ዐሥሩ ወሰዱሱ |
| ዕድሜህ ስንት ነው? | ዐሥራ ስድስት |
| ለምንት ጐንደይከ? | እምጽራልዩ ውእቱ ዘመጻእኩ |
| ለምን ዘገየህ? | ከገጠር ነው የመጣሁ |
| እስፍንቱ ብሩር ይትረከብ? | በበዕለቱ፣ ዕሥራ ይከውን |
| ስንት ብር ይገኛል? | በቀየኑ ፳ ይሆናል |
| ምስለ መኑ ትነብር? | ምስለ ቢዕየ |
| ከማን ጋር ትኖራለህ? | ከጓደኛዬ ጋር |
| እም አይቴ መጻእከ? | እም ወልቂጤ |
| ከየት መጣህ? | ከወልቂጤ |
| ቤተ ክርስቲያን ተሐውር? | እዎ አሐውር ኀበ እግዝእትነ |
| ቤተ ክርስቲያን ትሔዳለህ? | አዎ ወደ እመቤታችን እሔዳለሁ |
| በጽባሕኑ ወሚመ በምስየት? | በጽባሕ ውእቱ ለኪዳን |
| በጧት ነው ወይስ በምሽት? | ለኪዳን በጧት ነው፡፡ |



## የሴቶች አለባበስና...

**ከገጽ ፴፫ የዞረ**

ስለ ድምፅ /አነጋገር/ ምንም ነገር አላልኩም፡፡ ምንም እንኳ በጣም የማስመሰል ነገር በዚህም ቢታይባችሁ፡፡ ስለሽቶም ሆነ ስለ ሌሎች ጉዳዮች ምንም አላልኩም፡፡ በዓለም ሴቶች የምንጠላው /የሚቀየሙን/ በእነዚህ ጉዳዮች ነው፡፡ ለድንግልና የሚሰጠው ክብር ጠፍቷል፡፡ መከበር እንደሚገባት ማንም ሰው አያከብራትም፡፡ ጊዜ የሚሰጡት ለራሳቸው ክብር ባልሆነ ጉዳይ ላይ ነው፡፡ በእግዚአብሔር ቤተ ክርስቲያን ሴቶች ከመንግሥተ ሰማይ እንደሚመጡ መስለው መታየት አይገባቸውምን? አሁን ግን ተንቀዋል፡፡ ምንም እንኳ ከእናንተ መካከል ጠንቃቆች ብትኖሩም እነዚህ ግን ሊናቁ ይገባቸዋል፡፡

ዳሩ ግን ቤቷን የምትመራ ባልና ልጆች ያሏት ሴት ለዓለም ሙት መሆን ሲገባት ስለራሷ ከማሰብ ይልቅ ለዓለም ራሷን መሥዋዕት ታደርጋለች፡፡ ይህቺ ሴት ታዲያ ልትንቅህና ልታሞኝህ አትችልምን? ምንኛ ጥንቃቄ እንደምታደርግ ተመልከት! እንዴት የሚያም ነገር ነው! በትሕትና አለባበሳችሁ ውድ ጌጣጌጦችን ለመታያ ከለበሱት ሴቶች እናንተ በልጣችሁ ተገኙ፡፡ በወርቅ ተንቆጥቁጠው /አሽብርቀው/ በልዩ ሁኔታ ከሚለብሱትም እንዲሁ፡፡ በትሕትና አለባበሳችሁ ተሽላችሁ ተገኙ፡፡ በመልካም ሥራዎች ተጠምዳችሁ ስትገኙ ራሳችሁን በጌጣጌጥ ለማሸፈን አትፈልጉም /አትሹትም/፡፡

በእነዚህ ምክንያቶች ግን ደናግላን ከዚህ ዓለም ሴቶች ባነሰ ሁኔታ ይከበራሉ፡፡ በድንግልና ሕይወት የሚጠበቅባቸውን ሥራዎች አይሠሩምና፡፡ ይህ ለሁሉም የሚነገር አይደለም፡፡ የሚገባ ልብስን በመልበስ /ትሕትናን/ ይማሩ ዘንድ በስሕተት ላሉት እንጂ፡፡ ትሕትናን ሊያስተምሩ የሚችሉ ከወቀሳ የጸዱት የሚገባውን ለሌሎች ሊያስተምሩ ይችላሉ፡፡ ነገር ግን ይህ ግሣጼ በምግባር /በተግባር/ መገለጥ እንዳለበት እወቁ፡፡ እነዚህን ነገሮች የምንላችሁ /የምንነግራችሁ በእጅጉ እንድናዝንባችሁ አይደለም፡፡ እናንተን እንድናርማችሁ፣ በእናንተ እንድንደሰት እንጂ፡፡ ሁላችንም እነዚያን እግዚአብሔር የሚቀበላቸውን ነገሮች ሠርተን ከጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ በተገባልን ቃል ኪዳን መሠረት በረከቱን እናገኝ ዘንድና በክብሩ እንድንኖር ነው፡፡

St. Chrysostom, Nicene & Post Nicene Fathers Vol. 13. Homilies on Timothy (432-35)

✢

# ከአንባብያን ለአንባብያን

## የፋሲካ ሌሊት

ትዕግሥት ታፈረ

ሰላም ለሁላችሁ ይሁን!

እንዴት በጃችሁልኝ? የፋሲካ ሆድ እንዴት ነው? በፋሲካ ሰሞን ሆዱ 'ማያጉረመርምበት መቼም አይኖርም:: ለሃምሳ አምስት ቀናት ከቅባት ጋር የተረሳሳ ሆድ የእንኳን ደህና መጣህ ይሁን፣ ጾም ከከረመ ሆድ ጋር ያስመገባባት ይሁን መንጫጫቱ የተለመደ ነው:: እንግዲህ እዚህ ላይ ነው ብልጥ መሆን «በመጠን ኑሩ» የሚል ጥቅስ እንዳለ አትርሱ::

ኑ ምስው የትንሣኤ ሌሊት የት ነበራችሁ? በቤተ ክርስቲያን፣ በጭፈራ ቤት፣ በእንቅልፍ፣ በስካር፣ በዝሙት...

እናንተ ከመናገራችሁ በፊት እኔ የራሴን ላውራ:: መቼም ሺ ጊዜ ተግኘ ብሆን ... ሰዎች ከርታታ ብለው ስም ቢያወጡልኝ ለእምነቴ አልታማም የጌታዬን የመድኃኒቴን የኢየሱስ ክርስቶስን የትንሣኤ በዓል ያከበርኩት በቤተ ክርስቲያን አፀድ ውስጥ ነው::


ክርስቶስ ተንሥአ እሙታን ... በዓቢይ ኃይል ወሥልጣን

አሰሮ ለሰይጣን ... አጋአዞ ለአዳም

እም እዜሰ ...ኮነ ...ፍስሐ ወሰላም ... እያልኩ::

እናላችሁ የሌሊቱ ቅዳሴ አልቆ ወደ ቤቴ ስመለስ እኔን የመሰለ ነጩላ ለባሾችን በእጥፍ የሚበልጡ ሴቶቹ ከፊል 'ራቁት በሆነ አለባበሳቸው፣ ወንዶቹ ቀጥ በጠፋው ፀጉራቸው በእነሱ ልብ አምረው፣ በእኛ ልብ ለትዝብት ተዳርገው መንገዱን አስንቀውታል::

መንገዳቸው ወዴት እንደ ሚያቀና መቼም ሳትጠረጥሩ አት ቀሩም:: እኔ እንደሆንኩ ገና ድሮ አውቄባቸዋለሁ::በሕማማት ሰሞን ጆሮዬ በዘፈን ማስታወቂያዎች ሲደነቁር ምንም አል ቀረውም ነበር:: መቼም እግሬ አርፎ አይቀመጥ የመንገድ ዳር ግድግዳዎች የመብራት፣ የስልክ እንጨቶች ሁሉ የፋሲካን በዓል ድግስ ደልፋሉ::




ለዚያውም አስቡት «ፍቅሬን ረገጥሽው፣ ክህደትህ አንጀቴን ቆረጠው፣ አይኖችሽ፣ ጥርሶችሽ ...» የሚሉ ሐሳቦች ሳቢ ቸው ዘፈኖች በሌሊት መኳተን ምን ይባላል?

«ለነገሩ ለስ ሀገርም ሲዘፈን ይችላል?» የሚል ይኖራል:: ሀገርን ማን ፈጠራት? ቃሉ ብቻውን ዓለምን የፈጠረ እግዚአብሔር ነው::

የፋሲካን በዓል አስመልክተው ወንዱም ሴቱም መንገድ ላይ «ጨርቅ ሆነዋል»:: የፋሲካ ባለቤት «አትስከር» አለ? ወይስ «ስከር?»

ፋሲካ እኮ የባለ ዓይናማዋ ገድል አይደለም:: ፋሲካ እኮ የከሃዲ ፍቅረኛ መታሰቢያ ቀን አይደለም? ፋሲካ እኮ የአንድ ታዋቂ ዘፋኝ ድል አይደለም:: 'ፋሲካችን ክርስቶስ ኢየሱስ ነው::'

እሱ እየወደድነው አልከዳንም፤ እየጠላነው ወደደን እንጂ:: እሱ ፍቅራችን አልረገጠም፤ ጠላት ዲያብሉስን 'ረገጠልን እንጂ ...

እዚህ ላይ መግደላዊት ማርያምን ማስታወስ ግድ ይለ ኛል:: ሕይወቷን ሁሉ በዝሙት የኖረች ጌታ ኢየሱስ ክርስቶስ ወደ እሱ በመጣች ጊዜ አክብሮ በፍቅር የተቀ በላት፣ ለባት አጋንንት ያስወጣላት፣ ኃጢአቷ እንደ እግር እሳት የፈጃት ምስኪን ሴት በትንሣኤ ሌሊት የት ነበረች?

«አይ እሷ እኮ ከተደረገላት አንጻር...» ብሎ የሚያስብ ይኖር ይሆን? ያልተደረገለት በራሱ የቆመ እሱ ማን ነው? በምህረት ያልታየ ማነው?

መግደላዊት ማርያም ግን ባለውለታዋን አልረሳችም:: እንቅልፍ አላሸነፋትም፤ የተወችውየዓለም ደንኪራ አላማ ለላትም:: ለለ ፍቅረ ብዛት በመ ስቀል ላይ በስቃይ ሲቃትትያየችውን ...ርጠች በሌሊት ወደ ቀራኒዮ:: እሾሁ፣ ቆንጥሩ፣ እንቅፋቱ፣ የሌ ሊቱ ግርማ አላ ስፈራትም:: ተነ ሥቶ አየችው፤ አባቷን:: ተነሥቶ አየችው፤ በፍቅር ብቻ የማረላትን አምላክ:: ከእሷ በፊትማንም በት ንሣኤ አላየውም:: ውለታን 'ማይዘ ነጋየበለጠ ይውል ላታልና::


የሆነስ ሆነና «ወግ ቢያበዙት በአህያ አይጫንም» ይባ ላል:: ፋሲካም አልፎ አይቀርም:: በዓመቱ ይመጣል:: ያድ ርሰንና አሁን ብን ቀጣጠርስ? የፋሲካ ሌሊት የት ነን?፟

ከትዕግሥት ታፈረ

አዲስ አበባ





## የምሥራች ለጅምላና ለግል ተጠቃሚዎች




በኦሮምኛ ቋንቋ የተዘጋጁ
የመዝሙርና የስብከት ካሴቶች
በሥርጭት ላይ

ለጅምላ አከፋፋዮች   የተለየ ቅናሽ አድርገናል
ስልክ   011 124 61 81ጠ82ጠ84
ፖ.ሳ.ቁ 80078

# አዲስ የጋብቻ ፖስት ካርድ በገበያ ላይ




በጅምላ ለማከፋፈል
ለምትፈልጉ
ልዩ ቅናሽ አድርገናል።
ስልክ
0111 246181/82/84
ይደውሉልን
በፖ.ሳ.ቁ.80078
ይጻፉልን።

ዋጋ ብር 4.00

ሜጋ ማተሚያ ኃ.የተ.የግ.ማ.

©

!" #$ %
& ' ( ) * $++